# መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ

በ1ኛ ሳሙኤል መጀመሪያ ላይ እንደጠቀስነው አንደኛና ሁለተኛ በመባል የተጠቀሱት ሦስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት፣ ማለትም፣ ሳሙኤል፣ ነገሥት እና ዜና መዋዕል፣ ከጅምሩ አንድ አንድ መጻሕፍት ነበሩ:: የተከፋፈሉት ሴፕቱጀንት የተባሉት ተርጓሚዎች መጽሐፍ ቅዱስን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ በ300 BC አካባቢ በተረጐሙት ጊዜ ነው::

እነዚህ ጥምራ የነገሥት መጻሕፍት (1ኛ እና 2ኛ ነገሥት) ከሰሎሞን ንግሥና እስከ እስራኤልና ይሁዳ መማረክ ድረስ ይተርካሉ:: ከቤተ መቅደሱ መሠራት እስከ ቤተ መቅደሱ መፍረስና መቃጠል ያካትታሉ:: በእነዚህ የነገሥት መጻሕፍት ውስጥ 20 የይሁዳ (የዳዊት የንግሥ ሐረግ) ነገሥታትና 19 የእስራኤል (የተከፈለው 10 ነገድ መንግሥት) ነገሥታትን ታሪክ እናነባለን::

እነዚህን የነገሥት መጻሕፍት የጻፈ ሰው ማን እንደሆነ በግልጽ ባይታወቅም በአይሁዳውያን ዘንድ ነቢዩ ኤርምያስ እንደጻፈው ይታመናል:: ይህም እምነት በአጠቃላይ ተቀባይነት ያለው እምነት ነው:: ምንም እንኳን ኤርምያስ የተነማውና ያገለገለው የይሁዳ መንግሥት መጨረሻ አካባቢ ቢሆንም ከአንዳንድ የታሪክ መጻሕፍት በሚያገኘው እርዳታ ሊጽፍ እንደሚችል ይገመታል 1ነገ. 11÷41፣ 14÷29

እነዚህ የነገሥት መጻሕፍት የእስራኤልን ታላቅ ክብርና ከፍ ከፍ ማለት በሰሎሞን ንግሥና እንዲሁም በመጨረሻ በእስራኤልና በይሁዳ የደረሰውን ታላቅ ውድቀትና መማረክ ይተርካሉ::

1ኛ ነገሥትን ብቻ በምናይበት ጊዜ የሰሎሞንን መንገሥ፣ የእስራኤልና ይሁዳ መከፋፈል እና የኤልያስን አገልግሎት ያካትታል::

የዚህ መጽሐፍ ማዕከላዊ መልእክት፣ አለመታዘዝና አመጽ መከፋፈልን እንደሚያመጣ ነው:: ይህ መጽሐፍ የሚታወቅበት ዋና ክስተት አንድ የነበረው የእስራኤል መንግሥት ለሁለት መከፈሉ ነው:: እነዚህ የተከፈሉት ሁለት መንግሥታት የተከፈሉበት ምክንያት በንጉሥ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መተላለፍ እንደሆነ እንረዳለን:: እግዚአብሔርን ትቶ ሌሎችን አማልክትን ስላመለከ እግዚአብሔር መንግሥቱን ከልጁ ከሮብዓም ከፍሎ አሥሩ ነገድ የሰሎሞን ባሪያ ለነበረው ለኢዮርብአም ይሰጠዋል:: የይሁዳና የብንያም ነገዶች ግን በዳዊት ዘር ሐረግ ሥር ሆነው የይሁዳ መንግሥት በመባል ጸንተው ቀሩ:: መንግሥቱን ሁሉ ከሰሎሞን ልጅ ከሮብዓም ያልወሰደበትም ስለ ዳዊት ሲል እንደሆነ እናያለን (1ኛ ነገሥት 11÷11-13)::

<u>ይህ መጽሐፍ በሁለት ይከፈላል፤</u>

1. የሰሎሞን አርባ ዓመት ንግሥ (ከምዕ. 1-11)
   - ሀ. ሰሎሞን መልካም ጅማሬ ምዕ. 1-4
   - ለ. የሰሎሞን ቤተ መቅደስና ቤተ መንግሥት መሠራት ከምዕ 5-8
   - ሐ. የሰሎሞን ዓለም አቀፍ ዝናና ክብር (ምዕ. 9-10)
   - መ. የሰሎሞን ውድቀትና መነሳት (ምዕ. 11)

2. የተከፋፈለው መንግሥት የመጀመሪያው 80 ዓመታት (ከምዕ 12-22)
   - ሀ. የሮብዓም መንገሥና የመንግሥቱ መከፈል (ምዕ. 12)

ለ. የተከፋፈሉት የይሁዳና የእስራኤል ነገሥታት የመጀመሪያው ሰማንያ ዓመታት ታሪክ (ምዕ. 13-22)

- የይሁዳ ነገሥታት፣ ከሮብአም እስከ ኢዮሳፍጥ አራት ነገሥታት
- የእስራኤል ነገሥታት፣ ከኢዮርብዓም እስከ አካዝያ ስምንት ነገሥታት
- የነቢዩ ኤልያስ አገልግሎት (ከምዕ. 17-22)
- እንዲሁም የነቢዩ ኤልሳዕ መቀባትና አገልግሎት ጅማሬ (ምዕ. 19)

## ክፍል I
## የሰሎሞን አርባ ዓመት ንግሥ (ምዕ. 1-11)

ምዕራፍ 1 በዚህ ምዕራፍ የዳዊትን መሸምገል፣ የዳዊት ልጅ አዶንያስ እነግሣለሁ ብሎ መነሣትና የሰሎሞንን መንገሥ እናያለን።

ከቁ. 1-4 የዳዊትን መሸምገል ይገልጻል
«ንጉሡ ዳዊትም ሸመገለ ዕድሜውም በዛ...» ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት የሄደ ሰው ስለነበረ ዕድሜ እስከሚጠግብ ድረስ እንደኖረ እናያለን። ከቁ. 5-10 የዳዊት አራተኛ ልጅ የነበረው አዶንያስ ንጉሥ እሆናለሁ ብሎ እንደተነሣ እናነባለን። አዶንያስ የዳዊት አራተኛ ልጅ እንደነበረ በ2ሳሙ. 3÷2-5 እናነባለን። ከአዶንያስ በፊት የተወለዱት ሦስቱ፣ በኵሩ አምኖን (በአቤሴሎም ተገድሎ ነበረ) ሁለተኛው ዶሎህያ (በ1980 ዓ.ም. በታተመው መጽሐፍ ቅዱስና በእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ኪልአብ ይለዋል)፣ ሦስተኛው ደግሞ አቤሴሎም በዳዊት ላይ ባመጸ ጊዜ የተገደለው ነበረ። ምናልባት አዶንያስ በዚህ ጊዜ ከዳዊት ልጆች በሕይወት ያለሁት በኵር እኔ ነኝ ብሎ መነሣቱ ይሆናል። ሁለተኛ የነበረው ልጅ (ኪልአብ) ምናልባት ሞቶ ሊሆን ይችላል «ንጉሥ እሆናለሁ ብሎ ተነሣ» የሚለውን ቃል የእንግሊዝኛው መጽሐፍ "He exalted himself" ወይም «ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ» ይለዋል። እግዚአብሔር ከፍ ከፍ የሚያደርገው እንጂ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ መጨረሻው እንደማያምር ፍጻሜውን በዚሁ ምዕራፍ እናያለን። ራሱን ከፍ ከፍ ማድረግ ብቻ ሳይሆን «ሰረገሎችንና ፈረሰኞችን በፊቱም የሚሮጡ አምሳ ሰዎች አዘጋጀ።» ይላል። አንድ ዓመጸኛ ሰው ሲነሣ ምን ጊዜም ቢሆን በፊቱ የሚሮጡ ሰዎች (አጨብጫቢዎች) አያጣም። አጨብጫቢዎች ስላገኘን ብቻ ጤናማ ጎዳና ላይ ነን ማለት አይደለም።

በቁ 6 ላይ የምናገኘው ቃል ግን የዳዊትን ደካማ ጎን የሚያሳይ ነው። «አባቱም ከቶ በሕይወቱ ሳለ፡- እንዲህ ለምን ታደርጋለህን? ብሎ አልተቆጣውም ነበር።» ይላል። ዳዊት ከአምላኩ ጋር የሠመረ ግንኙነት ቢኖረውም እንደ አባት ልጆቹን እንደሚገባ እንዳላሳደገ እናያለን። ስድ አድርጎ የማሳደጉንም ፍሬ ሲያጭድ በልጆቹ ታሪክ ማየት እንችላለን። የበኵር ልጁ አምኖን ግማሽ እህቱን አስነወራት፣ ሦስተኛ ልጁ የነበረውም አቤሴሎም ለእርሱ ሙሉ እህቱ ነበረችና አምኖንን ተበቅሎ ሲገድለው በ2ሳሙ 13 እናነባለን። ቀጥሎም አቤሴሎም አባቱን ዳዊትን ለመገልበጥ ብሎ ሲያምጽበትና በመጨረሻም በኢዮአብ ሲገደል እናነባለን። አሁን ደግሞ የዳዊት አራተኛ ልጅ የነበረው አዶንያስ ያለ ዳዊት ፈቃድ ራሱን ሊያነግሥ ሲነሳሳ እናያለን። ይህ ሁሉ ችግር በዳዊት ልጆች ላይ እንዲከሰት፣ ዳዊት ልጆቹን ስድ አድርጎ ማሳደጉ ትልቅ አስተዋጽዖ አለው።

አዶንያስ እነግሣለሁ ብሎ ሲነሳ፣ የጦሩ አለቃ የነበረው ኢዮአብና ካህኑ አብያታር ተባብረውት እንደነበረ እናነባለን። ነገር ግን ነቢዩ ናታንና ካህኑ ሳዶቅ ከአዶንያስ ጋር አልተባበሩም። ከዚህ የምንረዳው፣ በእግዚአብሔር ቤት ቆይተው የእግዚአብሔርን ሥራ ብዙ

ያዩ ሰዎች እንኳን ውጫዊውን ሁኔታ ብቻ አይተው የእግዚአብሔርን ሐሳብ ሊስቱና ሊያምጹ እንደሚችሉ ነው። ነቢዩ ናታንና ካህኑ ሳዶቅ ግን የአዶንያስን ውበትና የሰሎሞን ታላቅ ወንድም መሆኑን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድና ምርጫ ነበረ የተመለከቱት።

ከቁ. 11-27 ነቢዩ ናታን የሰሎሞንን እናት ቤርሳቤህን በመምከር ሄዳ ለዳዊት ሁኔታውን እንድታስረዳና «ልጅሽ ሰሎሞን ይነግሣል» ብሎ ቃል የገባላትን እንድታስታውሰው ወደ ዳዊት ይልካታል። እርሱም ከእርሷ በኋላ ሄዶ ቃልዋን ያጸናል። መንፈሳዊ ዐይናቸው የተከፈተላቸው ሰዎች በውጭ የሚታየውን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ሐሳብ ስለሆነ የሚመለከቱት ነቢዩ ናታን በዚህን ጊዜ የእግዚአብሔርን ሐሳብ ሲያገለግል እናያለን። ሥጋ ከዙፋን ወርዶ መንፈስ (የእግዚአብሔር ሐሳብ) እንዲነግሥ ያደረገው እርሱ ነበር።

ከቁ 28-48፦ ዳዊት ለቤርሳቤህ ሰሎሞን እንደሚነግስ እንደገና ሲምልላትና፣ ናታንን ካህኑ ሳዶቅንና በናያስን ልኮ ሰሎሞንን ቀብተው እንዲያነግሡትና በዙፋኑ ላይ እንዲያስቀምጡት ሲያዛቸው እናያለን። በቁ 29 ዳዊት ለቤርሳቤህ የማለበትን ቃል እናነባለን፤ «ነፍሴን ከመከራ ሁሉ ያዳነኝ ሕያው እግዚአብሔርን!» ብሎ ይምልለታል። ይህ መሐላ የሚያስደንቅ መሐላ ነው። እግዚአብሔር ነፍስን «ከመከራ ሁሉ» የሚያድን እንደሆነ ሕያው ምስክር ነኝ ማለቱ ነው። እንግዲህ በመዝ. 34፥19 «የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው እግዚአብሔር ከሁሉ ያድናቸዋል።» በማለት ይቀኛል።

ይህንን መሐላ ከማለላት በኋላ፤ «በእግዚአብሔር <u>እንደማልሁልሽ</u>፣ <u>እንዲሁ</u> ዛሬ በእውነት <u>አደርጋለሁ</u>።» ይላታል። መሐላ ቀላል ነገር እንዳልሆነ የሚያስረዳ ቃል ነው። መሐላ በተግባር መገለጽ (መደረግ) ያለበት ውሳኔ እንጂ ባዶ ቃል ብቻ አይደለም።

በዚሁ ምዕራፍ ላይ ዳዊት ለቤርሳቤህ እንደማለላት ሲፈጽመው እናያለን። ሰሎሞን ተቀብቶ በዙፋን ላይ ከተቀመጠ በኋላ፤ «ንጉሡም (ዳዊት) ደግሞ ዓይኔ እያየ ዛሬ በዙፋኔ ላይ የሚቀመጠውን የሰጠኝ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን፣ አለ።» (ቁ. 48)

የብዙ ነገሥታትና ባለሥልጣኖች ችግር፤ ሥልጣንን በቃኝ ብለው ዓይናቸው እያየ የሚተካቸውን ሰው አዘጋጅተው በፋንታቸው መንገሥ አለመቻል ነው። ሥልጣናቸውን እንደያዙ ጃጅተው መሞት ይመርጣሉ።

ከቁ 49-53 ንጉሡ ሰሎሞን ለአዶንያስ ምሕረት ሲያደርግለት እናያለን።

ከዚህ ምዕራፍ የምናያቸው ሁለት ተጨማሪ ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው፤ አዶንያስ ከእግዚአብሔር ፈቃድና ሐሳብ ውጭ አምጾ እነግሣለሁ ባለ ጊዜ፤ «ብዙ በሬዎችንና ፍሪዳዎችን በጎችንም» እንደሠዋ እናነባለን። ቁ 25 ይህ ቃል በጣም የሚገርመው፤ ያመጸው በእግዚአብሔር ሐሳብ ላይ ሆኖ መሥዋዕት አቀርባለሁ የሚለውም ለእግዚአብሔር ነበር። ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር ቤት የምናየው እርስ በርስ የማይታረቅ ድርጊት ይህን ይመስላል። ሰዎች በአመፃቸው የእግዚአብሔርን ቤትና የእግዚአብሔርን ሕዝብ እየበጠበጡ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለማቅረብ ይፈልጋሉ። እግዚአብሔርን እያገለገሉ ያሉ ይመስላቸዋል። የእግዚአብሔርን ሕዝብ እየከፋፈሉ የክርስቶስን አካል የሚያሳድጉ ይመስላቸዋል። እግዚአብሔር እንደዚህ ዓይነቱን በአመጽ እጅና ልብ የሚቀርብን መሥዋዕት ይጸየፋል። በሆሴዕ ውስጥ እግዚአብሔር ስለ እንደዚህ ዓይነት መሥዋዕት ይናገራል። «መሥዋዕቴን ያቀርባሉ፣ ሥጋንም ያርዳሉ፣ ይበላሉም እግዚአብሔር ግን አይቀበላቸውም በደላቸውንም ያስባል፣ ኃጢአታቸውንም ይቀጣል።» (ሆሴዕ 8፥13) እግዚአብሔር ከእንደዚህ ዓይነት የአመጽ መሥዋዕት ይጠብቀን።

ሌላ የምናየው ነጥብ የሰሎሞንን ብላቴንነት ነው ሰሎሞን በነገሠ ጊዜ የታሪክ ሰዎች እንደሚሉት ከ15 ዓመት በላይ አልነበረም። ሰሎሞን የተወለደበትን ጊዜ ስናይ በእውነትም ትንሽ ብላቴና እንደነበረ እናስተውላለን። ሰሎሞን የቤርሳቤህ ልጅ እንደመሆኑ፤ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር በኃጢአት የወደቀው በንግሥናው አጋማሽ ላይ እንደነበረ ይታመናል፤ ይህ

ከሆነ ዳዊት በንግሥናው ሃያ ዓመት አካባቢ ከቤርሳቤህ ጋር በዝሙት ከወደቀና ያ ህፃን ከተወለደ በኋላ ናታን መጥቶ ህፃኑ እንደሚሞት ይነግረዋል። ስለዚህ ቢያንስ የአንድ ዓመት ጊዜ ማለፍ ነበረበት ማለት ነው። ዳዊት ስለ ኃጢአቱ በእግዚአብሔር ፊት ወድቆ የህፃኑንም ሞት ተቀብሎ ከተነሣ በኋላ ነው ሰሎሞን ተፀንሶ ከቤርሳቤህ የተወለደው። በአጠቃላይ ከዳዊት ውድቀት በኋላ ቢያንስ ሁለት ዓመታት ቆይቶ ነው ሰሎሞን የተወለደው ማለት እንችላለን። ይህ አቆጣጠር የሰሎሞንን ዕድሜ ቢበዛ 18 ያደርገዋል ማለት ነው። ዋናው ቁም ነገር እግዚአብሔር ከዕድሜ ሳይሆን ጉዳዩ ከቅባት ላይ ስለሆነ፣ ሰሎሞን በዚህ በለጋነት ዕድሜው ለንግሥና ሲቀባ እናያለን።

1ኛ ነገሥት ምዕ 2፤ ዳዊት የመጨረሻውን ቃልና ኑዛዜ ለሰሎሞን ሲነግረው፤ እንዲሁም ሰሎሞንን ሊቀናቀኑ የሚችሉት ሁሉ አንድ በአንድ ሲገደሉና ዙፋኑ ጸንቶ ሲደላደል እናያለን።

ዳዊት ለሰሎሞን በመጀመሪያ የሰጠው ምክር፡- «በርታ ሰውም ሁን፤ የምታደርገውንና የምትሄድበትን ሁሉ ታከናውን ዘንድ በሙሴ ሕግ እንደተጻፈ፣ ሥርዓቱንና ትእዛዙን ፍርዱንና ምስክሩንም ትጠብቅ ዘንድ በመንገዱም ትሄዱ ዘንድ፣ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቅ።» ቁ. 3 ይህ ምክር ለማንም የእግዚአብሔር ሰው የሚሆንና የሚያስፈልግ ምክር ነው። ለኢያሱ የተሰጠውም ምክር ተመሳሳይ እንደነበረ በኢያሱ ምዕ. 1 ላይ ማየት እንችላለን የእግዚአብሔርን ቃልና ትእዛዝ አክብረን ካልተመላለስን ነገሮች አይከናወኑልንም። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቃችን ግን ሰው እንድንሆንና እንዲከናወንልን ይረዳናል።

ከዚህ ምክር ቀጥሎ ዳዊት በሕይወቱ የበደሉትንም ውለታ ያደረጉለትንም ሰዎች በመጥቀስ ሰሎሞን ተገቢውን ነገር ለእያንዳንዳቸው እንዲያደርግ ያሳስበዋል። የመጀመሪያው፤ የሠራዊት አለቃ የነበረው ኢዮአብ ነው። ኢዮአብ፤ ሁለቱን የእስራኤል ጭፍራ አለቆች፣ አበኔርንና አሜሳይን ስለገደለ በሰላም ወደ መቃብር አታውርደው ይለዋል። ይህንን የፍርድ ቃል ስናነብ በእውነትም ኢዮአብ ሊሞት እንደሚገባው ማየት እንችላለን፤ ጥያቄው፣ ለምን ያኔውኑ ዳዊት ራሱ ይህንን ፍርድ በኢዮአብ ላይ አልፈጸመበትም ነው። የሚቀጥለውን የዳዊትን ትእዛዝ ስናይ ግን ሰው ምንም ጻድቅ ቢሆን ምሕረቱ ፍጹም እንዳልሆነ እናያለን። ሳሚ የተባለው ሰው፣ ዳዊት ከአቤሴሎም በሸሸበት ጊዜ፤ ብርቱ እርግማን ስለረገመው፤ ምንም እንኳን በ2ሳሙ. 19÷23 ላይ «አትሞትም» ብሎ ቢምልለትም የተበደለውን ሳይረሳ አሁን የቂም በቀል ትእዛዝ ለልጁ ሲያስተላልፍ እናያለን። «የምታደርግበትን አንተ ታውቃለህ፣ ሽበቱንም ከደም ጋር ወደ መቃብር አውርድ።» የእግዚአብሔር ምሕረት ብቻ ፍጹም ነው። እግዚአብሔር ይቅር ሲል «ኃጢአትህንም ደግሞ አላስብም» ነው የሚለው።

ዳዊት ከሞተ በኋላ ሰሎሞን ወንድሙን አዶንያስን ለምን ሱነማይቱን አቢሳን ላግባ ብለህ ጠየቅህ ብሎ ሲያስገድለው፤ እንዲሁም ኢዮአብን በእግዚአብሔር ድንኳን ውስጥ የመሠዊያውን ቀንድ የሙጥኝ ብሎ የያዘበት ድረስ ልኮ ሲያስገድለውና ካህኑን አብያታርን ከክህነት ሲሽረው እናያለን። እነዚህ ሁሉ የሰሎሞን መንግሥት ተቀናቃኞች ነበሩ። ወንድሙን አዶንያስን ግን እንደው ምክንያት አገኘሁ ብሎ ማስገደሉ ይሆናል እንጂ ለምን አንዲት ሴት ላግባ ብሎ ጠየቀ ብሎ ወንድሙን ማስገደል ትክክል አይመስልም።

ዳዊትን ረግሞ የነበረውን ሳሚን ግን በቁም እስር ካጋዘው በኋላ «በኢየሩሳሌም ቤት ሠርተህ ተቀመጥ ወዲህና ወዲያም አትውጣ። በወጣህበትም ቀን፣ የቄድሮንንም ፈፋ በተሻገርክበት ቀን ፈጽመህ እንድትሞት እወቅ፣ ደምህ በራስህ ላይ ይሆናል።» ብሎ ካስማለው በኋላ፤ በሦስተኛው ዓመት ባሪያዎቹ ስለ ኰበለሉበት እነርሱን ፍለጋ አትለፍ የተባለውን ፈፋ አልፎ በመሄድ ባሪያዎቹን ቢያስመልስም የገባውን ቃል ኪዳን አፍርሶአልና በነፍሱ ላይ ሲፈርድ እናያለን። ሰሎሞንም ይህንን ነገር በሰማ ጊዜ፤ አስጠርቶ የገባውን ቃል ኪዳን እንደገና በማሳሰብ ሲያስገድለው እናያለን። ብዙ ጊዜ ሰዎች ጊዜያዊና ምድራዊ የሆነውን

ለማሳደድና ለማስመለስ ሲሉ ነፍሳቸውን በኪሳራ ውስጥ ሲጥሉ ይገኛሉ። ስለዚህ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ «ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል» ያለው።

ምዕ 3. ይህ ምዕራፍ ሰሎሞን ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን መልካም ጅማሬ ያሳያል። በተለይ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ካቀረበ በኋላ እግዚአብሔር በሌሊት በሕልም ተገልጦለት ምን እንድሰጥህ ትፈልጋለህ? ሲለውና ሰሎሞንም እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘውን ልመና እንዳቀረበ እንመለከታለን። ልመናው፤ በዚህ ታላቅና ብዙ ሕዝብ ላይ መፍረድ እችል ዘንድ አስተዋይ ልቦና ስጠኝ የሚል ነበረ።

ቁ 10 «ሰሎሞንም ይህን ነገር ስለ ለመነ ነገሩ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው» ሰሎሞን የለመነው ልመና በራስ ወዳድነት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን የተሰጠውን ኃላፊነት እንደሚገባ መወጣት እንዲችል የሚረዳውን ነገር ነበር የለመነው ልመናው ያተኮረው በራሱ ጥቅም ላይ ሳይሆን በሕዝቡ ጥቅም ላይ ነበረ። «<u>በሕዝብህ ላይ መፍረድ ይችል ዘንድ</u> ለባሪያህ አስተዋይ ልቦና ስጠው።»

እኛስ ዛሬ እግዚአብሔር ምን ልስጥህ ቢለን ምን እንላለን? ልመናችን እንደ ሰሎሞን እግዚአብሔርን የሚያስደስት ይሆን?

የሰሎሞን ልመና ትክክለኛ ልመና ስለነበረ፤ እግዚአብሔር የለመነውን ብቻ ሳይሆን ያልለመነውንም ባለጠግነትና ክብር ሲያጐናጽፈው እናያለን።

እግዚአብሔር ለሰሎሞን ሕዝቡን ያስተዳድር ዘንድ ጥበብን እንደሰጠው እስራኤል ሁሉ የሚያውቅበት ሁኔታ ሲከሰት በዚሁ ምዕራፍ እናያለን። ከቁ. 16-28 ሁለት ጋለሞቶች ተካሰው በሰሎሞን ፊት ሲቀርቡ እናያለን። የተካሰሱበት ምክንያት እንደሚከተለው ነው። ሁለቱም በአንድ ቤት ሲኖሩ ሳሉ ሁለቱም ልጅ ይወልዳሉ። አንደኛዋ በልጅዋ ላይ ስለተኛችበት ልጅዋ በሌሊት ሞተ። በእኩለ ሌሊት ተነስታ የሞተውን ልጅዋን ለሌላኛዋ አስታቅፋ የሌላዪቱን ደህነኛ ልጅ ሰርቃ ወሰደች። የደኅነኛው ልጅ እናት በማለዳ ስትነሳ ልጅዋ ሞቶ ታገኘዋለች። ብርሃን በሆነ ጊዜ በደንብ ስትመለከተው የእርስዋ ልጅ አይደለም። ስለዚህ ሁለቱም ደኅነኛው የእኔ ልጅ ነው የሞተው የአንቺ ነው እየተባባሉ በሰሎሞን ፊት ይቀርባሉ። ንጉሡ ሰሎሞንም፤ ሰይፍ አምጡልኝ ብሎ «ደኅነኛውን ሕፃን ለሁለት ከፍላችሁ አንደኛውን ክፍል ለአንዲቱ ሁለተኛውን ክፍል ለሁለተኛይቱ ስጡ አለ።» የደኅነኛይቱ ሕፃን እናት ለልጅዋ ስለራራች ደኅነኛውን ለእርስዋ ስጣት እንጂ አይገደል ስትል፤ ሁለተኛይቱ ግን «ይከፈል እንጂ ለእኔም ለአንቺም አይሁን» አለች ንጉሡ ሰሎሞንም የእውነተኛዋን እናት ርኅራኄና የሌላይቱን እናት ጭካኔ አይቶ እውነተኛዋ እናት ይህች ናትና ደኅነኛውን ሕፃን ለእርስዋ ስጧት ብሎ ሲፈርድ እናያለን።

ይህ ታሪክ የሰሎሞንን ጥበብ ብቻ ሳይሆን በዘመናችን ያሉትን ሁለት ዓይነት መንፈሳዊ እናቶችም ያሳየናል። መንፈሳዊ እናቶች ስንል የጾታ ጉዳይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እግዚአብሔር ልጆቹን መንጋውን እንዲጠብቁና እንዲንከባከቡ ኃላፊነት የሰጣቸው መንፈሳዊ መሪዎች ማለታችን ነው። አንዳንዶቹ፣ ምናልባትም አብዛኛዎቹ፣ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በትጋትና በጥንቃቄ የሚጠብቁ ቢሆኑም አንዳንዶቹ ግን፣ በራስዋ ልጅ ላይ ተኝታ እንደገደለችው፣ ከዚያም አልፋ የሌላዪቱን ጤናማ ልጅ እንደሰረቀች፤ የራሳቸውን ኃላፊነት በቸልተኝነት፣ በስንፍና፣ በራስ ወዳድነትና በአመጽ አፍነው ገድለው፣ የሌሎችን በታማኝነትና በትጋት የያዙትን ኃላፊነት፣ የሚሰርቁና የሚረብሹ መንጋውን የሚበታትኑና የሚከፋፍሉ፣ ሕፃኑ (የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ ቤተክርስቲያን) በጠላት ሰይፍ ቢከፈል እንኳን ግድ የሌላቸው፣ ለራሳቸው ጥቅም ብቻ የቆሙ ቀጥረኞች ናቸው። በእነዚህ ሰዎች ምክንያት ስንት ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ ተከፋፍሏል፣ ስንት ጊዜ የክርስቶስ አካል ተቆራርጧል። ይህ ሁኔታ

ትልቅ የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ያለበት ጉዳይ ስለሆነ የእግዚአብሔር ሰው ነኝ የሚል ሁሉ ትልቅ ጥንቃቄ ሊያደርግበት የሚገባው ነገር ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠን ከባድ ማስጠንቀቂያ «በእኔም ከሚያምኑ ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ፣ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቁ ባህር መስጠም ይሻለው ነበር።» የሚል ነው። (ማቴ 18፥6) ይህ ከባድ ፍርድ ከሚወርድብን ለእግዚአብሔር ሕዝብ አንድነትና መጠበቅ ስንል ብንጎዳ ይሻላል። የክርስቶስ አካል ከሚቆረጥ፤ እኔ የእናትነት መብቴ ይቅርብኝ ሕፃኑ ብቻ አይቆረጥ ብንል ይሻላል።

ምዕ. 4 በዚህ ምዕራፍ የሰሎሞን መንግሥት መደላደልና ብልጽግና እንዲሁም እግዚአብሔር የሰጠው ጥበብ ተወዳዳሪ የሌለው እንደነበረ እናነባለን።
ከቁ 1-6 ያለውን ክፍል ስናይ በዳዊት ዘመን ዳዊትን ያገለግሉ የነበሩ የተለያዩ ሰዎች አሁን ደግሞ በዳዊት ልጅ በሰሎሞን መንግሥት ውስጥ ልጆቻቸው እያገለገሉ እንደሆነ እናያለን።

ቁ. 2 «የሳዶቅ ልጅ ካህኑ ዓዛርያስ» ከአለቆች አንዱ ነበረ

ቁ. 5 «የናታን ልጅ ዓዛርያስ የሹሞች አለቃ ነበር፤ የናታንም ልጅ ዛቡድ የንጉሡ አማካሪና ወዳጅ ነበረ።»

ካህኑ ሳዶቅና ነቢዩ ናታን የዳዊት ታማኝ አገልጋዮች እንደነበሩ በምዕ. 1 ተመልክተናል። አሁን ደግሞ ልጆቻቸው የሰሎሞን ታማኝ አገልጋዮች እንደሆኑ እናያለን። እግዚአብሔርን የሚፈራና ታማኝ የሆነ ሰው ልጆቹን እግዚአብሔርን በመፍራት ካሳደገ በእርሱ ላይ ያለው በረከትና ቅባት በልጆቹም ላይ እንደሚሆን ነው የምናየው። «ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።» ምሳሌ 22፥6 ከቁ 7-28 ያለው ክፍል የሚናገረው፤ የንጉሡ ቤተሰብና ወደ ንጉሡ ማዕድ የሚቀርቡትን ሰዎች ሁሉ ለመቀለብ በወር በወር እየተፈራረቁ የሚያስተናግዱ፣ ከእስራኤል ሁሉ የተውጣጡ 12 ሹሞች እንደነበሩና እነዚህም ሹሞች በየቀኑ ለንጉሡ ማዕድ የሚያቀርቡት የምግብ መጠን ምን ያህል እንደነበረ ያስረዳል። በአጠቃላይ ይህ ክፍል የሚያሳየው፤ እግዚአብሔር ሰሎሞንን ምን ያህል አበልጽጎት እንደነበረና እስራኤል ሁሉ እፎይ ብሎ በሰላም ድንበሩ ተስፋፍቶ ይኖር እንደነበረ ነው።

«በዙሪያውም ባለው በሁሉ ወገን ሰላም ሆኖለት ነበር።»
«በሰሎሞንም ዘመን ሁሉ ይሁዳና እስራኤል ከዳን ጀምሮ እስከ ቤርሳቤህ ድረስ እያንዳንዱ ከወይኑና ከበለሱ በታች ተዘልሎ ይቀመጥ ነበር።» (ቁ. 25) ይህንን የብልጽግናና የሰላም ሁኔታ ስናይ በሰሎሞን ጽድቅና ችሎታ ሳይሆን ትልቁን አስተዋጽዖ ያደረገው፤ አባቱ ዳዊት በዘመኑ በእግዚአብሔር ታምኖ የእስራኤልን ጠላቶች ማጥፋቱ እንደሆነ እናስተውላለን። በተለይ በ2ሳሙ. 5፥6-10 ያለውን ክፍል ስናጠና፣ ዳዊት ከኢያሱ ዘመን ጀምሮ በኢየሩሳሌም መሽገውና ማንም አያስወጣንም ብለው የነበሩትን ኢያቡሳዊያንን ፈንቅሎ እንዳወጣ ተመልክተናል። ዳዊት እነዚህን ድሎች ባይጎናጸፍ ኖሮ ሰሎሞን ይህንን ብልጽግና ሰላም ባላየም ነበር። አንዳንድ ጊዜ በሕይወታችንና በአገልግሎታችን ዕረፍትን፣ ሰላምን፣ መከናወንንና ፍሬአማነትን ስንለማመድ፤ ሌሎች ከእኛ በፊት ቀድመው መንገዱን ጠርገውልን እንደሆነ መዘንጋት የለብንም። ኢየሱስ ይህንን እውነት ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስተምር እንዲህ አላቸው። «እኔ እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ፤ ሌሎች ደከሙ፣ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ።» ዮሐ. 4፥33

ከቁ. 29-34 ያለው ክፍል የሚናገረው፤ እግዚአብሔር ለሰሎሞን ሰጥቶ የነበረው ጥበብ በዓለም ላይ ከነበሩት ሰዎች ጥበብ የበለጠ እንደነበረ ነው።
«የሰሎሞንም ጥበብ በምሥራቅ ካሉ ሰዎች ሁሉ ጥበብና ከግብጽ ጥበብ ሁሉ በለጠ።»

ይህ የሚያሳየን፤ ከእግዚአብሔር የሆነ ሰማያዊ ጥበብ ከማናቸውም ምድራዊና ተፈጥሮአዊ ጥበብ እንደሚበልጥ ነው:: ይህ ሰማያዊ ጥበብ ደግሞ የሚጀምረው እግዚአብሔርን በመፍራት ነው::

ምዕ. 5 ይህ ምዕራፍ በጢሮስ ንጉሥ በኪራምና በሰሎሞን መካከል ስለ እግዚአብሔር መቅደስ ሥራ ዝግጅት ያደረጉትን ቃል ኪዳን ያሳያል:: እንዲሁም ለመቅደሱ ሥራ የሚያስፈልገው እንጨት ድንጋይ እንደ ተዘጋጀ እናያለን::

በቁ 1 ላይ የንጉሥ ኪራምና የሰሎሞን ግንኙነት መሠረት በኪራምና በዳዊት መካከል የነበረው ወዳጅነት እንደነበረ ይነግረናል:: «የጢሮስ ንጉሥ ኪራም ለዳዊት በዘመኑ ሁሉ ወዳጁ ስለ ነበረ፣ ሰሎሞን በአባቱ ፈንታ ንጉሥ ለመሆን እንደተቀባ ሰምቶ ባሪያዎቹን ወደ ሰሎሞን ሰደደ::» ከዚህ ጥቅስ የምናስተውለው፤ ሰሎሞን መቅደሱን ለመሥራት ከኪራም ያገኘው እርዳታና በጎ ፈቃድ የዳዊት ከኪራም ጋር የነበረው ወዳጅነት ፍሬ እንደሆነ ነው:: ኪራም የአሕዛብ ንጉሥ ነበረ:: ዳዊት ግን አሕዛብ ነው ብሎ ሳይንቀው ወዳጁ ስላደረገው ልጁ ሰሎሞን የበረከቱ ተካፋይ ሆነ::

በቁ 3 ላይ ሰሎሞን ወደ ኪራም ከላከው መልእክት ውስጥ አንድ ሐሳብ እናያለን:: «እግዚአብሔር ከእግሩ በታች እስኪጥልለት ድረስ በዙሪያው ስለ ነበረ ሰልፍ አባቴ ዳዊት የአምላኩን የእግዚአብሔርን ቤት መሥራት እንዳልቻለ አንተ ታውቃለህ» ይለዋል:: ከዚህ ጥቅስ ውስጥ ማየት የምንፈልገው ነጥብ፤ እግዚአብሔር ጠላቶቻችንን ከእግራችን በታች እስኪጥልልን ድረስ መታገስ እንዳለብን ነው:: እግዚአብሔር ጠላቶቻችንን ከእግዚአብሔር በታች እስከሚያደርግልን ጊዜ በዙሪያችን ሰልፍ ይኖራል፣ ሕይወታችን በውጊያ የተሞላ ይሆናል፤ ሆኖም በዚያን ጊዜም ቢሆን እንኳን በመሸነፍ ሳይሆን በእያንዳንዱ ውጊያ እያሸነፍን መሄድ እንደምንችል ከዳዊት ሕይወት ቀደም ብለን ተመልክተናል:: እግዚአብሔር ጠ ላቶቻችንን ከእግራችን በታች ከጣለልን በኋላ ግን ከሰልፉና ከውጊያውም እናርፋለን:: እንደ ሰሎሞን ዘመን የሰላምና የዕረፍት ዘመን ስለሚኖረን የእግዚአብሔርን መቅደስ የእግዚአብሔርን ሥራ ባረፈ ልብ መሥራት እንችላለን:: ዳዊት የእግዚአብሔርን ውጊያ ተዋጋ፣ ሰሎሞን ደግሞ የእግዚአብሔርን ሥራ (መቅደሱን) ሠራ:: እግዚአብሔር ጠላቶቻችንን ከእግራችን በታች ጥሎልን ዕረፍት የሚሰጠን፣ እጃችንን አጣምረን እፎይ እንድንል ሳይሆን የእርሱን መቅደስ እንድንሠራለት ነው:: በክርስትና ሕይወታችን የእግዚአብሔርን ውጊያ ካልተዋጋን ወይም የእግዚአብሔርን መቅደስ ካልገነባን መንፈሳዊ እንቅልፍ ውስጥ ገብተናል ማለት ነው:: የእግዚአብሔር ቃል፤ «ከእንቅልፍ የምትነቁበት ዘመን እንደደረሰ ዘመኑን እወቁ» ይለናል::

ሰሎሞን በቁ4 ላይ «እግዚአብሔር በዙሪያዬ ካሉት ዕረፍት ሰጥቶኛል፣ ጠላትም ክፉም ነገር የለብኝም::» ካለ በኋላ በቁ 5 መጨረሻ ላይ «... ለአምላኬ ለእግዚአብሔር ስም ቤት እሠራ ዘንድ አስባለሁ::» በማለት እግዚአብሔር ዕረፍትን የሰጠው ቤተ መቅደሱን እንዲሠራለት እንደሆነ ያሳስበናል::

በቁ 7 ላይ ኪራም ለሰሎሞን የሰጠውን መልስ ስናነብ ዳዊት ለኪራም ወዳጅ ብቻ ሳይሆን ጥሩ የእግዚአብሔር ምሥክር ሆኖለት እንደነበረ እናስተውላለን:: «ኪራምም ... በዚህ በታላቅ ሕዝብ ላይ ጥበበኛ ልጅ ለዳዊት የሰጠ እግዚአብሔር ዛሬ ይመስገን አለ::» ኪራም ያመሰገነው የአሕዛብ ጣዖታት አማልክትን ሳይሆን የእስራኤል አምላክ የሆነውን እግዚአብሔርን ነው::

በሚቀጥሉት ቁጥሮች፦ በሰሎሞንና በኪራም የተደረገውን ቃል ኪዳንና የቤተ መቅደሱን ሥራ ዝግጅት እናያለን:: ከቁ. 13-16 ስናነብ ቤተ መቅደሱን ለመሥራት በአጠቃላይ ከኪራም ሰዎች ሌላ 183,600 ተሰማርተው እንደነበረ እናያለን::

በቁ 18 ላይ «... ቤቱንም ለመሥራት እንጨቱንና ድንጋዮቹን አዘጋጁ።» በማለት አንድን ሥራ ከመጀመር በፊት ለዚያ ሥራ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ ያስተምረናል።

## ምዕራፍ 6

1ነገሥት ምዕራፍ 6 ይህ ምዕራፍ ሰባት ዓመት ስለ ፈጀው የሰሎሞን ቤተ መቅደስ መሠራት ይተርካል። በቁ 1 ላይ የቤተ መቅደሱ መሠራት የተጀመረበት ዘመን ሰሎሞን በነገሠ በአራተኛው ዓመት እንደነበረና ይህም እስራኤላውያን ከግብጽ ከወጡ ከ480 ዓመታት በኋላ እንደሆነ ይገልጻል። ይህንን መረጃ ይዘን የእስራኤላውያንን የታሪክ ጉዞ ከዘመናት አንጻር መረዳት እንችላለን። ከግብጽ ወጥተው ለ40 ዓመታት በምድረ በዳ የተቅበዘበዙበትን፣ የሳዖልንና የዳዊት የ40 የ40 ዓመታት ንግሥና ዘመናት፣ እንዲሁም የሰሎሞንን የ4 ዓመታት የንግሥና ዘመን ከ480 ዓመታት ላይ ስንቀንስ (480-40-40-40-4) 356 ዓመታት ይቀራሉ። ይህም ማለት እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡ ጀምሮ ሳዖል እስከ ነገሠበት ጊዜ ድረስ 356 ዓመታት ናቸው ማለት ነው። ከእነዚህ ዓመታት ላይ ኢያሱ በተስፋይቱ ምድር የኖረበትን ዘመን በመጽሐፈ ኢያሱ እንዳጠናነው በግምት 25 ዓመታት ያህል ስንቀንስ፣ ከኢያሱ ሞት እስከ ሳዖል መንገሥ ድረስ የመሣፍንት ዘመን ማለት ነው ወደ 330 ዓመታት ያህል ይሆናል።

ከዚህ ምዕራፍ የምናየው ተጨማሪ ነገር፣ ስለ ቤተ መቅደሱ አሠራር ነው። በቁ 7 ላይ «ቤቱም በተሠራ ጊዜ ፈጽመው በተወቀሩ ድንጋዮች ተሠራ፤ በተሠራም ጊዜ መራጃና መጥረቢያ የብረትም ዕቃ ሁሉ በቤቱ ውስጥ አልተሰማም» ይላል። ከዚህ ጥቅስ የምናስተውለው፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የተሠራው አስቀድመው በሌላ ስፍራ በኃዳ ተጠ ርበውና ተወቅረው በተሠሩ ድንጋዮች እንጂ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የጠራቢዎችና የወቃሪዎች ድምፅ እያስተጋባ እንዳልነበረ ነው። የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሁካታና የጫጫታ ድምፅ የሚሰማበት ስፍራ እንዳልሆነ እናያለን። በአዲስ ኪዳንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዋጮችንና ገበያተኞችን ገበታቸውን እየገለበጠ በጅራፍ ያስወጣቸው በቤተ መቅደሱ ውስጥ የማይገባ ሁካታና ድምፅ ስለፈጠሩ ነበር። በዘመናችንም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የእግዚአብሔር ቤት ሊሠራ የሚችለው፣ በቅድሚያ በኃዳቸው ተጠርበው ተወቅረው በተሠሩ ሕያዋን ድንጋዮች ነው። በ1ጴጥ. 2፥4-5 እንዲህ ይላል። «በሰውም ወደ ተጣለ በእግዚአብሔር ግን ወደ ተመረጠ ና ክቡር ወደ ሆነው ወደ ሕያው ድንጋይ ወደ እርሱ ወደ ክርስቶስ እየቀረባችሁ፣ እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መስዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ።» በኃዳችን ሳንሠራ (ሳንጠረብ) ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ስንመጣ ብዙ ጊዜ ጠ ֽናማ ያልሆነ ድምፅ (ማጉረምረምና ሁካታ) የምናሰማው እኛ እንሆናለን።

በቁ. 11 እና 12 ላይ፣ እግዚአብሔር ሰሎሞንን፣ ቤተ መቅደሱን መሥራት ብቻ ሳይሆን፣ በሥርዓቱ መሄድና ትእዛዙን መጠበቅም እንዳለበት ያሳስበዋል። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ሥራ ስለ ሠራንና አገልግሎት ስላገለገልን ብቻ ከቅድስናና እግዚአብሔርን ከመፍራት ሕይወት ነጻ የሚያደርገን ይመስለናል። እግዚአብሔር ግን፤ ቤተ መቅደሱን ከመሥራታችንም በላይ የሚጠብቅብን፣ የግል ሕይወታችንን ከእርሱ ጋር በትህትናና እግዚአብሔርን በመፍራት እንድናራምድ ነው (ሚክ 6፥8)

ከቁ 20-36 ድረስ በአጠቃላይ ስለ ቅድስተ ቅዱሳኑ አሠራር ሲናገር፤ ቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ የነበሩት ነገሮች ሁሉ፣ ቤቱና ወለሉ እንኳን ሳይቀር በወርቅ የተለበጠ እንደነበረ ይገልጻል። በእነዚህ 16 ጥቅሶች ውስጥ 9 ጊዜ «በወርቅ ለበጠ» የሚሉ ቃላት ሰፍረዋል። «ቤቱንም ሁሉ ፈጽሞ በወርቅ ለበጠው» (ቁ. 22) «የቤቱንም ወለል በውስጥና በውጭ በወርቅ ለበጠ» (ቁ. 30)

ይህ ሁኔታ በጣም የሚያስደንቅ ነው። ምክንያቱም ቅድስተ ቅዱሳኑ የእግዚአብሔር የክብር ብርሃን በኪዳኑ ታቦት ላይ ባለው የሥርየት መክደኛ ላይ የሚያርፍበት ስፍራ ስለሆነ የፀሐይም ብርሃን ሆነ ማንኛውም ሰው ሠራሽ የሆነ ብርሃን የማይገባበት፣ የእግዚአብሔር የክብር ብርሃን ብቻ የሚታይበት ስፍራ ነው። ቅድስተ ቅዱሳኑ እና በውስጡ የነበሩት ዕቃዎች ሁሉ በወርቅ መለበጣቸውን ከዚህ ሁኔታ ጋር ስናያይዘው ያ ስፍራ ምን ያህል የእግዚአብሔር ክብር ብርሃን የሚንጸባረቅበት እንደሆነ መገመት እንችላለን። ያ ሁሉ ወርቅ የእግዚአብሔር ክብር ብርሃን ለማንጸባረቅ የተደረገ ነበር። ይህ የቅድስተ ቅዱሳኑ ሥዕላዊ መግለጫ፣ በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያና ቤተ መቅደስ የተባልነው አማኞች ሁሉ ምን ያህል ሕይወታችን (በወርቅ የማይዝግ፣ በእሳት ተፈትኖ የሚያልፍና የእግዚአብሔርን ክብር የሚያንጸባርቅ) መሠራት እንዳለበት ያሳስበናል 1ቆሮ. 6፥19-20፤ 2ቆሮ. 6፥16፤ 1ቆሮ. 3፥12-15 ሕይወታችን እንደ ቅድስተ ቅዱሳኑ በወርቅ የተለበጠ ከሆነ የእግዚአብሔርን ክብር የምናንጸባርቅ እንሆናለን። «እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደመስታወት እያብለጨለጭን (እያንጸባረቅን) መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን» 2ቆሮ. 3፥18።

ምዕ. 7 ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን በ7 ዓመታት ከጨረሰ በኋላ የራሱን ቤተ መንግሥትና መኖሪያ ቤት በ13 ዓመታት እንደሠራ፤ እንዲሁም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሚያስፈልጉትን ዕቃዎች በሙሉ ኪራም በሚባል የጢሮስ ሰው በኩል እንደሠራ፤ የሚገልጽ ምዕራፍ ነው፡

ይህ ቤት ወይም ቤተ መንግሥት የተለያዩ ቤቶችን የያዘ እንደነበረ ከቁ. 1-8 እናነባለን። ምናልባት በአንድ ቅጥር ውስጥ ያሉና የተያያዙ ቤቶች ሳይሆኑ አይቀርም። እነዚህ በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ቤቶች የሚከተሉት ናቸው። የሊባኖስ ዱር ቤት (ቁ 2) አዕማዱ ያሉበት ቤት (ቁ.6) የሚፈርድበት ዙፋን ያለበት የፍርድ ቤት ቁ. 7 የራሱ መኖሪያ ቤት ቁ 8 እንዲሁም ላገባት ለፈርዖን ልጅ መኖሪያ ቤት (ቁ 8)።

ከቁ. 13-51 ድረስ፣ ንጉሡ ሰሎሞን ኪራም የሚባል ከጢሮስ አገር የሆነ፣ እናቱ ከንፍታሌም ወገን የነበረች፣ በናስ ሥራ ጥበብና ብልሃት የተሞላ ሰው አስመጥቶ እንዴት በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የነበሩትን የናስ ሥራዎች በሙሉ እንዳሠራ ይናገራል። ይህ ሰው በምዕ 5፥1 ላይ ካለው ከንጉሥ ኪራም የተለየ ነው። ከዚህ ክፍል የምናስተውለው፤ ምንም እንኳን ኪራም የሚባለው ሰው ግማሽ አሕዛብ ቢሆንም ለሰው ልጆች ጥበብና ማስተዋል የሰጠ እግዚአብሔር ስለሆነ፣ ይህንን እግዚአብሔር የሰጠውን ጥበብና ማስተዋል ለእግዚአብሔር ክብር ሲጠቀምበት እናያለን። እግዚአብሔር በዘመናት ውስጥ አሕዛብ የተባሉትን ሰዎች፤ ለምሳሌ፤ በምዕ. 5፥1 ላይ ያለውን የጢሮስን ንጉሥ ኪራምን፣ በመጽሐፈ ነህምያ ያለውን ንጉሥ አርጠ ሕስስን፣ በተለይ ደግሞ ከኢሳ. 44፥28-45፡56 የተጠቀሰው የአሕዛብ ንጉሥ ቂሮስን፣ እንዲሁም ናቡከደነፆርን እንዴት እንደተጠቀመባቸው ማየት እንችላለን። እኛም፣ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለቤቱና ለመንግሥቱ ሥራ አሕዛብንም እንኳን ሊጠቀም እንደሚችል አውቀን፣ እግዚአብሔር ለእነዚህ አሕዛብ የሰጣቸውን ስጦታ መጠቀም የሚኖርብን ጊዜ አለ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ግን፤ አንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ሰው እነዚህ ሰዎች የሚሠሩትን ነገር ከበላይ ሆኖ መቆጣጠር አለበት።

«ንጉሡም ሰሎሞን ልኮ ኪራምን ከጢሮስ አስመጣ። እርሱም ከንፍታሌም ወገን የነበረች የባል አልባ ሴት ልጅ ነበረ፣ አባቱም የጢሮስ ሰው ናስ ሠራተኛ ነበረ፤ የናስንም ሥራ ሁሉ ይሠራ ዘንድ በጥበብና በማስተዋል በብልሃትም ተሞልቶ ነበር። ወደ ንጉሡ ወደ ሰሎሞን መጥቶ ሥራውን ሁሉ ሠራ» ቁ. 13-14።

ምዕ. 8 የቃል ኪዳኑ ታቦት ከዳዊት ከተማ ከጽዮን ቤተ መቅደሱ ወዳለበት ወደ ኢየሩሳሌም እንደመጣና በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ እንደገባ፣ የእግዚአብሔር ክብር ቤተ መቅደሱን ሞልቶ

ስለነበረ ካህናቱ ቆመው ማገልገል እንዳልቻሉ፣ እንዲሁም ሰሎሞን በሕዝቡ ፊት፣ ተንበርክኮና እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ ድንቅ የሆነ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር እንዳቀረበና ታላቅ የበሬዎችና የበጎች መሥዋዕት በቤተ መቅደሱ እንዳቀረቡ የሚተርክ ረዥም ምዕራፍ ነው።

ከቁ 1-9 የምንመለከተው የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ከዳዊት ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣቱንና በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ በስፍራው መቀመጡን ሲሆን፤ በቁ. 10-11 ላይ የእግዚአብሔር የክብር ደመና የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶ ስለነበረ ካህናቱ ቆመው ማገልገል እንዳልቻሉ እናነባለን። በዘጸአት 40፥34-35 ላይም እንደዚሁ ተመሳሳይ ሁኔታ እናያለን። ሙሴ የመገናኛውን ድንኳን ሁሉ ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ «ደመናውም የመገናኛውን ድንኳን ከደነ፣ የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላ። ደመናውም በላዩ ስለነበረ የእግዚአብሔር ክብር ማደሪያውን ስለሞላ ሙሴ ወደ መገናኛው ድንኳን ይገባ ዘንድ አልቻለም» (ዘጸ 40፥34-35)። ሰሎሞንም ቤተ መቅደሱን ጨርሶ የኪዳኑ ታቦት በቅድስተ ቅዱሳኑ ከገባ በኋላ «ደመናው የእግዚአብሔርን ቤት ሞላው። የእግዚአብሔርም ክብር ቤተ መቅደሱን (የእግዚአብሔርን ቤት) ሞልቶ ነበርና ካህናቱ ከደመናው የተነሣ ለማገልገል ይቆሙ ዘንድ አልቻሉም» 1ነገ 8፥10-11። ከእነዚህ ክፍሎች የምንማረው፤ የእግዚአብሔርን ሥራ እግዚአብሔር እንዳዘዘን በፍጹም ልብ፣ በፍጹም ነፍስ፣ በፍጹም ኃይል ካከናወንን የእግዚአብሔር ክብር ከተገለጠ ደግሞ ማንም አገልጋይ የሚታይበት መድረክ ሳይሆን እግዚአብሔር ብቻ የሚከብርበትና የሚታይበት ይሆናል። የአገልግሎት ሁሉ ግብ የእግዚአብሔር ክብር እንዲገለጥ ስለሆነ የእግዚአብሔር ክብር ከተገለጠ በኋላ እግዚአብሔርን በአክብሮትና በስግደት በፊቱ ወድቀን ማምለክና ማመስገን እንጂ አገልግሎት በዚያን ጊዜ ቦታ አይኖረውም።

በቁ9 ላይ የቃል ኪዳኑ ታቦት በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ በገባ ጊዜ «ሙሴ በኮሬብ ካስቀመጣቸው ከሁለቱ ድንጋዮች በቀር ምንም አልነበረበትም።» ይላል። ይህንን ጥቅስ ከዕብ 9፥4 ጋር ስናስተያየው እርስ በርስ የሚቃረን ይመስላል፤ ነገር ግን በዕብ 9፥4 ላይ ከኪዳኑ ጽላት ሌላ የበቀለች የአሮን በትርና መና ያለባት የወርቅ ማዕጠንት ወይም መሶብ እንደነበሩ የሚናገረው፤ በሙሴና በአሮን ዘመን እግዚአብሔር ለልዩ ዓላማ፣ ለተወሰነ ዘመንና ትውልድ ምስክርና ማስጠንቀቂያ ይሆኑ ዘንድ በታቦቱ ውስጥ እንዲቀመጡ ያዘዛቸውን ሁለት ተጨማሪ ነገሮች ከታሪክ አንጻር በአንድ ወቅት እንደነበሩ ሲተርክ ነው እንጂ ላልተወሰነ ጊዜ ከድንጋዩ ጽላት ጋር ተጠብቀው የሚቀመጡ ነገሮች እንደነበሩ መጠቆሙ አይደለም። እነዚህ ሁለት ተጨማሪ ነገሮች፤ ማለትም፣ የአሮን በትርና የወርቅ ማዕጠንት፤ መቼ ከታቦቱ እንደወጡ የሚገልጽ ማስረጃ የለም። ምናልባት፣ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ወጥተው ይሆናል ወይም በዔሊ ዘመን ታቦቱ በፍልስጥኤማውያን ተማርካ በነበረችበት ጊዜ ተወስደው ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ጉዳይ የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ የሚነግረን ነገር ስለሌለ በዚህ ምክንያት ነው ማለት አይቻልም። የኪዳኑ ጽላት ግን፣ የእግዚአብሔርን ሕያውና ዘላለማዊ ቃል ያዘለ ስለነበረ በታቦቱ ውስጥ ጸንቶ እናየዋለን። እግዚአብሔር በዘመናት ውስጥ ለተወሰኑ ወቅቶች ለምክርና ለማስጠንቀቂያ ብሎ እንደ አሮን በትርና እንደ ወርቁ ማዕጠንት በልባችን የሚያስቀምጣቸው ነገሮች፤ አሉ፤ እነዚህ ነገሮች በሕይወታችን ዓላማቸውን ከፈጸሙ በኋላ አውጥተን ልንጥላቸው እንችላለን። «ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር፣ እንደ ልጅም አስብ ነበር፣ እንደ ልጅም እቆጥር ነበር፤ ጎልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ» (1ቆሮ. 13፥11)። ነገር ግን ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ቃል ከልባችን ታቦት አውጥተን ልንጥለው አንችልም። ቃሉ ዘወትር በልባችን ጽላት ላይ ተጽፎ መኖር አለበት። በዚህ ክፍል እግረመንገዳችንን መጥቀስ የምንፈልገው፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የእንጨት ታቦትና የድንጋይ ጽላት የማያስፈልግበት ምክንያት ታቦቱም ሆነ ጽላቱም የአማኞች ሕይወትና ልብ ስለሆነ ነው። እነዚህን ጥቅሶች ተመልከት፡- 2ቆሮ. 3፥3፤ 3፥6-9፤ ዕብ. 6፥10፤ 1ቆሮ. 6፥19-20፤ 2ቆሮ. 6፥16።

በቁ. 12-21 ሰሎሞን የእስራኤልን ጉባኤ ይመርቅና ከቁ. 22-53 ድረስ ያለውን ድንቅ የሆነ ጸሎት ከማድረጉ በፊት ለሕዝቡ መንደርደሪያ የሚሆን መግለጫ ይሰጣል። በቁ. 13 ላይ «... እኔም ለዘላለም የምትኖርበት ማደሪያ ቤት በእውነት ሠራሁልህ» ብሎ ለእግዚአብሔር ይናገራል። ይህንን ቃል ከሰሎሞን የመጨረሻ ሕይወት ጋር ስናወዳድረው፤ ለእግዚአብሔር ማደሪያ የሚሆን ቤተ መቅደስ አሠራ ነገር ግን የራሱን ሕይወት ለእግዚአብሔር ማደሪያ አድርጎ ሙሉ ለሙሉ አልሰጠም። እግዚአብሔር ከምንሠራለት ውጫዊ አገልግሎትና መቅደስ ይልቅ ሕይወታችንን የእርሱ ማደሪያ አድርገን እንድንሰጠው ይፈልጋል። ዳዊት ለእግዚአብሔር መቅደስ አልሠራም ነገር ግን «እንደ ልቤ የሆነ፣ ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ» ብሎ የመሠከረለት ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሰው ነበር።

ከቁ. 22-53 ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ያቀረበውን ድንቅ የሆነ ጸሎት እናነባለን። «የእስራኤልም ጉባኤ ሁሉ እያዩ ሰሎሞን በእግዚአብሔር መሠዊያ ፊት ቆሞ እጆቹን ወደ ሰማይ ዘረጋ። እንዲህም አለ:-» በማለት ጸሎቱን እንዴት እንደ ጀመረ ይነግረናል። ከቁ. 54 እንደምንረዳው ይህንን ጸሎት ሲያደርግ «በጉልበቱ ተንበርክኮ፣ እጁንም ወደ ሰማይ ዘርግቶ» ነበር። በዚህ ምዕራፍ ሰሎሞንና እስራኤላውያን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በጎችና በሬዎች እንደሰው በቁ. 5 እና 63 ላይ ይናገራል። ከቁ. 22-53 ያለውን፣ ሰሎሞን ተንበርክኮና እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ የጸለየውን ጸሎት ስናይ ግን ለእግዚአብሔር ከእነዚያ «ከብዛታቸው የተነሳ የማይቆጠሩትንና የማይመጠኑትን በጎችና በሬዎች» ቁ. 5 ካቀረቡት መሥዋዕት ይልቅ ደስ የሚያሰኝ መስዋዕት ሳይሆን አይቀርም። ምክንያቱም፤ የሰቡትን በጎችና በሬዎች ለመስዋዕት ማቅረብ ከሆነ ሳያልም ቢሆን ሊያደርግ የወደደው ነገር ነበር። ሰሎሞን ግን ራሱን በእግዚአብሔር ፊት አንበርክኮና ልቡን ከእጆቹ ጋር አንስቶ ለእግዚአብሔር ሕያው መስዋዕት የሆነውን ራሱን ነው ያቀረበው። (በመዝ 49(50)7-14) እግዚአብሔር ከሚቃጠል የእንስሳት መስዋዕት ይልቅ ከግል ሕይወታችን የሚመነጭ የምስጋናን መስዋዕት እንደሚሻ ይናገራል። እኛም በአዲስ ኪዳን የታዘዝነው «ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ» በሚል አምላካዊ ቃል ነው» ሮሜ 12÷1።

የሰሎሞንን ጸሎት በአጠቃላይ በምንመለከትበት ጊዜ አምልኮን፣ ልመናንና ምልጃን ያጠቃለለ ጸሎት ነበር። በመጀመሪያ የእስራኤል አምላክ ከሁሉም በላይ የሆነ፣ እርሱን የሚመስለው በላይ በሰማይም ሆነ በታች በምድር ማንም እንደሌለ በመናገር በአምልኮና በአክብሮት ቃል ይጀምራል። ቀጥሎም እግዚአብሔር ቃል ኪዳንን የሚጠብቅ የምሕረት አምላክ እንደሆነ ይናገራል። ከዚያም እግዚአብሔር ለዳዊት እና ለዘሩ የገባለትን ቃል ኪዳን በመጥቀስ ቃል ኪዳኑን ለዳዊትና ለዘሩ እንዲጠብቅ ይጸልያል። ይህንን የመግቢያ ጸሎት ካደረገ በኋላ፤ ለእግዚአብሔር ስለ ሠራው ቤተ መቅደስ ከመጸለዩ በፊት፤ በቁ. 27 ላይ «በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን»? በማለት የሚያስገርም ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ የሚያስገርም የሚሆንበት ምክንያት፣ ከሰው አንጻር ሲታይ እግዚአብሔር ታላቅና ወሰን የሌለው ስለሆነ እንዴት ውስን ከሆኑና ከእግዚአብሔር ጋር ሲተያዩ ኢምንት ከሆኑ ሰዎች ጋራ በምድር ላይ ራሱን ወስኖ ይኖራል? የሚል ስሜትን ያዘለ ጥያቄ ነው። ሰሎሞንም የጠየቀው በዚህ መንፈስ ነው። ይህንን ጥያቄ ከእግዚአብሔር አንጻር ስናየው ግን እግዚአብሔር ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ «አዎን በምድር ላይ ከሰው ጋር መኖር እወዳለሁ» የሚል ይሆናል። ይህንን ያልንበት ምክንያት፣ የእግዚአብሔርን ቃል ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራዕይ ድረስ ስንመለከት፤

ከመጀመሪያው ጀምሮ አዳምና ሔዋን «ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን (የአምላክን) ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ» በማለት በገነት ከአዳምና ከሔዋን ጋር እግዚአብሔር ይመላለስ እንደነበረ እንመለከታለን። በተጨማሪም በዘጸአት 25÷8 ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ ስለ መገናኛው ድንኳን መሠራት፤ «<u>በመካከላቸው አድር ዘንድ</u> መቅደስን ይሥሩልኝ» ብሎ

ሲናገረው እናነባለን። በመጨረሻም በራእ. 21፥3 ላይ የነገር ሁሉ ፍጻሜ ሆኖ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ከመጡ በኋላ «ታላቅ ድምፅም ከሰማይ፦ እነሆ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው። ከእነርሱም ጋር ያድራል፣ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፣ እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል።» የሚል የእግዚአብሔርን የመጨረሻ ዓላማ የሚገልጽ ትንቢታዊ ቃል አለ።

ከቁ. 31-53 ሰሎሞን ጸሎቱን በመቀጠል እስራኤላዊያን በተለያዩ ሁኔታዎች በሚያልፉበትና በሚበድሉበት ጊዜ፤ ተመልሰው በዚህ ቤት ውስጥ በንስሐ ቢጸልዩ እግዚአብሔር ምሕረትን እንዲያደርግላቸው የምልጃ ጸሎት ያቀርባል። «ሰው ባልንጀራውን ቢበድል እርሱም መጥቶ በዚህ ቤት በመሠዊያህ ፊት ቢምል፣ በሰማይ ስማ፣ አድርግም፤ በባሪዎችህም ላይ ዳኛ ሁን፣ በበደለኛውም ላይ ፍረድ፤ ...» (ቁ. 31-32)

«አንተን ስለ በደሉ በጠላቶቻቸው ፊት ድል በተመቱ ጊዜ ወደ አንተ ቢመለሱ... በዚህም ቤት ቢጸልዩና ቢለምኑህ ... ቁ. 33
«አንተን ስለ በደሉ ሰማይ በተዘረጋ ጊዜ... (ቁ. 35) «በምድር ላይ ራብ፣ ወይም ቸነፈር፣ ወይም ዋግ...
ወይም አንበጣ፣ ወይም ኩብኩባ ቢሆን፣ የሕዝብም ጠላት የአገሩን ቀበሌዎች ከብቦ ቢያስጨንቃቸው ... (ቁ. 37)
«ማናቸውም ሰው የልቡን ሕመም አውቆ ጸሎትና ልመና ቢጸልይ፣ እጆቹንም ወደዚህ ቤት ቢዘረጋ... በማደሪያህ ስማ፣ ይቅርም በል ...» ቁ. 38-40

በቁ 38 ኃጢአትና በደልን ሁሉ «የልብ ሕመም» ይለዋል።

ከቁ. 41-42 ለእስራኤላውያን ብቻ ሳይሆን «ከሕዝብህም ከእስራኤል ወገን ያልሆነ እንግዳ ታላቁን ስምህን፣ ብርቱይቱንም እጅህን፣ የተዘረጋውንም ክንድህን ሰምቶ ስለ ስምህ ከሩቅ አገር በመጣ ጊዜ አንተ በማደሪያህ ስማ» በማለት ለአሕዛብ ሁሉ የሚሆን ጸሎትና ምልጃ ያደርጋል። በሐዋ. 8፥26-40 የምናገኘው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የዚህ ጸሎት ተጠቃሚ በመሆን እግዚአብሔር በፊልጶስ በኩል ሲገናኘው እናያለን። የሰሎሞን ጸሎት በጊዜያዊና በወቅታዊ ወይም በአንድ ወገን (በእስራኤላውያን) ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ እቅድ ያዘለ ጸሎት ነበረ። በቁ. 43 ላይ በመቀጠል እንደዚህ ብሎ ይጸልያል። «የምድርም አሕዛብ ሁሉ ስምህን ያውቁ ዘንድ እንደ ሕዝብህም እንደ እስራኤል ይፈሩህ ዘንድ፣» በማለት እግዚአብሔር ለአብርሃም ከመጀመሪያው ከገባለት ቃል ኪዳን ጋር አብሮ የሚሄድና የሚስማማ ጸሎትን ያደርጋል። «እግዚአብሔርም አብራምን አለው፦ ... እባርክሃለሁ የምድርም ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።» ዘፍ 12፥1-3።

በመጨረሻም፤ ሰሎሞን፣ እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ለመውጋት ሲወጡ ከእነርሱ ጋር እንዲሆን፤ በድለውም በጠላቶቻቸው ቢማረኩና በምርኮ ምድር ሆነው ወደዚህ ቤተ መቅደስ ፊታቸውን አቅንተው ቢጸልዩ «በደላቸውን ሁሉ ይቅር በል ይራሩላቸውም ዘንድ በማረኩአቸው ፊት ምሕረት ስጣቸው» ብሎ ይማልዳል። ይህንን ሁሉ ከጸለየ በኋላ «ከግብጽ ምድር ከብረት እቶን ውስጥ ያወጣሃቸው ሕዝብህና ርስትህ ናቸውና» በማለት የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔር ርስት እንደሆነ ያስረዳል። እኛም በአዲስ ኪዳን ያለን አማኞች ክርስቶስ በደሙ የዋጀን ገንዘቡና ርስቶቹ ነን። «በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ» 1ቆሮ. 6፥20።

ምዕ. 9 እግዚአብሔር በሰሎሞን ለሁለተኛ ጊዜ ይገለጥለትና ጸሎቱን እንደሰማ ይነግረዋል። እንዲሁም እንደ አባቱ እንደ ዳዊት በፊቱ በቅንነት እንዲሄድና ትእዛዙን ሁሉ እንዲጠብቅ ያስጠነቅቀዋል። ይህንን ትእዛዝ እርሱም ሆነ እስራኤላውያን ካልጠበቁ «እስራኤልን ከሰጠ

ኋቸው ምድር አጠፋቸዋለሁ፤ ለስሜም የቀድስኩሁትን ይህን ቤት ከፊቴ እጥለዋለሁ፤ እስራኤልም በአሕዛብ ሁሉ መካከል ምሳሌና ተረት ይሆናሉ» ቁ. 7 በማለት የሚጠብቃቸውን ቅጣት ያሳስበዋል።

በቁ. 21 ላይ እስራኤላውያን ሊያጠፏቸው ያልቻሉትን አሕዛብ ሰሎሞን ገባሮች አድርጎ እንደመለመላቸውና በእስራኤል መንግሥት ውስጥ እንደ ባሪያዎች ሆነው ይሠሩ የነበሩት እነርሱ እንደነበሩ ይገልጻል። «ሰሎሞን ከእስራኤል ልጆች ማንንም ባሪያ አላደረገም» ቁ. 22። ከዚህ ቃል የምናስተውለው፤ አንዳንድ ጊዜ ጠላት እንቢ ብሎ የቀረ በሚመስለን ጊዜ እንኳን እግዚአብሔር ለእኛ ባሪያ ሊያደርገው አስቦ ይሆናልና መደናገጥ የለብንም።

ምዕ. 10 የንግሥተ ሳባን ወደ ሰሎሞን መምጣትና የሰሎሞን ዝናና ብልጽግና ምን ያህል እንደነበረ ይገልጻል። ከቁ. 1-13 ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ዝና ሰምታ ልትፈትነው እንደመጣችና ካሰበችውና ከሰማችው በላይ ሆኖ እንዳገኘችው፣ እንዲሁም ለንጉሥ ሰሎሞን የሰጠችውን ገጸ በረከትና ከንጉሥ ሰሎሞን ደግሞ የተቀበለችውን ስጦታ ይገልጻል። በዚህ ክፍል ውስጥ፣ በቁ. 1 ላይ «የሳባም ንግሥት በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ እንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች» ይላል። የሰሎሞን ዝና ወጣ የሚለው «በእግዚአብሔር ስም» ነው። ዝናችን በራሳችን ስም ሳይሆን በእግዚአብሔር ስም ሲወጣ ክብሩ ለእግዚአብሔር እንጂ በእኛ ላይ አያተኩርም። ሰዎች ስለ እኛ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ እንጂ እኛን አያመሰግኑም። በቁ 9 ላይ ንግሥተ ሳባ ሁሉን ካየችና ከሰማች በኋላ፤ «አንተን የወደደ፣ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን» በማለት እግዚአብሔርን ታከብራለች፡ ፡

በቁ 1 ላይ ሌላ የምናየው ቃል «በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች» ይላል። ኢየሱስ በሉቃስ 11፥31 ውስጥ ስለ ንግሥተ ሳባ (አዜብ) እንዲህ አለ፤ «ንግሥተ አዜብ በፍርድ ከዚህ ትውልድ ሰዎች ጋር ተነሥታ ትፈርድባቸዋለች፣ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና፣ እነሆም፣ ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ።» ይህንን ቃል የተናገረው፣ የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ፊት ለፊት አይተውና ሰምተው ማመንና መቀበል ላቃታቸው አይሁዳውያን ነበረ። ንግሥተ አዜብ ግን ከሩቅ በሰማችው ዝና አማካይነት ተነስታ ለማረጋገጥ ወደ ሰሎሞን መጣች። ያመጣችውንም የእንቆቅልሽ ፈተና ሁሉ ፈታላት። ከሰሎሞን የሚበልጠው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላቸው ተአምራት እያደረገና ጥበብ የተሞላውን ትምህርት እያስተማረ እንኳን ሊቀበሉት አልቻሉም። በፍርድ ቀን የሚፈረድብን በተገለጸልን ብርሃንና ባገኘው ዕድል መጠን ነው።

ንግሥተ ሳባ የምትደነቅበት አንዱ ምክንያት፤ የሰማችውን ዝና ዝም ብላ አልተቀበለችም ወይም ቸል አላለችም፤ ነገር ግን እውነተኛነቱን ለማመረጋገጥ የሰማችውን ነገር በግል ፈተነችው። የእግዚአብሔር ቃል «ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ ይለናል። በተጨማሪም «መንፈስን ሁሉ አትመኑ፣ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ» 1ዮሐ 4፥1 ይለናል።

በቁ. 3 ላይ «ሰሎሞንም የጠየቀችውን ሁሉ ፈታላት ሊፈታላት ያልቻለውና ከንጉሡ የተሰወረ ነገር አልነበረም።» ይላል። ፍጡርና ውስን የሆነው ሰሎሞን እግዚአብሔር በሰጠው ጥበብ የጠየቀችውን ሁሉ ሊፈታላት ከቻለ፣ «ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ» የተባለለት ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት አብልጦ የችግራችንንና የእንቆቅልሻችንን ቋጠሮ አይፈታም?

ከቁ 13-29 ድረስ የምናየው የሰሎሞንን ብልጽግና ነው። «ንጉሡም የሚጠጣበት ዕቃ ሁሉ ወርቅ ነበረ በሰሎሞንም ዘመን ብር ከቶ አይቆጠርም ነበር።» ይህ ሁሉ ብልጽግናና ክብር

የሆነለት እግዚአብሔር በሰጠው ጥበብ አማካይነት ነበረ። «ንጉሡም ሰሎሞን በባለጠግነትና በጥበብ ከምድር ነገሥታት ሁሉ በልጦ ነበር። ምድርም ሁሉ እግዚአብሔር በልቡ ያኖረለትን ጥበቡን ይሰማ ዘንድ የሰሎሞንን ፊት ይመኝ ነበር» ቁ. 23-24። ከዚህ ቃል የምናስተውለው፣ እግዚአብሔር በሚሰጠን ግርማ፣ ሞገስ፣ ጥበብ፣ ጸጋ፣ ኃይል ወዘተ ... አማካይነት የሰዎች ዓይን ወደ እኛ ሊያተኩር ይችላል፤ ነገር ግን ክብሩን ሁሉ አሳልፈን ክብር ሁሉ ለሚገባው ለአምላካችን መስጠት ይገባናል። እግዚአብሔር በሰጠን ነገር የሰዎች ዓይን በእኛ ላይ ሲሆን ክብሩን ለራሳችን ከወሰድን ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን ክብር ሰርቀናል ማለት ነው። ሌባ ደግሞ የሚጠብቀው ቅጣትና ውርደት ነው። የተባልነው፤ «የሚገባችሁን ሁሉ ካደረጋችሁ በኋላ እኛ የማንጠቅም ባሪያዎች የሚገባንን አድርገናል በሉ» ነው።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፣ ስለ ንግሥት ሳባ ካነሳን ዘንድ፣ ሳንጠቅስ ማለፍ የማንፈልገው ነገር አለ። ምንም እንኳን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ባይጻፍም በአገራችን ታሪክ ውስጥ ጎልቶ የሚታይ ነገር ስለሆነ በአጭሩ መመልከቱ መልካም ነው። በአገራችን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እንደምንሰማው፣ ንግሥተ ሳባ ወይም ንግሥተ አዜብ የኢትዮጵያ ንግሥት እንደነበረችና (ምናልባት ግዛቷ በኢትዮጵያ ብቻ የተወሰነ ላይሆን ይችላል) ወደ ንጉሥ ሰሎሞን በሄደችበት ጊዜ ከሰሎሞን ቀዳማዊ ምኒሊክን ፀንሳ እንዳመጣች ይነገራል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነገረው ሌላ አፈ-ታሪክ፤ ቀዳማዊ ምኒልክ 20 ዓመት ሲሆነው ወደ አባቱ ወደ ሰሎሞን ተመልሶ ሦስት ዓመት በኢየሩሳሌም ከአባቱ ጋር ከኖረ በኋላ ታቦቱን ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ ይዞ እንደመጣ ነው። ይህንን አፈ-ታሪክ ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ስንመዝነው እውነተኛነቱ አስተማማኝ አይደለም። አስተማማኝ የማያደርጉትም ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው። 1ኛ የንጉሥ ሰሎሞንን 40 ዓመት ንግሥ በምንመለከትበት ጊዜ፤

ሀ. በነገሠ በ4ተኛው ዓመት በ2ተኛው ወር የመቅደሱን ሥራ ጀመረ 1ነገ 6÷1

ለ. ቤተ መቅደሱንና የራሱን ቤቶች (ቤተ መንግሥቱንና መኖሪያውን) በሃያ ዓመታት ውስጥ ፈጸመ 1ነገ 9÷10

ሐ. ከዚያ በኋላም የዘመኑ ቁጥር ባይጠቀስም ንግሥተ ሳባ ከመምጣትዋ በፊት ልዩ ልዩ ሥራዎችን ሠርቷል 1ነገ 9÷15፤ 19፤24

በተራ ቁ. «ሐ» የተዘረዘሩት ሥራዎች የፈጁትን ዘመን ባናውቅም በ«ሀ» እና «ለ» ሥራ ያሉት ዘመናት ድምር ብቻ 24 ዓመታት ከ2ወር ነው። በዚህ ላይ ንግሥተ አዜብ ወደ ሰሎሞን መጥታ ከእርሱ ፀንሳ ምኒሊክ እስከሚወለድ ቢያንስ የ9 ወራት ዕድሜ ተጨመረ ማለት ነው። ስለዚህ በተራ ቁ «ሐ» ያለውን ዘመን ሳንጨምር ምኒልክ እስከሚወለድ ድረስ የሰሎሞን መንግሥት 25ኛውን (24 ዓመት ከ11 ወር) ዓመት ይዞ ነበር ማለት ነው። በዚህ ላይ ምኒሊክ በ20 ዓመቱ ወደ አባቱ ተመልሶ መጣ የተባለውን ዘመን ስንጨምርበት 45 ዓመታት ይሆናል። ይህም ማለት የሰሎሞን መንግሥት አክትሞ 5 ዓመታት አልፈዋል ማለት ነው።

2ኛ መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ዜና መዋዕል 35÷3 ላይ በንጉሡ በኢዮስያስ ዘመን እንኳን ታቦቱ እንደነበረ ይናገራል። «እስራኤልንም ሁሉ ያስተምሩ ለነበሩት ለእግዚአብሔርም ለተቀደሱት ሌዋውያን እንዲህ አለ፦ <u>ቅዱሱን ታቦት</u> የእስራኤል ንጉሥ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን በሠራው ቤት ውስጥ አኑሩት ከዚህም በኋላ በትከሻችሁ ላይ ሸክም አይሁንባችሁም።» ይላቸዋል ይህንን ታቦት «ቅዱሱን ታቦት» ነው የሚለው፤ አፈ-ታሪኩ እንደሚለው ቀዳማዊ ምኒሊክ «ቅዱሱን ታቦት» ወስዶ በፋንታው ሌላ እርሱን የሚመስል ተተክቶ ቢሆን ኖሮ የእግዚአብሔር ቃል «ቅዱሱን ታቦት» አይልም ነበር።

ከላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች እንደምንረዳው «ቅዱሱ ታቦት» በቀዳማዊ ምኒሊክ አማካይነት ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል የሚለው ታሪክ የእግዚአብሔር ቃል ፈተና የሚያልፍ ታሪክ አይደለም።

ምዕራፍ 11፡- የንጉሥ ሰሎሞን ውድቀትና የመንግሥቱ ፍጻሜ የንጉሡ ሰሎሞን ውድቀት በገሃድ የሚታየው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ነው። የዚህም ውድቀት ዋናው መንሥኤ፤ ብዙ «እንግዳ ሴቶች» በማፍቀሩና በእነርሱም ጣዖታት ልቡ በመወሰዱ ነበር። «ንጉሡም ሰሎሞን ከፈርዖን ልጅ ሌላ በሞዓብአውያን፣ በአሞናውያን በኤዶማውያንም፣ በሲዶናውያንና በኬጢያውያን ሴቶች በብዙ እንግዶች ሴቶች ፍቅር ተነደፈ።» 1ነገ. 11÷1 «እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች፡- አምላኮቻቸውን ትከተሉ ዘንድ ልባችሁን በእውነት ያዘነብላሉና ወደ እነርሱ አትግቡ፣ እነርሱም ወደ እናንተ አይግቡ ካላቸው ከአሕዛብ፣ ከእነዚህ ጋር ሰሎሞን በፍቅር ተጣበቀ።» 1ነገ 11÷2፤ ዘጸ 7÷7÷3-4፤ ዘጸ. 34÷16 «ሰሎሞንም ሲሸመግል ሚስቶቹ ሌሎችን አማልክት ይከተል ዘንድ ልቡን አዘነበሉት።» 1ነገ 11÷4። «ሲሸመግል» የሚለው ቃል፤ «ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው» እንደሚባለው ቀስ በቀስ ልቡ እንደተወሰደ ያመለክታል። ለጥቂት ዘመናት ሳያንገራግር አልቀረም፤ በኋላ ግን ልቡ ተወሰደ። ከኃጢአት ጋር መደራደርና መጫወት ለሳምሶንም አልበጀውም። ምንም ጊዜ ቢፈጅ፣ ውሃ ቀስ በቀስ ሸርሽሮ ድንጋይን እንደሚቦረቡር፣ ልባችን በዚያ ኃጢአት መቦርቦሩ አይቀሬ ነው። «ሸክምን ሁሉ፣ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን ...» (ዕብ 12÷1) የሚለው፣ ከኃጢአት ጋር እንዳንጫወትና እንዳንያዝ ሲመክረን ነው። ሰሎሞን፤ የከበበውን ኃጢአት ቶሎ ከማስወገድ ይልቅ፣ በዚያ ኃጢአት ተነደፈ። ኃጢአትን ቶሎ፣ ሥር ሳይሰድ ካላስወገድነው እንደ መርዛም እባብ ይነድፈናል። የኃጢአትም መጨረሻው ሞት የዘላለም ሞት ነው።

የሰሎሞን ውድቀት በምዕራፍ 11 ተገለጸ እንጂ ውድቀቱ ወይም መሳት የጀመረው በምዕራፍ 10 ነው። በዘጸ 17÷14-17 ያለውን፤ እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን ስለሚያነግሡት ንጉሥ የሰጣቸውን መመሪያና ትእዛዝ በሙሉ በዚህ ክፍል፤ እግዚአብሔር ንጉሡ ማድረግ የለበትም ያላቸውን ሦስት ነገሮች በሙሉ ተላልፏል።

1ኛ. ለእርሱ ፈረሶችን አያበዛም (ዘጸ 17÷16)

«ሰሎሞንም ሰረገሎችንና ፈረሰኞችን ሰበሰበ፣ አንድ ሺህ አራት መቶ ሰረገሎች፣ አሥራ ሁለት ሺህም ፈረሰኞች ነበሩት» 1ነገ 10÷26

2ኛ ልቡም እንዳይስት ሚስቶችን ለእርሱ አያበዛም ዘጸ 17÷17ሀ

«ለእርሱም ወይዛዝር የሆኑ ሰባት መቶ ሚስቶች፣ ሦስት መቶም ቁባቶች ነበሩት፤ ሚስቶቹም ልቡን አዘነበሉት» 1ነገ 11÷3

3ኛ ወርቅና ብርም ለእርሱ እጅግ አያበዛም (ዘጸ 17÷17ለ)

«ንገሡ ሰሎሞን የሚጠጣበት ዕቃ ሁሉ ወርቅ ነበር፣ የሊባኖስ ዱር የተባለውም ቤት ዕቃ ሁሉ ጥሩ ወርቅ እንጂ ብር አልነበረም። በሰሎሞን ዘመን ብር ከቶ አይቆጠርም ነበር» ነገ 10÷21 በተጨማሪ፤ ስለ ንጉሡ ወግ፣ በክፍል አንድ ላይ ያለውን የዘጻግም 17 ጥናት ማንበብ ይቻላል

እግዚአብሔር ምንም ዓይነት መመሪያ ሲሰጥ፣ ያንን መመሪያ መከተል ስለሚበጀን ነው እንጂ እንዲሁ መመሪያ ለመስጠት አይደለም። በምንም ዓይነት የሕይወት ሚና ውስጥ ብንሆን፣ እግዚአብሔር በቃሉ ለዚያ ሚና የሰጠን መመሪያ አለ። የተሰጠንን መመሪያ እንደሚገባ ሳንከተል ያንን ሚና በድል መወጣት አንችልም። አባት ብንሆን፣ እግዚአብሔር በቃሉ ለአባቶች የሰጠውን መመሪያ መከተል አለብን (ኤፌ 6÷4)። ባል ብንሆን ወይም ሚስት፣ እግዚአብሔር ለባሎችና ለሚስቶች የሰጠውን መመሪያ መከተል አለብን ኤፌ. 5÷21-33። ልጆች ብንሆንም እንደዚሁ ኤፌ. 6÷1-3። የቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ እረኛ፣

ወይም ሽማግሌ ብንሆን እግዚአብሔር በቃሉ ለሽማግሌዎች የሰጠውን መመሪያ መከተል አለብን 1ጴጥ. 5፥1-4፣ 1ጢሞ 3፥1-7 ከላይ ያሉትን ሚናዎችና ጥቅሶች ለምሳሌ ያህል ጠቀስን እንጂ ዋናው ሐሳብ፣ የእግዚአብሔርን መመሪያ ቸል ብለን ሚናችንን ለእግዚአብሔር ክብርና ለሰዎች ጥቅም በሚሆን ሁኔታ መፈጸም እንደማንችል ለመጠቆም ነው።

ንጉሥ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን መመሪያ ባለመከተሉ እግዚአብሔርን አሳዘነ፣ እግዚአብሔርን አስቆጣ 1ነገ 11፥9-11።

ከዚህም የተነሣ የሰሎሞን መንግሥት ከልጁ ከሮብዓም ተወሰደ፣ የሰሎሞን ባሪያ ለነበረ ኢዮርብዓም ለሚባል ሰው እንደሚሰጥ እግዚአብሔር ይናገራል። ይህም በምዕራፍ 12 ሲፈጸም እናያለን።

ከምዕ. 11፥14-26 ድረስ፣ እግዚአብሔር የተለያዩ ሰዎችን በሰሎሞን ላይ ጠላት አድርጎ እንዳስነሳበት የሚገልጽ ክፍል ነው። ከቁ. 27-40 የሰሎሞን ባሪያ ለነበረው ለኢዮርብአም፣ በእሥራኤል ላይ ንጉሥ እንደሚሆን ነቢዩ አኪያ እንደተነበየለት የሚናገር ክፍል ነው። ይህንን ክፍል ስናይ፣ እግዚአብሔር ለኢዮርብዓም፣ ከዳዊት ያላነሰ የተስፋ ቃሎችን እንደሰጠው እንመለከታለን። «ባሪያዬ ዳዊት እንዳደረገ፣ ያዘዝሁህን ሁሉ ብትሰማ፣ በመንገዴም ብትሄድ፣ በፊቴም የቀናውን ብታደርግ፣ ሥርዓቴንና ትእዛዜን ብትጠብቅ፣ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፣ ለዳዊትም እንደሠራሁለት ጽኑ ቤት እሠራልሃለሁ፣ እስራኤልንም ለአንተ እሰጥሃለሁ።» ቁ. 38 ይህን የመሰለ ጽኑ ቃል ኪዳን ከተገባለት በኋላ፣ በእርሱ በኩል የሚጠበቅበትን ሆኖ ስላልተገኘ ለእስራኤል ነገሥታት ሁሉ የርኩሰትና የዓመጽ መለኪያ (Standard) ሆኖ እናገኘዋለን። «እስራኤልን ካሳተው ከኢዮርብአም ኃጢአት አልራቀም» የሚለው ሐረግ፣ ለአብዛኛዎቹ የእስራኤል ነገሥታት እንደተጠቀሰ በመጽሐፈ ነገሥት መጻሕፍት ማየት ይቻላል። እግዚአብሔር የሰውን ፊት አይቶ አያደላም፣ ለሮብዓም ሰጥቶት የነበረው የተስፋ ቃል ይህንን ያረጋግጥልናል። ነገር ግን ኢዮርብአም በራሱ ፈቃድ አመጸኛና የኃጢአተኛ ነገሥታት ሁሉ መለኪያ ሲሆን እናያለን።

## ክፍል II

<u>የእስራኤል መንግሥት መከፈል።</u>

### ምዕራፍ 12:- የሰሎሞን ልጅ የሮብዓም መንገሥ፣ የኢዮርብዓም በአሥሩ ነገደ-እሥራኤል ላይ መንገሥ።

በዚህ ምዕራፍ፣ የሰሎሞን ልጅ ሮብዓምን ለማንገስ የእስራኤል ጉባኤ ሁሉ ተሰብስበው፣ «አባትህ ቀንበር አክብዶብን ነበር፣ አሁንም አንተ ጽኑውን የአባትህን አገዛዝ፣ በላያችን የጫነውንም የከበደውን ቀንበር አቃልልን፣ እኛም እንገዛልሃለን።» (ቁ. 3-4) ይሉታል። ሮብዓምም ስለዚህ ጉዳይ፣ በመጀመሪያ በዕድሜ ሽማግሌዎች የነበሩትን የአባቱን አማካሪዎች ይጠይቅና መልካም ምክር ይመክሩታል። «ለዚህ ሕዝብ አሁን ባሪያ ብትሆን ብትገዛላቸውም፣ መልስህም በገርነት ብትናገራቸው፣ በዘመኑ ሁሉ ባሪያዎች ይሆኑልሃል ብለው ተናገሩት እርሱ ግን ሽማግሌዎች የመከሩትን ምክር ትቶ ከእርሱ ጋር ካደጉትና በፊቱ ይቆሙ ከነበሩት ብላቴኖች ጋር ተማከረ።» ቁ 7-8። እነዚህ አብሮ አደጎችም ግልፍተኝነት የተሞላበት ስሜታዊና ክፉ የሆነ ምክርን ይመክሩታል። «ታናሺቱ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ትወፍራለች። አሁንም ከባድ ቀንበር ጭኖባችኋል እኔ ግን በቀንበራችሁ ላይ እጨምራለሁ፣ አባቴ በአለንጋ ገርፎአችኋል፣ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ በላቸው ብለው ተናገሩት ቁ. 10-11።

ነገሩ ከእግዚአብሔር አስቀድሞ የተወሰነ ነገር ስለነበረ ሮብዓም መልካም የነበረችውን የሽማግሌዎች ምክር ትቶ የወጣቶችን ጭፍን ምክር በመከተል ለእስራኤል ጉባኤ ጽኑ ምላሽ

ይመልስላቸዋል:: «እግዚአብሔርም በሴሎናዊው በአኪያ አድርጎ ለናባጥ ልጅ ለኢዮርብዓም የተናገረውን ነገር እንዲያጸና ከእግዚአብሔር ዘንድ ተመድቦ ነበርና ንጉሡ ሕዝቡን አልሰማም::» (ቁ. 15)

የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነትና ሁሉን ቻይነት ለጊዜው ተወት አድርገን፣ ይህንን ክፍል በምንመለከትበት ጊዜ ስለ ምክር የምንማረው ነገር አለ:: ምክር መቀበል ያለብን በዕድሜም ሆነ በልምምድ በሰል ካሉ ሰዎች እንጂ ከእኩዮቻችን ወይም ብስለትና ጥልቀት ከሌላቸው ሰዎች አለመሆኑን በግልጽ ያሳየናል:: እነዚህ አብሮ አደጎች ምናልባት ስሜታችንን የበለጠ ይቀሰቅሱት፣ ወኔአችንን የበለጠ ያነሳሱት ይሆናል:: በአንጻሩ ደግሞ የበሰሉትና ጠለቅ ያለ ልምምድ ያላቸው ሰዎች፤ ስሜታችንን የሚያቀዘቅዙ፣ ወኔአችንን የሚገቱ፣ ሐሳባችንን የሚለጉሙ ይመስለን ይሆናል:: አንዳንድ ጊዜ በእውነትም ስሜታችን ቀዝቀዝ ማለት፣ ወኔአችን መገታት፣ ሐሳባችን ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ልጓም መያዝ ያስፈልገዋል::

ይህ ከላይ የተጠቀሰው ሐሳብ አጠቃላይ መመሪያችን ሆኖ ሳለ፤ አንዳንድ ጊዜ የሽማግሌ አጥፊ፣ የወጣት አልሚ አይታጣም:: በዕድሜና በልምምድ የሽመገለ ቢሆንም የመንፈስ ቅዱስ ሕያው አሠራር በውስጡ ከሌለበት፤ እንደ ዔሊ፣ የእግዚአብሔር ጥሪ የሚቀሰቅሳቸውን ሳሙኤሎች «ተመልሰህ ተኛ» የሚሉ ሊኖሩ ይችላሉ:: (1ሳሙ. 3÷3-7):: የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ በሕይወታቸው የሚሠራ ወጣቶች ደግሞ በዕድሜ ከሸመገሉ ይልቅ የበለጠ ጥበብና ማስተዋል ሊኖራቸው ይችላል:: (መዝ 118) (119)99-100:: በመጽሐፈ ኢዮብ፣ ሦስቱ የኢዮብ አማካሪዎች የሚናገሩትን ከጨረሱ በኋላ፣ የሁሉም ታናሽ የነበረው ዔሊሁ «እኔ በዕድሜ ታናሽ ነኝ፣ እናንተ ግን ሽማግሌዎች ናችሁ፤ ስለዚህም ሰጋሁ፣ እውቀቴን እገልጥላችሁ ዘንድ ፈራሁ:: እንደዚህም አልሁ፡ - ዓመታት በተናገሩ ነበር፤ የዓመታትም ብዛት ጥበብን ባስተማረች ነበር:: ነገር ግን በሰው ውስጥ መንፈስ አለ፣ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ማስተዋልን ይሰጣል::» (ኢዮብ 32÷6-8) በማለት ዕድሜ ከሚሰጠው ጥበብና ማስተዋል ይልቅ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚሰጠው ጥበብና ማስተዋል እንደሚልቅ ይናገራል::

የሚልቀው ግን በዘመናት የእግዚአብሔር መንፈስ ካስተማራቸው የበሰሉ ሰዎች ምክርን መቀበል ነው:: የዕድሜንም ሆነ የልምምድን እንዲሁም ከእግዚአብሔር መንፈስ ምክርና ማስተዋል አግኝተዋልና:: ከሁሉ በላይ፤ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ድንቅ መካር» ተብሎ በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል የተሰየመ ድንቅ መካር ነውና፣ በምናደርገው ውሳኔ ሁሉ የእርሱ ድንቅ ምክር አይለየን ኢሳ 9÷6::

ሮብዓም የወጣቶቹን ምክር ሰምቶ ጽኑ ምላሽ ከመለሰላቸው በኋላ፤ እስራኤል ሁሉ ከይሁዳና ከብንያም ነገድ በስተቀር ሮብዓምን ትተው ኢዮርብዓምን በላያቸው አነገሡ::

ሮብዓምም እስራኤልን በኃይል ለማስገበር አስገባሪውን አዶኒራምን ቢልክ በድንጋይ ወግረው ስለገደሉት ከይሁዳና ከብንያም ነገድ 180.000 ሰልፈኞች ሰብስቦ ከእስራኤል ጋር ለመዋጋት ተነሳ:: በዚህን ጊዜ፤ «የእግዚአብሔር ቃል ወደ እግዚአብሔር ሰው ወደ ሳማያ ... ይህ ነገር ከእኔ ዘንድ ነውና አትውጡ፣ የእስራኤልንም ልጆች ወንድሞቻችሁን አትውጉ፤ እያንዳንዱም ወደ ቤቱ ይመለስ ብለህ ንገራቸው ሲል መጣ::» ቁ. 22-24::

«የእግዚአብሔርንም ቃል ሰሙ እንደ እግዚአብሔርም ቃል ተመልሰው ሄዱ ቁ. 24ለ:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተደረገው አብዛኛው ነገር የሚያሳዝን ነገር ቢሆንም ይህ ከላይ የተጻፈው ቃል እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው:: ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ ከስህተትና ከጥፋት መንገዱ ከመመለስ የበለጠ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነገር ምን አለ? የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የባሪያን መልክ ለብሶ የወረደውም፣ ሰው የእግዚአብሔርን

ህያው ቃል ሰምቶ ከጥፋቱና ከስህተቱ እንዲመለስ ነው። አንድ ኃጢአተኛ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ «በሰማይ ታላቅ ደስታ» ይሆናል። ንስሐ የሚለው ቃል፤ የራስን ሐሳብ ትቶ ወደ እግዚአብሔር ሐሳብ መመለስ እንደመሆኑ መጠን፤ ሮብዓምና ሠራዊቱ ያደረጉትም ከዚህ ያነሰ ድርጊት አይደለም። የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተውና እግዚአብሔርን ፈርተው ልባቸው ባይመለስ ኖሮ እግራቸውም ባልተመለሰ ነበር። ይህ መታዘዛቸውና መመለሳቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብን በጦርነት ከመሞት እንደ አዳነ ማስተዋል እንችላለን።

ሌላው፣ ከዚህ ክፍል የምንማረው ድንቅ ነገር የነቢያት አገልግሎት ምን ያህል ወሳኝና አስፈላጊ አገልግሎት እንደሆነ ነው። የእግዚአብሔር ሰው የነበረው ነቢዩ ሳማያ፣ የእግዚአብሔርን የማስጠንቀቂያ ቃል ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ባያስጠነቅቅ ኖሮ፣ ይህ ሁሉ ሕዝብ በደም በታጠበ ነበር።

እግዚአብሔር ለነቢዩ ኤርምያስ እንዲህ ይለዋል፤

«ያዘዝሁህን ቃል ሁሉ ተናገራቸው አንዳችም ቃል አታጉድል። ምናልባት ይሰሙ ከክፉ መንገዳቸውም ይመለሱ ይሆናል፤ እኔም ስለ ሥራቸው ክፋት ያሰብሁባቸውን ክፉ ነገር እተዋለሁ።? (ኤር 26፥2-3) እግዚአብሔር ሳይልካቸው ለሚሮጡ፣ ሳይናገራቸው ትንቢት ለሚናገሩ ደግሞ እንዲህ ይላል፡- «እኔ ሳልካቸው እነዚህ ነቢያት ሮጡ፤ እኔም ሳልናገራቸው ትንቢትን ተናገሩ። በምክሬ ግን ቢቆሙ ኖሮ፣ ለሕዝቤ ቃሌን ባሰሙ ነበር፣ ከክፉ መንገዳቸው፣ ከሥራቸውም ክፋት በመለሱአቸው ነበር» (ኤር 23፥21-22)።

እውነተኛ ነቢያት፣ ሰውን ከክፉ መንገድና ከጥፋት ሲያድኑ ሐሰተኛ ነቢያት ደግሞ ሰዎች በሐሰት እንዲታመኑ ያደርጋሉ። «ነቢዩ ኤርምያስም ነቢዩን ሐናንያን፡- ሐናንያ ሆይ፣ ስማ ይህ ሕዝብ በሐሰት እንዲታመን አድርገሃል እንጂ እግዚአብሔር አላከህም። ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። እነሆ ከምድር ላይ እሰድድሃለሁ፤ በእግዚአብሔር ላይ ዓመጽን ተናግረሃልና በዚህ ዓመት ትሞታለህ አለው። ነቢዩም ሐናንያ በዚያው ዓመት በሰባተኛው ወር ሞተ» ኤር 28፥15-17። እግዚአብሔር እንደ ሳማያና እንደ ኤርምያስ ያሉ እውነተኛ ነቢያትን ያብዛልን። ለሐሰተኛ ነቢያት ግን ወዮላቸው፣ የሚጠብቃቸው ሞት ነውና። «ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ላይ ታሥሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይቀለዋል።»

ከ1ነገሥት 12፥25-33 ያለው ክፍል የሚያሳየው፣ ኢዮርብዓም በነቢዩ አኪያ አማካኝነት ምዕ. 11፥26-40 እግዚአብሔር በእስራኤል 10 ነገዶች ላይ እንደሚያነግሠው ከተነገረለትና ከነገሠ በኋላ፤ እግዚአብሔር ከዳዊት በማያንስ የተስፋ ቃል የሰጠውን መንግሥትና ሥልጣን በራሱ ብልጠትና ኃይል ሊያጸና ሲሞክር ነው።

«ኢዮርብዓምም በልቡ፡- አሁን መንግሥቱ ወደ ዳዊት ቤት ይመለሳል። ይህ ሕዝብ በእግዚአብሔር ቤት መሥዋዕትን ያቀርብ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ቢወጣ፣ የዚህ ሕዝብ ልብ ወደ ጌታቸው ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ ሮብዓም ይመለሳል፣ እኔንም ይገድሉኛል አለ» (ቁ. 26-27)። እግዚአብሔር በምዕ. 11፥31-39 የተናገረውን ረሳ። በተለይም በምዕ 11፥38 ላይ «ባሪያዬም ዳዊት እንዳደረገ ያዘዝሁህን ሁሉ ብትሰማ፣ በመንገዴም ብትሄድ፣ በፊቴም የቀናውን ብታደርግ፣ ሥርዓቴንና ትእዛዜን ብትጠብቅ፣ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፣ <u>ለዳዊትም እንደ ሠራሁለት ጽኑ ቤት እሠራልሃለሁ</u> እስራኤልንም ለአንተ እሰጣለሁ።» እግዚአብሔር የሰውን ፊት አይቶ የሚያዳላ ስላልሆነ ከዳዊት ያላነሠ የተስፋ ቃል ነበረ የገባለት። እርሱ ግን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል አስታውሶ በዚያ ከመታመንና ከማረፍ ይልቅ የራሱን ዋስትና ለማስጠበቅ ፈለገ። የራሱን ጠማማ መንገድ ቀየሰ። ክፉ ምክርን ከአማካሪዎቹ ጋር ተማከረ፤ በእስራኤልም የባዕድ አምልኮን ጀመረ። «ንጉሡም ተማከረ፣ ሁለቱም የወርቅ ጥጆች አድርጎ

እስራኤል ሆይ ወደ ኢየሩሳሌም ትወጡ ዘንድ ይበዛባችኋል፤ ከግብጽ ምድር ያወጡህን አማልክቶችህን እይ አላቸው። አንዱን በቤቴል ሁለተኛውንም በዳን አኖረ ቁ. 28-29።

አዮርብዓም ለራሱ ክብርና ሥልጣን ሲል የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ስህተት አምልኮና ሃይማኖት መራ። ኢዮርብዓም የተከለው መራራ ሥር እስከመጨረሻው እስራኤልን በስህተትና በጥፋት መንገድ ሲመራ እናያለን። ከእርሱ በኋላ በእስራኤል ላይ የነገሡ ነገሥታት በሙሉ በእርሱ ክፋት ተመርዘው አብዛኞቹም ከእርሱ ብሰው አለፉ። ከኢዮርብዓም የምንማረው ግልጽ ትምህርት ቢኖር፤ የስህተት አስተሳሰብ ወደ ስህተት ድርጊትና ወደ ጥፋት እንደሚመራ ነው። በቁ. 26 ና 27 ላይ ያሰበው የስህተት ሐሳብ ነው ወደ ክፉ መንገድና ጥፋት የመራው።

ምዕራፍ 13

ይህ ምዕራፍ በአስደናቂ ነገሮችና ትምህርቶች የተሞላ ነው። አጠቃላይ ሐሳቡ፤ በእግዚአብሔር ተልእኮ ወደ ኢዮርብዓም ስለሄደ አንድ የእግዚአብሔር ሰውና፤ ከእርሱ በኩልም ሆነ በእርሱ ላይ ስለተከናወኑት ነገሮች የሚተርክ ነው።

ይህ ስሙ ያልተገለጠ ነቢይ፣ በእግዚአብሔር ቃል፤ ኢዮርብዓም ወደ ነበረበት ወደ ቤቴል በመምጣት እግዚአብሔር በአፉ ያደረገውን ትንቢት ይናገራል። በዚያን ጊዜ ኢዮርብዓም በመሠዊያው አጠገብ ቆሞ ዕጣን እያጠነ ነበር።

ይህ ነቢይ የተናገረውም ቃል የሚከተለው ነበር፤ «መሠዊያ ሆይ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ - እነሆ፣ ስሙ ኢዮስያስ የሚባል ልጅ ለዳዊት ቤት ይወለዳል፣ ዕጣንም የሚያጥኑብህን የኮረብታ መስገጃዎቹን ካህናት ይሠዋብሃል፣ የሰዎቹንም አጥንት ያቃጥልብሃል ብሎ በእግዚአብሔር ቃል ጮኸ» (ቁ. 2) ይህ የሚያስደንቅ ትንቢት፤ ገና ከ300 ዓመታት በኋላ ሊመጣስላለ ንጉሥ ኢዮስያስ በመተንበይ የኢዮርብዓምን ኃጢአት እንደሚበቀል ይናገራል። የዚህን ትንቢት ፍጻሜ በ2ነገ 23፥15-18 እናነባለን።

ይህ ክፍል የሚያሳየን፤ እኛንም ከመወለዳችን በፊት፣ ከዘመናት በፊት፤ እግዚአብሔር እንደሚያውቀን ነው። ማወቅ ብቻ ሳይሆን፤ ብንሰማውና ብንታዘዘው፣ ለእርሱ ክብር ማድረግና ማከናወን ያለብንን ነገር ጭምር «ከዘመናት በፊት» በራሱ መዝገብ ጽፎልናል። ዳዊት በመዝ. 139፥14-18 ላይ የሚገልጽልን ሐሳብ ይህንኑ ነው። «...ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ፣ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ።»

ይህ የእግዚአብሔር ነቢይ ይህንን አስደናቂ ትንቢት ከተናገረ በኋላ፤ ኢዮርብዓም እጁን በነቢዩ ላይ በመዘርጋት «ያዙት» ይላል። «በእርሱም ላይ የዘረጋት እጅ ደረቀች፣ ወደ እርሱም ይመልሳት ዘንድ አልተቻለውም» ቁ.4። እኛ እግዚአብሔርን ታዝዘን በምንናገርበት ወይም በምናደርግበት ጊዜ፣ በእኛ ላይ በሚነሳው እጅ ላይ እግዚአብሔር ይነሳል። ከፍ ካለው በላይ ከፍ ያለው ጌታችን «በአንቺ ላይ የተሠራ መሣሪያ ሁሉ አይከናወንም» (ኢሳ. 54፥17)፤ ብሎ ቃል ገብቶልናል። ንጉሡ ኢዮርብዓም የእጁን መድረቅ ሲመለከት ዛቻውን ትቶ ልመና ማቅረብ ጀመረ። «እነርሱ ወደ አንተ ይመለሳሉ እንጂ አንተ ወደ እነርሱ አትመለስም» የሚለው አምላካዊ ቃል በእርግጥም እውነት ነው። «ንጉሡም የእግዚአብሔርን ሰው አሁን የአምላክህን የእግዚአብሔርን ፊት ለምን፣ እጄም ወደ እኔ ትመለስ ዘንድ ስለ እኔ ጸልይ አለው። የእግዚአብሔርም ሰው እግዚአብሔርን ለመነ፣ የንጉሡም እጅ ወደ እርሱ ተመለሰች፣ እንደቀድሞውም ሆነች» ቁ. 6።

ከቁ. 7-32 ያለው ክፍል፤ ይህ የእግዚአብሔር ሰው በድንቅ ሁኔታ የእግዚአብሔርን መልእክት ካስተላለፈ በኋላ፣ እራሱ ለእግዚአብሔር ያለው ታዛዥነት ሲፈተን እንመለከታለን።

ከቁ. 7-10 ባለው ክፍል፤ ንጉሡ «ከእኔ ጋር ወደ ቤቴ ና እንጀራም ብላ በረከትንም እሠጥሃለሁ» ይለዋል:: የእግዚአብሔርም ሰው «እንጀራ አትብላ፣ ውኃም አትጠጣ፣ በመጣህበትም መንገድ አትመለስ፤ በሚል በእግዚአብሔር ቃል ታዝዤአለሁና በዚህ ስፍራ እንጀራ አልበላም ውኃም አልጠጣም» በማለት ለንጉሡ ይመልስለታል:: በዚህ ክፍል የንጉሡን ፈተና እንዳለፈ እናያለን::

ከቁ. 11-19 ባለው ክፍል ግን ይኸው ፈተና ጠንከር ባለና ሽንገላ በተሞላበት መንገድ ይመጣበታል:: ይህ ትዕይንት በተደረገበት በቤቴል ከተማ የነበረ አንድ ሽማግሌ ነቢይ፤ የተከናወነውን ነገር ሲሰማ፣ በሌላ መንገድ በመመለስ ላይ የነበረውን የእግዚአብሔር ሰው በመከተል ያገኘውና፤ «እኔ ደግሞ እንደ አንተ ነቢይ ነኝ፤ መልአክም፡- እንጀራ ይበላ ዘንድ፣ ውኃም ይጠጣ ዘንድ ከአንተ ጋር ወደ ቤትህ መልሰው ብሎ በእግዚአብሔር ቃል ተናገረኝ አለው:: ዋሽቶም ተናገረው:: ከእርሱም ጋር ተመለሰ በቤቱም እንጀራ በላ፣ ውኃም ጠጣ::» ቁ. 18-19

በመጀመሪያ አልፎት የነበረውን ፈተና፤ አሁን አመጣጡ በስውር ስለነበረ፣ ፈተናውን ሲወድቅ እናያለን:: ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ የሚጥለን ፈተና ፊት ለፊት ግልጽ ሆኖ የሚመጣው አይደለም:: ነገር ግን፤ በስውር የብርሃን መልአክ መስሎ የእግዚአብሔርን ስም እየጠራ የሚመጣው የጠላት ሽንገላ ብዙ ጊዜ አጠላልፎ ይጥለናል:: «የእርሱን ሐሳብ አንስተውም» ሲል፣ የፊት ለፊቱንም ሆነ ስውሩን ያጠቃልላል:: ስውሩ ፈተና ግን የበለጠ ጥንቃቄና የመለየት ስጦታ /disiernment/ ያስፈልገዋል::

ውሸታሙ ነቢይ በውሸቱ በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ ቢሆንም፤ ይህኛው የእግዚአብሔር ሰው «በቀጥታ» እግዚአብሔር ለራሱ የነገረውን ትእዛዝ ነበረ «የሙጥኝ» ብሎ መያዝ የነበረበት:: እግዚአብሔር በቀጥታ በልባችን የተናገረንን፤ በውጫዊ ድምፅ (መልአክም ሆነ ነቢይ) መለወጥ ወይም መሻር የለብንም:: በአንጻሩ ደግሞ፤ እግዚአብሔር ለልባችን ሳይናገረንና ሳይመሰክርልን፣ ገና ለገና አንድ ነቢይ ወይም አንዲት ነቢይ (ተናግሯል) ተናግራለች ብለን መሸምጠጥ የለብንም:: እግዚአብሔር ለልባችን በቀጥታ የሚናገረን ድምፅ ከሌላ ከምንም ዓይነት ድምፅ ይበልጣል::

ከቁ. 20-32 የምናየው፤ ይህ የእግዚአብሔር ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ስላልጠበቀና ስለተታለለ የእግዚአብሔር ቅጣት ሲመጣበት ነው::

ከ20-22 የእግዚአብሔር ቃል ወደዚሁ ወደ ዋሸው ነቢይ መጥቶ በእግዚአብሔር ሰው ላይ ትንቢት ይናገራል::

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- በእግዚአብሔር አፍ ላይ ዐምጸሃልና፣ አምላክህም እግዚአብሔር ያዘዘህን ትእዛዝ አልጠበቅህምና፣ ተመልሰህም እንጀራ አትብላ፣ ውኃም አትጠ ጣ፣ ባለህ ስፍራ እንጀራ በልተሃልና፣ ውኃም ጠጥተሃልና፣ ሬሳህ ወደ አባቶችህ መቃብር አይደርስም ብሎ ጮኸ::» እንደተናገረውም ትንቢት «በመንገድ ላይ አንበሳ አግኝቶ ገደለው፤ (ቁ. 24)::

ይህ ሁኔታ ለሚያነበው ሁሉ ግራ ሊያጋባ የሚችል ነው:: እግዚአብሔር እንዴት በሐሰተኛና በአታላይ ነቢይ በኩል እውነተኛ የሆነ ቃሉን ያስተላልፋል? ይህ ሁኔታ፤ አሪት ዘኍልቁ የበለዓምን ታሪክ በክፍል አንድ ስናጠና የተመለከትነው ጥናት ነው:: የእግዚአብሔር ቃል በለዓምን «መተተኛና» «እብድ» እያለው፤ በአንዳንድ ስፍራ ግን ትክክለኛ ትንቢትን ሲናገር ይታያል:: እግዚአብሔር ቃሉን በአፉ አስቀምጦ ስለነበረ ሊናገረው የነበረውን መርገም ለውጦ በረከትን ለእሥራኤል እንዲናገር ሲያደርገው እናያለን ዘኍ. 23፥16-24፤25::

እነዚህ ሁኔታዎች የሚያሳዩን፤

ሀ. እግዚአብሔር ሁሉን በራሱ ፈቃድ እንደሚያደርግ /Sovereignty/

ለ. የእግዚአብሔር መንፈስ በእኛ በኩል አንድ ነገርን ቢያከናውን ትንቢት ቢሆን፣ ተአምር ቢሆን ወዘተ.. የእኛን ጽድቅ ወይም የእኛን እውነተኛነትና ታማኝነት እንደማያሳይ ነው።
ጌታ ኢየሱስ በማቴ 7÷22-23 «በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፣ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፣ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋችሁም፣ እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።» ብሎ ማስጠንቀቂያ የሰጠን፤ አፋችን ስሙን እየጠራና ቃሉን እየተናገረ፣ ልባችን ግን ዓመፀኛ ሊሆን እንደሚችል ሲያሳስበን ነው። ዋናው መልእክት በማቴ 7÷21 ተጽፏል፤ «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፣ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።» ስለዚህ፤ እግዚአብሔር ምን ያህል ትንቢት በአፌ ተናገረ፤ ወይም ምን ያህል ተዓምር በእጄ ሠራ? ሳይሆን፤ መጠየቅ ያለብን «በልቤ አመጽና እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኝ ነገር አለ ወይ?» ብለን ነው።

«አቤቱ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል?

በተቀደሰውም ተራራህ ማን ይኖራል?

በቅንነት የሚሄድ፣ ጽድቅንም የሚያደርግ

በልቡም እውነትን የሚናገር

በአንደበቱ የማይሸነግል፣

በባልንጀራው ላይ ክፉትን የማያደርግ....

እንዲህ የሚያደርግ ለዘላለም አይታወክም» መዝ 15

በ1ኛነገ 13 ላይ የምናየው ዋሾ ነቢይ እንደተነበየው በመንገድ ላይ ያ የእግዚአብሔር ሰው ሞቶ ሲያገኘው «ያለቅስለትና ይቀብረው ዘንድ ወደ ገዛ ከተማው ይዞት መጣ። ሬሳውንም በገዛ መቃብሩ አኖረው፤ ዋይ ዋይ ወንድሜ ሆይ እያሉ አለቀሱለት» ይላል። ወንድምን፤ ሸንግሎ፣ አታሎና ቀብሮ ማልቀስ። እግዚአብሔር ከእንደዚህ ዓይነት ግብዝነትና አመጽ ይጠብቀን። ይህንን ሽማግሌ ነቢይ የገፋፋው ምን ይሆን? ምናልባት፤ እንዴት እኔ ባለሁበት ከተማ መጥቶ ይህንን ድንቅ ትንቢት ንጉሡን የሚያንበረክክ እኔ እያለሁ ተናገረ? እኔ እያለሁ እግዚአብሔር እንዴት ተጠቀመበት? የሚል ቅናት ይሆን? ወይስ፣ አለኝ ብሎ የሚያስበው መንፈሳዊ ሥልጣን የተነካ የተደፈረ መስሎት ይሆን? እግዚአብሔር ከቅንዓትና ከምቀኝነት ይጠብቀን። «ወንድሜ ከእኔ ይልቅ ይሻላል» የሚልን ትሑት ልቦና ይስጠን።

በዚህ ምዕራፍ ሌላ የምናየው አንድ ነገር አለ። ይኸውም የአንበሳው አህያውንም ሆነ የእግዚአብሔርን ሰው ሬሳ አለመብላት ነው። አንበሳ በተፈጥሮው ሥጋ ፊት ለፊቱ ተቀምጦለት ዝም አይልም። እግዚአብሔር አንበሳውን ያዘዘው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የተላለፈውን የእግዚአብሔርን ሰው እንዲገድል ብቻ ስለነበረ፤ አንበሳው ከተሰጠው ትእዛዝ አልተላለፈም። የእግዚአብሔር ሰው የተላለፈውን ትእዛዝ አንበሳው ሲፈጽም እናያለን። «ሬሳውም በመንገድ ወድቆ፣ በሬሳውም አጠገብ አህያውና አንበሳው ቆመው፣ አንበሳው ሬሳውን ሳይበላው አህያውንም ሳይሰብረው አገኘ» (ቁ. 28)።

እንስሳት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሲፈጽሙ የእግዚአብሔር ሰዎች ግን ሲሳሳቱ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በተደጋጋሚ እናያለን። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የነቢዩ ዮናስና የዓሣ ነባሪውም ታሪክ ነው። ዮናስ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላልፎ ሲኮበልል ዓሣ

ነባሪው ግን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሲፈጽም እናያለን፡፡ የበለዓምንም እብድነት የመለሰች አህያዪቱ እንደነበረች የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል፡፡ «ቃል የሌለው አህያ በሰው ቃል ተናግሮ የነቢዩን እብድነት አገደ» 2ጴጥ. 2፥16፡፡

የሐዋርያው ጴጥሮስን ክህደትም በጩኸትዋ የጌታን ቃል እንዲያስታውስ አድርጋ ወደ ጸጸት የመለሰችው አንዲት ዶሮ ናት፡፡

ይህ 1ኛነገ 13 ምዕራፍ የሚደመደመው በኢዮርብዓም በንስሐ አለመመለስና በኃጢአት መንገድ በመጽናቱ ነው፡፡ «ከዚህም በኋላ ኢዮርብዓም ከክፉ መንገዱ አልተመለሰም»

1ኛነገ 14፡- ይህ ምዕራፍ በእስራኤል አሥሩ ነገዶች ላይ ነግሦ የነበረው የኢዮርብዓምን ክፉ ፍጻሜ ከቁ. 1-20 ሲያትት፤ ከቁ. 21-31 ደግሞ በይሁዳ ላይ ነግሦ ስለነበረው ስለ ሰሎሞን ልጅ ሮብዓም ፍጻሜ ያትታል፡፡

ስለ ኢዮርብዓም የሚናገረው ክፍል፣ አብያ ስለሚባል የኢዮርብዓም ልጅ መታመምና መሞት ትምህርታዊ የሆነ ታሪክ ዘግቧል፡፡ ኢዮርብዓም፤ ልጁ አብያ በታመመ ጊዜ ሚስቱን ወደ ነቢዩ አኪያ እንዲህ በማለት ይልካታል፤

«ተነሺ የኢዮርብዓምም ሚስት እንደሆንሽ እንዳትታወቂ ልብስሽን ለውጪና ወደ ሴሎ ሂጂ እነሆ በዚህ ሕዝብ ላይ እንዲነግሥ የነገረኝን ነቢዩ አኪያ በዚያ አለ፡፡

... በልጁም የሚሆነውን ይነግርሻል» (ቁ. 2-3)፡፡ የንጉሥ ኢዮርብዓም መልእክት ብዙ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያሳያል፡፡ እግዚአብሔር በምሕረቱና በቸርነቱ አንድ ቦታ አድርሷቸው እግዚአብሔርን እርግፍ አድርገው ከረሱ፣ ተግሣጹንም ከረገጡ በኋላ፤ አንድ ጭንቀትና መከራ ሲመጣባቸው እንደገና እርዳታውን ፍለጋ ወደ እርሱ ይጮኻሉ፡፡ በዚያን ጊዜም እንኳን እርዳታውን ከመከራ እንዲያወጣቸው ብቻ እንጂ እርሱን ፈልገው አይደለም የሚጠሩት፡፡

ሚስትየው እንደታዘዘችው ወደ ነቢዩ ሌላ ሴት መስላ ትሄዳለች፡፡ ነቢይ መሆኑን ካመነበት በሌላ በኩል ደግሞ ነቢዩን ለማታለል መሞከር ሞኝነት ነው፡፡ ይልቁንስ በእውነተኛ ልብና ንስሐ ወደ እግዚአብሔር ቢቀርብ ለልጁ ብቻ ሳይሆን ለራሱም ይበጀው ነበር፡፡

ነቢዩ አኪያ፤ ገና የኢዮርብዓም ሚስት ወደ እርሱ ሳትደርስ እግዚአብሔር ነግሮት ስለነበረ፤ ገና ኮቴዋን በውጭ ሲሰማ፣ ዕጢዋን ዱብ የሚያደርግ ቃል ይናገራታል፡፡

«የኢዮርብዓም ሚስት ሆይ፣ ግቢ፣ ስለ ምንስ ሌላ ሴት መሰልሽ? እኔም ብርቱ ወሬ ይገፀ ተልኬልሻለሁ» (ቁ. 6)፡፡ አኪያ ምንም እንኳን ሽምግሎና አይኖቹ ፈዘው ቢሆኑም እንኳን፣ (ቁ. 4) መንፈሳዊ አካል አይሸመግልምና፣ በመንፈሳዊ አይኖቹ እግዚአብሔር ሲገልጥለት እናያለን፡፡ «በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም» የሚለውን ቃል አጉልቶ የሚያሳይ ትእይንት ነው፡፡

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ስለ ኢዮርዓምም ሆነ ስለ ልጁ እግዚአብሔር የተናገረው አንድ በአንድ ይነግራታል፡፡ የኢዮርብዓም ኃጢአት እግዚአብሔርን እጅግ ያስቆጣና እስራኤልን ሁሉ ያሳተ ሥር-ነቀል የሆነ ኃጢአት ስለነበረ፤ እግዚአብሔር እርሱንና ዘሩን ፈጽሞ እንደሚያጠፋ ይነግራታል፡፡ የኢዮርብዓም ኃጢአት፤ የእግዚአብሔር ሰዎች በድካማቸውና ባለማስተዋላቸው ኃጢአትን እንደሚሠሩት ዓይነት ኃጢአት አልነበረም፡፡ ነገር ግን ከክፉ ልብ

የመነጨ «ሆን ብሎ» ይህንንና ይህንን አደርጋለሁ ብሎ ባዕድ አምልኮን በእሥራኤል ምድር የተከለና የሐሰትን አምልኮ የፈለሰፈ ነው።
ይህንን በምዕ. 12÷25-33 ባለው ክፍል ተመልክተናል።

የኢዮርብዓም ኃጢአት ሥር ነቀል መሆኑን የምናውቀው እግዚአብሔር በእርሱ ኃጢአት ምክንያት ያስተላለፈውን ፍርድ ስንመለከት ነው። «እግዚአብሔርንም ያስቆጡ ዘንድ፣ የማምለኪያ አፀድ ተክለዋልና ለአባቶቻቸው ከሰጣቸው ከዚህ በታች ከመልካሚቱ ምድር እስራኤልን ይነቅላል፣ በወንዙም ማዶ ይበትናቸዋል። ስለ በደለውና እስራኤልንም ስላሳተበት ስለ ኢዮርብዓም ኃጢአት እስራኤልን ይጥላል።» (ቁ 15-16)።

ይህንን ቃል ስናጤን፤ እግዚአብሔር ኢዮርብዓም ስለሠራው በደልና ኃጢአት «ከመልካሚቱ ምድር እስራኤልን ይነቅላል» «እስራኤልን ይጥላል» ነው የሚለው። እስራኤል በእውን ከመልካሚቱ ምድር የተነቀሉት ከብዙ ዓመታት (ምናልባት ወደ 200 የሚጠጉ ዓመታት) በኋላ ነው። የእስራኤልን ከመልካሚቱ ምድር መነቀል የምናገኘው በ2ነገ 15÷29 ላይ ነው።

በ1ነገ 14፤ ከኢዮርብዓም ሥር-ነቀልና አስከፊ ኃጢአት ሌላ የምናየው መልካም ነገር፤ እግዚአብሔር ስለ ታመመው የኢዮርብዓም ልጅ የተናገረው ቃል ነው። «በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ዘንድ በኢዮርብዓም ቤት በዚህ ልጅ መልካም ነገር ተገኝቶበታልና ከኢዮርብዓም ቤት እርሱ ብቻ ይቀበራል» ቁ. 13። የሚያስደንቀው ነገር፤ ይህ ልጅ ርኩስና ክፉ በሆነ ቤትና አካባቢ በጎ ኀሊናውን ጠብቆ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን አገኘ። በአካባቢያችን ማመካኘት እንደማንችል ያስተምረናል። እያንዳንዱ ግለሰብ ክፉንና መልካምን ለማድረግ ነጻ ምርጫ አለው። ይህ ብላቴና በክፉ ውቅያኖስ ውስጥ እንዳለች መልካም ደሴት ሆኖ ተገኘ። ከዚህ ልጅ የምንማረው ሌላ ነገር ቢኖር፤ ሞት ሁልጊዜ ለክፉ እንዳልሆነ ነው። በረጅም ዕድሜ በክፋት በኃጢአት ከመዋኘት በአጭሩ ከክፋት ተጠብቆ መገላገል ይሻላል። ኢሳ 57÷1 የሚናገረው ሐሳብ ይህንኑ ነው። መልካም ሰዎች ሊመጣ ካለው ክፉ ነገር እንዲጠበቁ እግዚአብሔር እንደሚወስዳቸው እንድናስተውል ያሳስበናል።

ነቢዩ አኪያ ለኢዮርብዓም ሚስት ከተናገረው ክፍል፤ አንድ ሳንጠቅስ ማለፍ የማንፈልገው ቃል አለ። ይህም ቃል እግዚአብሔር ስለ ዳዊት የተናገረው ቃል ነው። «ነገር ግን በፍጹም ልቡ እንደተከተለኝ፣ በፊቴም ቅን ነገር ብቻ እንዳደረገ፣ ትእዛዜንም እንደጠበቀ እንደ ባሪያዬ እንደ ዳዊት አልሆንክም (ቁ. 8)።

ይህንን ቃል ስንመለከት፤ እግዚአብሔር እንዴት «በፊቴም ቅን <u>ነገር ብቻ</u> እንዳደረገ» ብሎ ለዳዊት ይመሰክራል የሚለው ጥያቄ ወደ ልባችን መምጣቱ አይቀርም። ዳዊት የኦርዮን ሚስት ወሰደና ኦርዮንን አስገድሎ በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ንስሐ የገባበትን ቃል በመዝ 51÷4 ስናይ «አንተን ብቻ በደልኩ፣ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ» በማለት በእግዚአብሔር ፊት ክፉትን እንዳደረገ ኃጢአቱን አውቆ ንስሐ ይገባል። እግዚአብሔር ግን በዚህ ክፍል፤ «በፊቴ ቅን ነገር ብቻ እንዳደረገ» ይለዋል። ይህ የሚያሰየን

1. ዳዊት ሆን ብሎና በአመጽ ተነሳስቶ ያደረገው ኃጢአት ሳይሆን ከሥጋው ድካም የተነሣ የወደቀበት ኃጢአት እንደሆነ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ።

2. ዳዊት ከልቡ ንስሐ በገባ ጊዜ፤ «ዓመጻቸውን እምራቸዋለሁ፤ ኃጢአታቸውንም ደግሜ አላስብም» ኤር 31÷34 የሚል መሐሪና ይቅር ባይ አምላክ ስለሆነ፤ እንደ ቃሉ የዳዊትን ኃጢአት ከፊቱ ስለጣለ ነው።
   በተጨማሪም፤ በሚክያስ 7÷19 በአዲሱ መደበኛ ትርጉም

«ተመልሰህ ትራራልናለህ፤

ኃጢአታችንን በእግርህ ትረግጣለህ፣
በደላችንንም ሁሉ ወደ ጥልቁ ባሕር ትጥላለህ።» በማለት የእግዚአብሐርን ምሕረት ያበስርልናል።
ይህ ለሁላችን ትልቅ ተስፋ ነው። እንደ ዳዊት በእውነተኛና ልባዊ ጸጸት ንሥሐ ከገባን ኃጠ ‚አታችን ከፊቱ ተወግዷል፤ ከእኛም ፊት መወገድ አለበት። እርሱ ደግሞ አያስታውሰውም፤ እኛም፣ ደግመን እንዳንወድቅ ለመጠንቀቅ ካልሆነ በቀር ደግመን ማስታወስ የለብንም።

በ1ነገ 14፥21-31 የምናየው የሮብዓምን የፍጻሜ ታሪክ ነው። የሮብዓምና ይሁዳ ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ስም በሚጠራበት በኢየሩሳሌም ከተማና መቅደሱ ባለበት ስፍራ ቢሆኑም፤ እነርሱም በልባቸው ከእግዚአብሔር ርቀው ነበር። «ይሁዳም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሠራ» ቁ. 22።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ያለውን የእስራኤልንና የይሁዳን ኃጢአት ወይም የኢዮርብዓምንና የሮብዓምን ኃጢአት ስናስተያይ፣ ልዩነቱ፤ አንዱ ከእግዚአብሔር ቤትና ፊት እልም ብሎ ጠ ፍቶ በኃጢአት የሚዋኝ ሲሆን፤ ሌላው ግን ምንም በኃጢአት ውስጥ ቢሆንና ክፉን ቢሠራም ከእግዚአብሔር ቤት ጭልጥ ብሎ አልጠፋም። ምንም ቢሆን፤ እስከነ ድካማችንም ቢሆን በእግዚአብሔር ቤት መሆን ይሻለናል። ይህም ሆኖ ግን፤ ወደ ንስሐና ወደ ጸጸት ካላመጣን መጨረሻው ጥፋት ነው።

ምዕራፍ 15፡ -

ይህ ምዕራፍ ስለ ሮብዓም ልጅ አብያምና ስለ አብያም ልጅ አሳ ንግሥና ሲተርክ፤ በእስራኤል ወገን ደግሞ ስለ ኢዮርብዓም ልጅ ናዳብ መንገሥ፣ ባኦስ የሚባል ሰው ተነሥቶ ናዳብን እንደገደለውና የኢዮርብዓምን ዘር ሁሉ እንዳጠፋ ይተርካል።

ከዚህ ምዕራፍ ሊጠቀሱ የሚገባቸውን አንዳንድ ክፍሎች እንመልከት።
የሮብዓም ልጅ አብያም እንደ አባቱ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ እንዳደረገ ከገለጸ በኋላ ቁ. 3፤

«ነገር ግን ልጁን ከእርሱ በኋላ ያስነሣ ዘንድ ኢየሩሳሌምንም ያጸና ዘንድ አምላኩ እግዚአብሔር ስለ ዳዊት በኢየሩሳሌም መብራት ሰጠው» ቁ. 4 ይላል። ይህን ቃል በምናነብበት ጊዜ፣ ዳዊት የአብያም ቅድመ አያት ቢሆንም እንኳን፤ ከእርሱ በኋላ በመጡት ዘሮቹ ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት እንዲመጣ ያደረገ ጻድቅ ሰው እንደነበረ ማስተዋል እንችላለን። አብያም፤ ከእርሱ በኋላ በዙፋኑ ላይ የሚቀመጥ ልጅ ያገኘው በእርሱ ጽድቅ ሳይሆን በዳዊት ጽድቅ እንደነበረ የሚገልጽ ክፍል ነው።

በዚህ ምዕራፍም ሆነ በሚቀጥሉት ምዕራፎችና በ2ነገሥት መጽሐፍም በምንመለከትበት ጊዜ የይሁዳንና የእስራኤልን (አሥሩ ነገዶች) ነገሥታት ስናስተያይ፤ ይሁዳ፤ ከሰሎሞን ልጅ ከሮብዓም ጀምሮ እስከ መጨረሻው መስመሩን ጠብቆ፣ ልጅ የአባቱን ንግሥና ተክቶ ሲፈራረቁ እናያለን። ይህም የሆነው፤ ከላይ እንዳነበብነው፣ እግዚአብሔር ለባሪያው ለዳዊት ስለገባው ቃል ኪዳን እንደነበረ ግልጽ ነው።

የእስራኤልን የንግሥና ታሪክ በአንጻሩ ስንመለከት ደግሞ፤ በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ክፉና ሥር-ነቀል ኃጢአትና ክህደትን ከፈጸመው ከኢዮርብዓም የጀመረ ክፉ አርአያነት፣ ከእርሱ በኋላ ለሚነሱ ነገሥታት ሁሉ ሲተርፍና ከክፋት ወደ ክፋት ሲሄድ እናያለን። የእሥራኤልም መንግሥት በአብዛኛው፤ ንግሥና ከአንዱ ወደ አንዱ ይተላለፍ የነበረው፣ በሰላም ሳይሆን ደም በመፋሰስ እንደነበረ ከእግዚአብሔር ቃል መረዳት እንችላለን።

እነዚህ የይሁዳና የእስራኤል መንግሥታት፤ የአንድ አባት አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ ልጆች ቢሆኑም እንኳን ይህንን ያህል ታላቅ ልዩነት የሚታይባቸው፤ የሁለቱ ወገኖች ሥርና ግንድ ሆነው የመንግሥታቸውን ፈርና ትልም ያወጡት ነገሥታት፤ ማለትም፣ የዳዊትና የኢዮርብዓም ልዩነት ነው። የይሁዳ ሥርና ግንድ ዳዊት ሲሆን፤ የእስራኤል 10ሩ ነገዶች ሥርና ግንድ ደግሞ ኢዮርብዓም ነበር።

የዳዊትን ትልም ተከትለው ከነገሡት ነገሥታት ጥቂት ክፉዎች ቢኖሩም በአብዛኛው መልካምን ነገር ያደረጉ ነበሩ። በእሥራኤል በኩል ከነበሩት ነገሥታት ግን፣ አንድ ስንኳ በእግዚአብሔር ፊት መልካም የነበረ ንጉሥ አልነበረም።

ይህንን ጉዳይ ወደ እኛ ስንመልሰው፤ እኛም ከእኛ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ የመልካም ወይም የክፉ ምሳሌ መሆን እንደምንችል፤ ለመጪው ትውልድ በረከት ወይም መርገም መሆን እንደምንችል ያሳየናል።

ከቁ. 9-24 ያለው ክፍል፤ የይሁዳ ንጉሥ የአብያም ልጅ አሳ በፋንታው እንደነገሠና በእግዚአብሔር ፊት መልካም ነገር እንዳደረገ ይተርካል።

ምንም እንኳን አባቱ አብያም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር ያደረገ ቢሆንም፤ ልጅ የአባቱን ክፋት መውረስ የለበትምና፣ ልጁ አሳ በእግዚአብሔር ፊት ቅን የሆነውን ነገር ያደርጋል። «ከአገሩም ሰዶማውያንን አስወግዶ አባቶቹም ያደረጉትን ጣዖታትን ሁሉ አራቀ። በማምለኪያ ዐፀድ ጣዖት ስለ ሠራች እናቱን መዓካን እቴጌ እንዳትሆን ሻራት፤ ጣዖትዋንም ሰበረው፣ በቄድሮንም ፈፋ አጠገብ አቃጠለው» ቁ. 12-13።

የንጉሥ አሳን አካሄድ ከአባቶቹ (አብያም)፣ ሮብዓምና ሰሎሞን አካሄድ ጋር ስናወዳድረው፣ 180 ዲግሪ እንደመመለስ ያህል ነው ምዕ 14፥22-24ትን ማወዳደር።

«ከእኔ ይልቅ እናቱን ወይም አባቱን፤ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም» ብሎ ጌታችን በወንጌል እንዳስጠነቀቀን፤ ንጉሥ አሳ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከእናቱ ፈቃድ ሲያስቀድም እናያለን። እኛም፣ ጌታን ብቻ በሕይወታችን እየሾምን፣ የእርሱን ጌትነት የሚቀናቀነውን ሁሉ (እናት እንኳን ብትሆን) ከሕይወታችን መሻር አለብን።

መቼም ሰው ሥጋ ለባሽ ሆኖ ድካምና ስህተት አይጠፋበትምና፣ ንጉሡ አሳም በሕይወቱ የሠራቸውን ስህተቶች የእግዚአብሔር ቃል ይገልጽልናል። በተለይ ይህንን ክፍል ከ2ዜና 14-16 ጋር አብረን ማየት ይኖርብናል። በ2ዜና ምዕ. 14-16 የምናነበው ክፍል ስለ ንጉሥ አሳ የበለጠ የሚያብራራ ታሪክ ነው። አሁን በምናጠናው ምዕራፍ 1ነገሥት 15 ስለ ንጉሥ አሳ የተጠቀሰውን ሐሳብ በደንብ የሚያብራራውን ክፍል ብቻ ከ2ዜና 16 እንመለከታለን። የቀረውን የንጉሥ አሳን ሰፋ ያለ ታሪክ በ2ዜና መጽሐፍ ጥናት እናየዋለን። በ1ነገ 15 ላይ፤ ሁለት ስለ ንጉሥ አሳ የተጠቀሱ ድክመቶች አሉ። ድክመቶቹ ምን እንደሆኑ ግን የበለጠ የምንረዳው 2ዜና 16ትን ስንመለከት ነው።

የንጉሥ አሳ አንደኛው ስህተት ከቁ. 16-22 1ነገ 15 የተገለጸው ታሪክ ነው። የእስራኤልን ንጉሥ ባኦስ በይሁዳ ላይ በተነሣ ጊዜ፣ አሳ በእግዚአብሔር ከመታመን ይልቅ ከሶርያ ንጉሥ ከወልደ አዴር ጋር የፖለቲካ ድርድር ውስጥ ሲገባ እናያለን። ድርድሩ በሥጋ ዓይን ሲታይ የሠራለት ይመስላል።

«ወልደ አዴርም ለንጉሡ ለአሳ እሺ አለው፤ የሠራዊቱንም አለቆች በእስራኤል ከተሞች ላይ ሰድዶ ... የንፍታሌምንም አገር ሁሉ መታ:: ባኦስም ያንን በሰማ ጊዜ ራማን መሥራት ትቶ በቴርሳ ተቀመጠ» (ቁ 20-21) በ2ዜና 16÷7 የሚከተለውን ቃል እናነባለን፤

«በዚያን ጊዜም ባለ ራዕዩ አናኒ ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ አሳ መጥቶ እንዲህ አለው በሶርያ ንጉሥ ታምነሃልና፣ በአምላክህም በእግዚአብሔር አልታመንህምና ስለዚህ የሶርያ ንጉሥ ጭፍራ ከእጅህ አምልጧል::» ከዚህም ትንቢታዊ መልእክት የተነሣ፤ «አሳም በባለ ራዕዩ ላይ ተቈጣ፤ ስለዚህም ነገር ተቈጥቶአልና በግዞት አኖረው፤ በዚያን ጊዜም አሳ ከሕዝቡ አያሌ ሰዎችን አስጨነቀ» (2ዜና 16÷10)::

የአሳን ሁለተኛ ድክመት ወይም ኃጢአት፤ በ1ነገ 15÷23 «ነገር ግን በሸመገለ ጊዜ እግሮቹ ታመሙ» በማለት አድበስብሶ ቢያልፈውም፤ በ2ዜና 16÷12 «በነገሠም በሠላሳ ዘጠኝ ዓመቱ አሳ እግሩን ታመመ፣ ደዌውም ጸናበት፤ ነገር ግን በታመመ ጊዜ ባለ መድኃኒቶችን እንጂ እግዚአብሔርን አልፈለገም» በማለት በግልጽ አስቀምጦታል:: ያለፉትን የእግዚአብሔር ሰዎች ታሪክ እያነበቡ መፍረድ በጣም ቀላል ነው፤ ነገር ግን እኛስ ስንት ጊዜ፣ በእግዚአብሔር ከመታመን ይልቅ በሶርያ ንጉሥ ታምነናል? ስንት ጊዜ የእግዚአብሔርን መድኃኒትና ፈውስ ከመፈለግ ይልቅ ሌሎች ባለመድኃኒቶችን ፈልገናል?

የእግዚአብሔር ቃል፤ «በገዛ ራስህ ማስተዋል አትደገፍ ነገር ግን ቀኑን ሁሉ እግዚአብሔርን በመፍራት ኑር» የሚለን መታመኛችንና ድጋፋችን እርሱ ብቻ መሆን ስላለበት ነው:: «በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ ርጉም ይሁን ... በእግዚአብሔር የታመነ እምነቱም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ብሩክ ነው» (ኤር 17÷5-7)

በ1ነገ 15÷25-34 ያለው ክፍል የሚናገረው የኢዮርብአም ልጅ ናዳብ እንደነገሠ፣ በእግዚአብሔር ፊት እንደ አባቱ ክፉ እንዳደረገና ባዖስ የሚባል ሰው ተነስቶ ናዳብንና የኢዮርብዓምን ዘር ሁሉ፤ በኢዮርብዓም ላይ እንደተነገረው ትንቢት እንዳጠፋ ነው::

«በሴሎናዊው በአኪያ ልጅ እንደተነገረው እንደ እግዚአብሔር ቃል፣ እስኪያጠፋው ድረስ ከኢዮርብዓም አንድ ትንፋሽ ያለው አላስቀረም» ቁ. 30::

እግዚአብሔር ባኦስን በኢዮርብአም ላይ ቅጣትን ለማምጣት ቢጠቀምበትም፤ ባዖስም፤ በኢዮርብአም መንገድ እስራኤልንም ባሳተበት ኃጢአት ሄደ» (ቁ. 34)::

በእነዚህ ምዕራፎች መካከል፤

Resources Sprit የይሁዳንና የእስራኤልን ነገሥታትና ዘመናቸውን ያዘለ ሠንጠረዥ ማስገባት:: (የጥቅሶቹንም ረድፍ መጨመር) ጥቅሶቹ ዜና መዋዕልንም ይጨምሩ

Filled Life Bible እንዲሁም በእነዚህ ነገሥታት ዘመን የነበሩትን
አዲሱ መደበኛ ትርጉም-ነቢያት ስሞች የያዘ ሌላ ሠንጠረዥ ማዘጋጀት (ጥቅሶቹን መጨመር)

Halleys Bible Hand book-በተጨማሪ እነዚህ ነገሥታት
Vngers Bible Survey etc -በእግዚአብሔር ፊት መልካም ወይም ክፉ እንደነበሩ በአንድ ረድፍ መግለጽ:: (ጥቅሶቹን መጨመር)::

1ነገ ምዕ 16 ይህ ምዕራፍ በይሁዳ ንጉሥ በአሳ ዘመነ መንግሥት (የነገሠው 41 ዓመታት ነው) በእስራኤል ላይ ስለ ተፈራረቁት 6 ነገሥታት የሚተርክ ምዕራፍ ነው:: በምዕ 15 ላይ ያለውን

የኢዮርብዓምን ልጅ ናዳብን (ምዕ 15፥25) ብንጨምር በይሁዳ ንጉሥ በአሳ 41 የንግሥ ዘመናት የተፈራቁት የእስራኤል ነገሥታት 7 ይሆናሉ። እነርሱም፤ ናዳብ፣ ባዖስ፣ ኤላ፣ ዘምሪ፣ ዘንባሪ፣ ታምኒ፣ አክአብ (ያምሪ በአዲሱ መደበኛ ትርጉም) ናቸው።

(ከቁ. 1-7) የባኦስን ጥፋት ነቢዩ ኢዩ ካስተላለፉ በኋላ፤ ከቁ. 8-14 ይህ የትንቢት ቃል በባዖስ ልጅ በኤላ ዘመን ይፈጸማል። ይህንንም ቃል የፈጸመውና የባዖስን ልጅ ኤላን የገደለው ዘምሪ ነው። የነገሠበትም ጊዜ 7 ቀናት ብቻ ነው (ቁ. 15)። ከዘምሪም በኋላ መንግሥቱ ለሁለት ተከፋፍሎ ለጥቂት ዘመናት ታምኒና ዘንበሪ የሚባሉ ነገሥታት በሁለት የእሥራኤል ወገኖች ላይ ነግሠው ነበር። በኋላም፣ ዘንበሪ በረታ፣ ታምኒም ሞተ። ይህ ዘንበሪ የሰማርያን ተራራ የገዛና በተራራው ላይ ከተማ ሠርቶ ከተማይቱን «ሰማርያ» ብሎ የሠየማት ንጉሥ ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰማሪያ የእሥራኤል ዋና ከተማ ሆና እናያለን።

ከዘንበሪም በኋላ ልጁ አክአብ በፋንታው ነገሠ በዚህ ምዕራፍ ጎልቶ የምናየው ነገር ቢኖር፤ በእስራኤል ነገሥታት ዘንድ ክፋት እየባሰና እየከፋ ይሄድ እንደነበረ ነው።

«ዘንበሪም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ፣ ከእርሱም አስቀድሞ ከነበሩት ይልቅ እጅግ ከፋ» (ቁ. 25)

«የዘንበሪም ልጅ አክአብ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ (አባቱን ዘንበሪንም ያጠ ቃልላል)፣ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ። በናባጥም ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄድ ታናሽ ነገር መሰለው፣ የሲዶናውያንንም ንጉሥ የኤትበአልን ልጅ ኤልዛቤልን አገባ፣ ሄዶም በኣልን አመለከ ሰገደለትም። በሰማርያም በሠራው በበኣል ቤት ውስጥ ለበኣል መሠዊያ አቆመ። አክአብም የማምለኪያ ዐፀድ ተከለ፤ አክዓብም ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን የሚያስቆጣውን ነገር አበዛ።» (ቁ. 30-33)

አንዱ ከሌላው የከፋ ነገር ለማድረግ ውድድር ላይ ይመስላሉ።

ይህ የክፋት ጨለማ በእስራኤል ላይ በጣም በጨለመበት ጊዜ፤ ድሮ ፈርሰውና ተቀብረው የነበሩ ክፋቶች እንኳን ከመሬት ሲነሱ /Revived/ ሲሆኑ እናያለን።
«በእርሱም ዘመን የቤቴል ሰው ኢሊኤል ኢያሪኮን ሠራ፤ በነዌም ልጅ በኢያሱ እጅ እንደተነገረው እንደ እግዚአብሔር ቃል (ኢያሱ 6፥26) በበኩር ልጁ በአቢሮን መሠረትዋን አደረገ፣ በታናሹ ልጅም በሠጉብ በሮችዋን አቆመ» (ቁ. 34)። የክፋት መነቃቃት /Evil Revival/ ነበረ።

በዚህ በድቅድቅ ጨለማ ዘመን ነው፤ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ምናልባት የነቢያት አውራ የነበረው ታላቁ ነቢይ አልያስ የተነሳው።
ምዕ. 17፡ - ይህ ምዕራፍ የነቢዩ የኤልያስን አገልግሎት ታሪክ የሚጀምር ምዕራፍ ነው።

በምዕ 16 እንዳየነው በንጉሥ አክአብ ዘመን፤ ኃጢአት፣ ክፋትና ባዕድ አምልኮ እንደ ድቅድቅ ጨለማ በነበረበት ዘመን፣ እግዚአብሔር ታላቁን ነቢይ ኤልያስን ወደ አክአብ ይልካል።
አልያስም አክአብን፤ «በፊቱ የቆምሁት የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን፤ ከአፌ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም አለው» (ቁ.1)። ይህንን የእግዚአብሔርን ቃል ካስተላለፈ በኋላ፣ «የእግዚአብሔርም ቃል እንዲህ ሲል ለእርሱ መጣለት፡ - ከዚህ ተነሥተህ ወደ ምሥራቅ ሂድ በዮርዳኖስም ትይዩ ባለው በኮራት ፈፋ ውስጥ ተሸሸግ። ከወንዙም ትጠጣለህ፣ ቁራዎቹም በዚያ ይመግቡህ ዘንድ አዝዣለሁ» (ቁ. 2-4)።

በመጀመሪያ ላይ ያስተላለፈው የእግዚአብሔር ቃል ለአክአብና ለእሥራኤል ሁሉ የሚሆን የእግዚአብሔርን ተግሣጽና ቅጣትን ያዘለ ቃል ነበረ፡፡ በኋላም የመጣለት ቃል ግን «ለእርሱ ለራሱ» የሚሆን መመሪያ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሕይወታችን ለተለያዩ ዓላማዎች እንደሚመጣ ያሳየናል፡፡ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለሌሎች እናስተላልፍ ዘንድ ቃልን (መልእክትን) ወደ ልባችን ያመጣል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ለራሳችን የሚሆንን ቃል ይናገረናል፡፡ ሁለቱን ለይቶ ማወቅና በአግባቡ ማስተናገድ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሌሎች እናስተላልፍ ዘንድ የሰጠንን መልእክት በውስጣችን አምቆ ማስቀረት ወንጀል ነው፤ ተጠያቂነትም አለበት (ሕዝ 3፥16-18)፡፡ በአንጻሩ ደግሞ፤ እግዚአብሔር ለግላችን የተናገረንን ቃል ለሌሎች ማወጅ አላስፈላጊ የሆነ ጉዳትና ስደት ሊያመጣብን ይችላል፡፡ በወንጌል ውስጥ፤ ቅድስት ማርያም ስለ ህፃኑ ክርስቶስ የተነገረውን ሁሉ «በልቧ» ትጠብቀው ነበር ይለናል፡፡

ነቢዩ ኤልያስ፤ «ሄደህ በፈፋ ውስጥ ተሸሸግ» ከተባለ በኋላ፤ በዚያ ስፍራ ቁራዎች ይመግቡት እንደነበረ እናነባለን፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ስናይ «ቁራ» በጥፋት ውኃ ዘመን፣ ውሃው ከምድር ላይ መጉደሉን ለማወቅ ኖኅ በመጀመሪያ የላካትና ሳትመለስ የቀረች ወፍ ናት፡፡ ይህንንም አስመልክቶ በአገራችን «የቁራ መልእክተኛ» የሚባል አባባል ተፈጥሮላት ስሟ የጎደፈ ወፍ ናት፡፡ እግዚአብሔር ግን ነቢዩን ትመግብ ዘንድ ይህችን ወፍ መራ ፡፡ ቁራ፣ በተፈጥሮዋ፣ ሥጋን በአፏ ከያዘች፤ ወደ ውስጥ መዋጥ እንጂ፤ አሳልፋ ለሌላ ፍጥረት ማስተላለፍ ከተፈጥሮዋ በላይ /Super natural/ ነው፡፡ የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ የሆነ እግዚአብሔር አምላክ ሲያዝ ግን የማይታዘዝ ማን አለ? ቁራዎቹ ኤልያስን ከተፈጥሮአቸው ውጭ በሆነ መንገድ ይመግቡት የነበሩት በእግዚአብሔር በፈጣሪአቸው ታዘው ስለነበረ ነው፡፡

«ቁራዎችም በዚያ ይመግቡህ ዘንድ አዝዣለሁ» (ቁ 4)፡፡
በምዕ 13 ላይ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የተላለፈውን ነቢይ እንደ ገደለው አንበሳ እነዚህ ቁራዎችም እግዚአብሔርን ሲታዘዙ ነው የምናየው፡፡

ነቢዩ ኤልያስ የሚበላውን ምግብ ተዓምራዊ በሆነ መንገድ ቢያገኝም፤ የሚጠጣውን ውኃ ግን ከወንዙ ወርዶ  ይጠጣ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በተዓምር አያደርግልንም፡፡ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ማግኘት የምንችለውን ነገር በተፈጥሮአዊ መንገድ እንድናገኝ ፈቃዱ ነው፡፡ በተፈጥሮአዊ መንገድ ለማግኘት ከአቅማችን በላይ የሆነውን ነገር ተዓምራዊ በሆነ አሠራሩ ያደርግልናል፡፡

ወንዙ በደረቀ ጊዜ (ተፈጥሮአዊው አቅም ሲያልቅ) እግዚአብሔር ኤልያስን ወደ አንዲት ድሃ መበለት ይልከዋል፡፡ በዚህም ክፍል የእግዚአብሔር ምርጫ የሚያስገርም ነው፡፡ ባለጠጋ ወደሆኑ፣ ማድጋቸውና ማሰሮአቸው ወደ ሞላ ሰዎች ሊልከው ይችል ነበረ፡፡ ወደ እነዚህ ሰዎች ቢልከው ክብርና ምሥጋናው ለእነርሱ ሊሆን ነው፡፡ እግዚአብሔር የላከው ግን ወደ አንዲት፤ ማድጋዋ እፍኝ ዱቄት ብቻ ወደ ቀረው፤ ማሰሮዋም እላቂ ዘይት ወደ ቀረው፣ መበለት ነበረ፡፡ በተጨማሪም፣ ይህች መበለት እሥራኤላዊ፣ ማለትም በአብርሃም ቃል ኪዳን ውስጥ የነበረች ሴት አይደለችም፡፡ አገርዋ፣ ኤልዛቤል የመጣችበት አገር ነው (16፥31)፡፡ የበኣል አምልኮ መዲና የነበረች አገር ናት፡፡

ጌታ ኢየሱስ በሉቃ 4፥25-26 «ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፣ በኤልያስ ዘመን ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ሰማይ ተዘግቶ ሳለ በምድር ሁሉ ብርቱ ራብ በነበረ ጊዜ በእስራኤል ብዙ መበለቶች ነበሩ፤ ኤልያስም በሲዶና አገር ወዳለች ወደ ሰራፕታ ወደ አንዲት መበለት እንጂ ከእነርሱ ወደ አንዲቱ አልተላከም» በማለት እግዚአብሔር አሕዛብ የነበረችይቱን መበለት እንደመረጠ ያስተምረናል፡፡ ይህም የሆነው እስራኤል ሁሉ ከእግዚአብሔር ርቀው በባዕድ አምልኮ ውስጥ ስለነበሩ ነው፡፡

ይህች መበለት፣ ምንም አሕዛብ ብትሆንም በባልዋ የእሥራኤልን አምላክ በመጠኑም ቢሆን የምታውቅ እንደነበረች ከቁ. 12 እንረዳለን። «እርስዋም፣ አምላክህ ሕያው እግዚአብሔርን በማድጋ ካለው ከእፍኝ ዱቄት፣ በማሰሮውም ካለው ከጥቂት ዘይት በቀር እንጀራ የለኝም ...» ይህች መበለት ለኤልያስ ስትመልስ «በሕያው እግዚአብሔር» እንደማለች ማየት እንችላለን። ከአፍ የሚወጣው ከልብ ሞልቶ የተረፈው ስለሆነ፤ በዚህች መበለት ልብ ውስጥ «የሕያው እግዚአብሔር» እውቀት ባይኖር ኖሮ በአፍዋ መሐላ ሆኖ ባልወጣም ነበር።

በሐዋ ሥራ 10÷34-35 ላይ ጴጥሮስ፤ አሕዛብ ወደሆነው ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ገብቶ ንግግሩን የጀመረበትን ቃል ስንመለከት ለዚህች መበለትም አግባብ የሆነ ቃል እንደሆነ ለማየት እንችላለን። «እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያደላ ነገር ግን፣ <u>በአሕዛብ ሁሉ</u> እርሱን የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደ ሆነ በእውነት አስተዋልሁ»

እግዚአብሔር ኤልያስን ወደዚህች መበለት የላከው እርሱን እንድትመግብ ብቻ ሳይሆን እርሷንም ሊጎበኛት፣ ከሞት ሊታደጋት ስለወደደ ነው። «እነሆም ገብቼ ለእኔና ለልጄ እጋግረው ዘንድ <u>በልተነውም እንሞት</u> ዘንድ ጥቂት እንጨት እሰበስባለሁ አለች» (ቁ. 12)። ለሞት አንድ እርምጃ ወይም አንድ ጉርሻ የቀራት መበለት ነበረች፤ እግዚአብሔር ግን ሊታደጋት ወደደ።

«ኤልያስም አላት፡- አትፍሪ ይልቅስ ሄደሽ እንዳልሽው አድርጊ፤ <u>አስቀድመሽ</u> ግን ከዱቄቱ ለእኔ ታናሽ እንጎቻ አድርጊልኝ፣ ከዚያም በኋላ ለአንቺና ለልጅሽ አድርጊ፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፡- በምድር ላይ እግዚአብሔር ዝናብ እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ፣ ዱቄቱ ከማድጋ አይጨረስም ዘይቱም ከማሰሮው አይጎድልም» ቁ. 13-14። የኤልያስን ቃል ስንመለከት፤ እግዚአብሔር አዞትና መርቶት ባይናገር ኖሮ «ምን ዓይነት ሆዳም ነቢይ ነው?» የሚያስብል ቃል ነው የሚናገራት። «አስቀድመሽ ግን ከዱቄቱ ለእኔ ታናሽ እንጎቻ አድርገሽ አምጭልኝ» በውስጡ ግን ትልቅ መንፈሳዊ የሆነ ምስጢር አለበት። እርስዋ «በልተነው እንሞት ዘንድ» ብላ የነበረውን እፍኝ ዱቄትና ጥቂት ዘይት፤ ኤልያስ በእግዚአብሔር ምሪት «አስቀድመሽ ለእኔ» ይላታል። «ትመግብህ ዘንድ አንዲት ባልቴት አዝዣለሁ» (ቁ. 9)፤ የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል ስለሚያውቅ፤ «አስቀድመሽ <u>የእግዚአብሔርን ትእዛዝ</u> ፈጽሚ ማለቱ ነው። አስቀድማ እርሱን በመመገብዋ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መታዘዟንና እግዚአብሔርን መታመኗን ታሳያለች። የነበራት ምርጫ ሁለት ነበር። የመጨረሻውን እንጀራ ከልጅዋ ጋር በልታ መሞት ወይም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ታዝዛ በሕይወት መኖር። የመጀመሪያውን ምርጫ ብታደርግ፤ መዘራት የነበረበትን ዘር እንደመብላት ይሆንባት ነበር አሁን ግን እግዚአብሔር ባዘዛት መሠረት ያቺን የመጨረሻ ዘር ስለዘራቻት ብዙ ፍሬ ሆኖላት የድርቁን ዘመን ማለፍ ቻለች። «እንደ እግዚአብሔር ቃል ዱቄቱ ከማድጋው አልተጨረሰም፤ ዘይቱም ከማሰሮው አልጎደለም» (ቁ. 16)።

ከቁ 17-24 ያለው ታሪክ፣ ትንሽ ለየት ያለ መልክ የያዘ ነው። በዚህ፤ የእግዚአብሔር ረድኤትና በረከት በተትረፈረፈበት ቤት፤ የእግዚአብሔር ተዓምራዊና አስደናቂ አሠራር በየዕለቱ በሚታይበት ቤት፤ ሕመምና ሞት በር አንኳኩቶ ወይም ሳያንኳኳ ሲገባ እናነባለን። «ከዚያም በኋላ የባለቤቲቱ ልጅ ታመመ ትንፋሹም እስኪታጣ ድረስ ደዌው እጅግ ከባድ ነበረ» (ቁ. 17)። እዚህ ጋ ቆም ብለን፤ እንደዚህ ያለ ነገር ለምን ይሆናል ብለን ብንጠይቅ፤ ከዔድን ገነት ዘፍ. 3 ጀምሮ የነበረ ሲሆን፤ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መጥቶ የዘላለምን መንግሥት እስከሚመሠርትበትና «ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፣ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም» (ራእይ 21÷4) የሚለው ቃል እስከሚፈጽምበት ቀን ድረስ ከእኛ ጋር የሚኖር እውነታ ነው።

«በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ» ብሎ ጌታ እንደነገረን፤ የመከራ ጉብኝት አይቀሬ ነው:: ይህ ነገር ለምን ይሆናል እያልን ግድግዳን ከመግፋት ይልቅ፤ እኛ መጠየቅ ያለብን ጥያቄ «በዚህ ነገር ውስጥ የእግዚአብሔር ሐሳብና ዓላማ ምንድነው?» የሚል መሆን አለበት:: በምናልፍበት ነገር ሁሉ፤ የእግዚአብሔር ሐሳብና ዓላማ ለመረዳት ከጣርን፤ በአንጻሩ ደግሞ የጠላታችን የዲያብሎስ ሐሳብ ምን እንደሆነ ካልሳትን፤ «የእርሱን ሐሳብ አንስተውምና» ተብሎ እንደ ተጻፈ በምናልፍበት ማንኛውም ነገር አትራፊዎች (ድል ነሺዎች) እንጂ ከሳሪዎች (ተሸናፊዎች) አይሆንም::

እግዚአብሔር ጠላታችን ዲያብሎስ እንዲፈትነንና መከራ እንዲያመጣብን (እንደ አቅማችን መጠን) ቢፈቅድለትም፤ በዚያ ነገር እንሸነፍ ዘንድ ፈቃዱ አይደለም:: ጠላትን የምናሸንፍበትን ኃይል፣ ጸጋ፣ ምሕረት፣ ቸርነት፣ ወዘተ ... ሰጥቶን ነው፤ ጠላት እንዲፈትነን፣ እንዲያጠቃን የሚፈቅድለት:: «እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ» ዘፍ. 3÷5 ብሎ እግዚአብሔር ለእባብ ለዲያብሎስ እንደተናገረው የጌታንም ቢሆን ሰኮና ቀጥቅጧል:: ጌታ ግን የዲያብሎስን ራስ ሥልጣን ነው የቀጠቀጠው (ያፈራረሰው):: እኛም በክርስቶስ ስም የተጠራን የእርሱ አካል ስለሆንን ይህ ሥልጣን ተሰጥቶናል ሉቃ 10÷19፤ ኤፌ. 1÷18-23:: እኛ ራሱን ስንቀጠቅጥ እርሱ ሰኮናችንን መቀጥቀጡ ግን፣ በዓለም ሳለን መታገስ ከሚገባን መከራ ውስጥ የሚከተት ነው::

ወደ ኤልያስና መበለቲቱ ታሪክ ብንመለስ፤ ይህ፣ የመበለቲቱ ልጅ መሞት ወደዚህ ቤት ሲመጣ፤ የመበለቲቱንም ሆነ የኤልያስን ምላሽ /Reaction/ እንመልከት::

«እርስዋም ኤልያስን፡- የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለን? ኃጢአቴንስ ታሳስብ ዘንድ ልጄንስ ትገድል ዘንድ ወደ እኔ መጥተሃልን? አለችው» ቁ 18::

«ኤልያስ ልጅሽን ስጪኝ አላት:: ... ወደ እግዚአብሔርም አቤቱ አምላኬ ሆይ፣ ልጅዋን በመግደልህ፣ ይህችን ትቀልበኝ የነበረችይቱን ባልቴት እንዲህ ደግሞ አስጨነቅኻትን? ብሎ ጮኸ ቁ. 20 የመበለቲቱም ሆነ የኤልያስ ምላሽ /Reaction/ ትክክለኛ ያልሆነ ክስ እንደነበረ መረዳት እንችላለን:: እርስዋ፤ «ኃጢአቴን ለእግዚአብሔር እያሳሰብክ /እየሰበቅህ/ ልጄን አስገደልክብኝ» ነው ያለችው:: ይህ አባባሏ የተሳሳተ ክስ እንደነበረ መረዳት አያዳግትም ከእርሷ ምላሽ ይልቅ የሚገርመው ግን የኤልያስ የመጀመሪያው ምላሽ ነው:: ኤልያስም፤ ምንም የእግዚአብሔር ነቢይ ቢሆንም፤ የእግዚአብሔር በያዕ 5÷17 «እንደ እኛ ሰው ነበረ» ብሎ እንደሚነግረን፤ እግዚአብሔርን በመክሰስ ሲጸልይ (ወደ እግዚአብሔር ሲጮኽ) ነው የምናየው:: «ልጅዋን በመግደልህ ... አስጨነቅኻትን? ብሎ ጮኸ»:: ከዚህ በላይ ውንጀላና ክስ ምን አለ? እግዚአብሔርን ነፍሰ ገዳይና አስጨናቂ ነህ እያለው ነው:: ይህንን የተዛባና የተሳሳተ መስመር የለቀቀ ጸሎት ከጸለየ በኋላ ወደ ልጁ ቢመለከት አሁንም ምንም እስትንፋስ የለውም:: በዘረጋበት ይነሣል ብሎ ሦስት ጊዜ ቢዘረጋበትም ምንም እንቅስቃሴ የለም:: ጸሎቱ የተዛባ ስለነበረ ምንም መልስ ሊያገኝ አልቻለም:: እግዚአብሔር የሚመልሰው ጸሎት «እንደ ፈቃዱና እንደ ሐሳቡ» የሆነውን ጸሎት ብቻ ስለሆነ 1ዮሐ. 5÷14 እግዚአብሔርን እየከሰሰ የጸለየው ጸሎት ምንም ምላሽ አጣ:: እንደገና ጸሎቱን አስተካክሎ መጸለይ ነበረበት:: በቁ. 21 ላይ እንዲህ ብሎ ለሁለተኛ ጊዜ ይጸልያል «አቤቱ አምላኬ ሆይ የዚህ ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ ብሎ ጮኸ» ይህ ጸሎት ምንም ክስ የሌለበት፣ መስመር ያልለቀቀ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ የነበረ ጸሎት ነው:: ከዚህኛው ጸሎት በኋላ «እግዚአብሔርም የኤልያስን ቃል ሰማ፣ የብላቴናው ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች፣ እርሱም ዳነ» ቁ. 22::

ይህንን ክፍል በአጠቃላይ ስንመለከት፣ እግዚአብሔር ከጅምሩ፤ በዚህ በረከት ረድኤትና ተዓምር በተመላበት ቤት ሞት ብቅ እንዲል የፈቀደው፤ የመጀመሪያውን የትንሣኤ ተዓምር

በኤልያስና በመበለቲቱ ሕይወት ሊሠራ ወዶ ነው። ነገር ግን መበለቲቱም ሆነ ኤልያስ በመጀመሪያ ይህንን አልተረዱም ነበር።

«ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላችሁ እንዲበዛላችሁ መጣሁ» (ዮሐ. 10÷10)።
1ነገ. ምዕ. 18

ይህ ምዕራፍ፤ ከሦስቱ የድርቅ ዓመታት በኋላ ኤልያስ ለአክአብ እንደተገለጠ፤ የበኣልን ነቢያት ሁሉ እንዲጠራ አድርጎ በቀርሜሎስ ተራራ «በእሳት የሚመልስ አምላክ እርሱ አምላክ ይሁን» በማለት የእግዚአብሔርን ሕያውነት እንዳስመሰከረና የበኣልን ነቢያት በቂሶን ወንዝ እንዳሳረዳቸው፤ እንዲሁም ሰማያት ተከፍተው ዝናብ እንደዘነበ የሚተርክ ድንቅ ምዕራፍ ነው።

ከቁ. 1-19 የምናየው፤ ኤልያስ፣ አብድዩ በሚባል እግዚአብሔርን እጅግ በሚፈራ የአክአብ ቤት አዛዥ በኩል ለአክአብ እንደተገለጠ ነው።

በዚህ ክፍል ውስጥ ያለውን የአብድዩን ታሪክ ስናነብ አስደናቂ የሆነ ትምህርትና የእግዚአብሔርን አሠራር እናስተውላለን።

ቁ. 3 «አክአብም የቤቱን አዛዥ አብድዩን ጠራ፤ አብድዩ እግዚአብሔርን እጅግ ይፈራ ነበር።» የእግዚአብሔር ቃል ስለ አክአብ የሚናገረውን ቃል ስንመለከት፣ እግዚአብሔርን እጅግ የሚዳፈር ንጉሥ እንደነበረ ማስተዋል እንችላለን። 1ነገ 16÷29-34፤ 1ነገ 20÷25። ታዲያ፣ የዚህ እጅግ የከፋ ንጉሥ የቤቱ አዛዥ «እግዚአብሔርን እጅግ የሚፈራ» ሰው መሆኑ የሚያስገርም ነው። በዚያ በክፋትና በአመጽ በተሞላ ቤት ውስጥ እግዚአብሔር አብድዩን ለራሱ ዓላማ አስቀምጦት ነበር። አብድዩ፣ በድቅድቅ ጨለማ እንደሚበራ መብራት ነበር። «ኤልዛቤልም የእግዚአብሔርን ነቢያት ባስገደለች ጊዜ እርሱ መቶውን ነቢያት ወስዶ አምሳ አምሳውን በዋሻ ውስጥ ሸሽጎ እንጀራና ውሃ ይመግባቸው ነበር። (ቁ. 4) ይህ ድርጊቱ ምን ያህል እምነትና ድፍረት እንደሚጠይቅ መገመት ይቻላል። አብድዩ የአክአብ ቤት አዛዥ ነበረ፤ ሲል በዘመኑ ቋንቋ ከአገሩ መሪ ቀጥሎ ሁለተኛ ሥልጣን የነበረው ታላቅ የመንግሥት ባለሥልጣን ነበረ ማለት ነው።

በክርስቲያኖች አካባቢ፣ በመንግሥት ወይም በፖለቲካው ዓለም ምንም ተሳትፎ ሊኖረን እንደማያስፈልግ የሚመስልበት ሁኔታ አለ። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብ ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች በመንግሥታት ሥልጣን ውስጥ ታላቅ ሚና እንደተጫወቱና እግዚአብሔርን በዚህ መስክ እንዳስከበሩ እናያለን። ለምሳሌ ያህል፤ ዮሴፍ፣ ዳንኤል፣ አስቴር፣ ነህምያ ወዘተ ... መጥቀስ ይቻላል። አብድዩም በዚህ ምዕራፍ ይህንኑ ሚና ሲጫወት ነው የምናየው። ቤተ ክርስቲያንም ይህንን አስተውላ፣ ይህ ጸጋ የተሰጣቸውን ወንድሞችና እህቶች ባሉበት ጸንተው እግዚአብሔርን እንዲያስከብሩ ማበረታታት አለበት። መንፈሳዊ አገልግሎት፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ የምንሰጠው አገልግሎት ብቻ ሳይሆን፤ እግዚአብሔር ባስቀመጠን ስፍራ ሁሉ የእግዚአብሔርን ሐሳብ በታማኝነት ማገልገላችን ነው።

ከዚህ ክፍል ሌላ የምንማረው ነገር፤ እግዚአብሔር ከሸሸን ማንም ሊያገኝን እንደማይችል ነው።

ኤልያስ አብድዩን ለአክአብ እገለጣለሁና ሄደህ ንገረው ሲለው፤ «አምላክህ ሕያው እግዚአብሔርን ጌታዬ ይፈልግህ ዘንድ ያልላከበት ሕዝብ ወይም መንግሥት የለም፤ ሁሉም፣ በዚህ የለም ባሉ ጊዜ አንተን እንዳላገኙ መንግሥቱንና ሕዝቡን አምሎአቸው ነበር» (ቁ. 10) ብሎ ይመልስለታል። እግዚአብሔር እውነተኛ መሸሸጊያና ከለላ ነው።

ከቁ. 20-40 ያለው ክፍል የኤልያስንና የበኣል ነቢያትን ፍልሚያ ያሳያል። ኤልያስ አክአብን፣ እስራኤልንና የበኣል ነቢያትን እንዲሰበስብ ካዘዘው በኋላ፣ ሕዝቡን «እስከ መቼ በሁለት ሐሳብ ታንከሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ፤ በኣል ግን አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ» ይላቸዋል (ቁ. 21)።

ይህ ቃል እግዚአብሔርን በግማሽ ልብ ለሚከተል ወይም ለሚያመልክ ሰው ሁሉ የሚሆን የምክር ቃል ነው። ጌታም በአዲስ ኪዳን «ለሁለት ጌቶች መገዛት አትችሉም» (ማቴ. 6፥24) በማለት ያስተምረናል። እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ በሙሉ ልብ እንዳናመልከው ልባችንን በመክፈል በሐሳባችን እንድናነክስ ያደረገን ነገር ምን ይሆን? ገንዘብ፣ ኃጢአት፣ እውቀት፣ ሥልጣን፣ ትዕቢት ወዘተ ...? ኤልያስ ይህንን ጥያቄ ለሕዝቡ ካቀረበ በኋላ ከበኣል ነቢያት ጋር ይወራረዳል።

«እናንተም የአምላካችሁን ስም ጥሩ፣ እኔም የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ፣ ሰምቶም በእሳት የሚመልስ አምላክ፣ እርሱ አምላክ ይሁን። ሕዝቡም ሁሉ ይህ ነገር መልካም ነው ብለው መለሱ» (ቁ. 24)። አንድ የእግዚአብሔር ጀግና በብዙ መቶ ከሚቆጠሩ የሐሰት ነቢያት ጋራ ፊት ለፊት ይጋፈጣል። እንደውም፤ ያላግጥባቸዋል የበኣል ነቢያት፣ በኣል እሳት አውርዶ መሥዋዕታቸውን እንዲበላ ሲጮኹ፤ «ኤልያስ፦ አምላክ ነውና በታላቅ ቃል ጩኹ ምናልባት አሳብ ይዞታል፣ ወይም ፈቀቅ ብሏል፣ ወይም ወደ መንገድ ሄዷል፣ ወይም ተኝቶ እንደሆነ መቀስቀስ ያስፈልገዋል እያለ <u>አላገጠባቸው</u>» ቁ. 27።

እነርሱም ቀኑን ሙሉ መከራቸውን አይተው ወደ በኣል ከጮኹ በኋላ፣... ድምፅም አልነበረም፣ የሚመልስና የሚያደምጥም አልነበረም ቁ. 29።

የኤልያስ ተራ በደረሰ ጊዜ «ፈርሶ የነበረውን የእግዚአብሔርን መሠዊያ አበጀ .. እንደ ያዕቆብ ልጆች ነገድ ቁጥር አሥራ ሁለቱን ድንጋዮች ወሰደ። ከድንጋዮቹም ለእግዚአብሔር ስም መሠዊያ ሠራ» (ቁ. 30-31)። ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ከመሠዋታችን በፊት መሰዊያው መታደስ አለበት። እግዚአብሔር በፈረሰ መሰዊያ ላይ የሚቀርብን መስዋዕት አይቀበልም። መሥዋዕቱ፣ ጸሎታችን፣ አምልኮአችን፣ ስጦታችን ወዘተ ... ነው፤ መሠዊያው ግን ሕይወታችን ልባችን፣ አእምሮአችን ነው። ልባችንና አእምሮአችን በኃጢአት፣ በክፉ ሐሳብ፣ ይቅር ባለማለት ወዘተ ... ተሞልቶ ለእግዚአብሔር መስዋዕትን ማቅረብ አንችልም። በመጀመሪያ ሕይወታችንን ራሱን እንደ መስዋዕት ማቅረብ አለብን። «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ ሰውነታችሁን፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው፣ ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ፤ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ» (ሮሜ 12፥1) የፈረሰውን መሠዊያ ከሠራ በኋላ በመሠዊያው ላይ ወይፈኑን አኖረና 12 ጋን ሙሉ ውሃ በመሥዋዕቱና በመሠዊያው ላይ በማፍሰስ ዙሪያው ሁሉ በውኃ እስኪሞላ አደረገ። ይህም፤ የእግዚአብሔር መልስ ስትመጣ ከእግዚአብሔር ለመሆኑ ምንም ዓይነት ጥርጥር እንዳይኖር ነው። እግዚአብሔር ጸሎቱን ሲመልስ ከእኛ ምንም ዓይነት እርዳታ አያስፈልገውም «ብቻውን» ተዓምራት ማድረግ የሚችል አምላክ ነው።

ይህንን ሁሉ ካደረገ በኋላ፤ ኤልያስ አጭር ጸሎት ያደርጋል፤ «አቤቱ የአብርሃምና የይስሐቅ የእስራኤልም አምላክ ሆይ፣ አንተ በእስራኤል ላይ አምላክ እንደሆንክ፣ እኔም ባሪያህ እንደሆንሁ፣ ይህንም ሁሉ በቃልህ እንዳደረግሁ ዛሬ ይገለጥ» ቁ. 36። ኤልያስ ያደረገው ነገር ሁሉ፤ ከእግዚአብሔር እንደመጣለት ቃል እንደሆነ በጸሎቱ ውስጥ ያረጋግጣል። ኤልያስ፣ በራሱ ሥጋዊ ድፍረቱ ተነሳስቶ ያደረገው ነገር አልነበረም። ድፍረቱ ከእግዚአብሔር ቃል የመነጨ ነበር። በእግዚአብሔር ቤት ስንመላለስ ለምናደርገው ነገር ሁሉ ምንጩ ማን እንደሆነ መመርመር ጥሩ ነው። አንዳንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ሳንሰማ በሥጋ ድፍረት መሸምጠጥ እንችላለን። ለዚያም ዋጋ የምንከፍለው ራሳችን ነን፤ እግረ መንገዳችንን ግን ብዙ ነገር

ለማጥፋት እንችላለን። ኤልያስ ጸሎቱን ከጨረሰ በኋላ «የእግዚአብሔር እሳት ወደቀች የሚቃጠለውን መስዋዕቱንም፣ እንጨቱንም፣ ድንጋዮቹንም፣ አፈሩንም በላች፣ በጉድጓዱም ውስጥ ያለውን ውኃ ላሰች» (ቁ. 38)። «ሕዝቡም ሁሉ ያንን ባዩ ጊዜ፤ በግምባራቸው ተደፍተው፡- እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው አሉ» (ቁ. 39)።

«ኤልያስም፡- ከበአል ነቢያት አንድ ሰው እንዳያመልጥ ያዙ አላቸው። ያዙአቸውም፤ ኤልያስም ወደ ቂሶን ወንዝ ወስዶ በዚያ አሳረዳቸው» ቁ. 40።

ባዕድ አምልኮና ጨለማ በሰፈነበት ዘመን፣ እግዚአብሔር አንድ ታማኝ ባሪያ አገኘ፣ ክብሩንና ማዳኑንም ገለጸ። እኛም እያንዳንዳችን በዚህች በክፉው ቁጥጥር ሥር ባለች በጨለማ ዓለም ነው የምንኖረው። እያንዳንዳችን የምንኖርበትን አካባቢ በክርስቶስ ኢየሱስ የወንጌል ብርሃን የማብራት ኃላፊነት አለብን። ክፉውን ማሸነፍና በክፉው የተያዙትን፤ ከክርስቶስ ባገኘነው ሥልጣን፣ ነጻ ማውጣት አለብን።

«እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» ማቴ 5÷14
«ወደ ሞት የሚነዱትን ታደግ ሊታረዱ የተወሰኑትን አድን» ምሳሌ 24÷11
«አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ» ይሁዳ 23

ከቁ. 41-45 ያለው ክፍል፤ ከአንድ፣ የሰው እጅ የምታህል ደመና፣ ብዙ ዝናብ እንደዘነበ ይገልጻል። ኤልያስ «ፊቱን በጉልበቱ መካከል አድርጎ በግምባሩ ተደፋ። ብላቴናውንም፡- ወጥተህ ወደ ባህሩ ተመልከት አለው። ወጥቶም ተመልክቶም፡- ምንም የለም አለ። እርሱም፡- ሰባት ጊዜ ተመላለስ አለው። ብላቴናውም ሰባት ጊዜ ተመላለሰ። በሰባተኛውም ጊዜ፡- እነሆ የሰው እጅ የምታህል ታናሽ ደመና ከባሕር ወጣች አለ።» ቁ. 42-43 ከእግዚአብሔር ዘንድ መገለጥ ያለው የጸሎት ሰው «ምንም የለም» በሚል መልስ አይበገርም። በቁ. 1 ላይ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለኤልያስ «በምድር ላይ ዝናብ እሰጣለሁ» ብሎ ተናግሮት ስለነበረ፤ ኤልያስ በሚታየው ወይም በማይታየው ነገር ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ነበር ያተኮረው። የእግዚአብሔር ቃል ዕውን እስከሚሆን ድረስ ብላቴናው እንዲመላለስ አደረገው። በሰባተኛው ጊዜ «ታናሽ ደመና ከባሕር ወጣች» ሲለው ዝናቡ ገና ሳይወርድ ዝናብ መዝነቡን አወጀ።

እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ቃሉን ከሰጠ ማተኮር ያለብን ቃሉ ላይ ነው እንጂ ሁኔታዎች ላይ አይደለም። በቃሉ ላይ ባለን እምነት እንጂ በማየት መመላለስ የለብንም።

## ምዕራፍ 19

ይህ ምዕራፍ ካለፈው ጋር ስናስተያየው በጣም የሚያስገርም ተቃርኖ /Contrast/ አለው። በምዕ. 18 ላይ የምናየው ኤልያስና በዚህ ምዕራፍ የምናየው ኤልያስ ያው ሰው መሆኑንም ያጠራጥራል። በምዕ. 18 የምናየው ኤልያስ «እንደ አንበሳ ያለ ፍርሃት» የሚንጎራደድ፣ በአምላኩ የሚወራረድ፣ ብዙ በነበሩት የጠላቶቹ ነቢያት ላይ የሚያላግጥ ጀግና ነበረ። በዚህ ምዕራፍ ግን የአንዲትን ሴት ዛቻ ሰምቶ እግሬ አውጪኝ ብሎ የፈረጠጠ፣ እግዚአብሔርን «... ይበቃኛል.. ነፍሴን ውሰድ» ብሎ የለመነ ፈሪ ሰውን ነው የምንመለከተው። የእነዚህ ሁለት ምዕራፎች ይህንን ያህል መለያየት መንስኤው ምንድነው ብለን ብንመረምር፤ የልዩነቱን ምስጢርና ትልቅ ትምህርት እናገኝበታለን። የልዩነቱን ምክንያት የምናገኘው፤ የሁለቱን ምዕራፎች አጀማመር ስንመለከት ነው።

ምዕ 18 የሚጀምረው «... ሂድ፣ ለአክአብ ተገለጥ፣ በምድር ላይም ዝናብ እሰጣለሁ፤ የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤልያስ መጣ» ቁ. 1 በሚል ቃል ሲሆን፤

ምዕ. 19 ደግሞ «ኤልዛቤልም፡- ነገ በዚህ ጊዜ ነፍስህን ከእነዚህ እንደ አንዲቱ ነፍስ ባላደርጋት፣ አማልክት ይህን ያድርጉብኝ፣ ይህንም ይጨምሩብኝ ብላ ወደ ኤልያስ መልእክተኛ ላከች» (ቁ. 2) በሚል የዛቻ ቃል ነው።

የሁለቱን ምዕራፎች የጅማሬ ቃሎች ስናስተያይ፣ አንደኛው ከእግዚአብሔር ወደ ኤልያስ የመጣለት የእግዚአብሔር ቃል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በኤልዛቤል በኩል ከሰይጣን የመጣበት የማስፈራራት ቃል ነው።

የእግዚአብሔር ቃል በሮሜ 10፥17 «እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» እንደሚል፣ በምዕ. 18 ወደ ኤልያስ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል፤ እምነትና ድፍረት ሆኖ ያንን ሁሉ ገድል ሲያደርግ ተመልክተናል። በምዕ. 19 ላይ ግን፤ የመጣበትን የጠላት ዛቻ ስለ ሰማና በልቡ ስፍራ ስለሰጠው፤ ይህ የጠላት ዛቻ «ፍርሃትንና መኮብለልን» ሲያመጣበት እናያለን። የጠላትን ቃል መስማትና በልባችን ስፍራ መስጠት ፍርሃትንና መኮብለልን እንደሚያመጣ ጥሩ ማስረጃ ነው። የእግዚአብሔር ቃል፤ በያዕ. 5፥17 «ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበር» የሚለው የበለጠ ትርጉም የሚሰጠን ምዕ. 19ኝን ስንመለከት ነው።

«ኤልያስም ፈርቶ ተነሣ፣ ነፍሱንም ሊያድን ሄደ» (ቁ. 3)። ከዚያም የአንድ ቀን መንገድ ያህል በምድረ በዳ ከተጓዘ በኋላ «ይበቃኛል ... ነፍሴን ውሰድ» ብሎ ወደ እግዚአብሔር እንዲሞት ለመነ። እኛስ ስንት ጊዜ ተልእኮአችንን ሳንጨርስ «በቃኝ» ብለናል? ኤልያስ በዚህን ጊዜ፣ ምንም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ቢሆንም እግዚአብሔር በተግሣጽ ሳይሆን በምህረት ይገናኘዋል። መልአክ ሁለት ጊዜ ከእንቅልፉ ቀስቅሶ ይመግበዋል። «የእግዚአብሔር መልአክ ደግሞ ሁለተኛ ጊዜ መጥቶ ዳሰሰውና የምትሄድበት መንገድ ሩቅ ነውና ተነሥተህ ብላ አለው። ተነሥቶም በላ ጠጣም፤ በዚያም ምግብ ኃይል እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ሄደ» ቁ. 7-8።

በዚያም በዋሻ ውስጥ ሳለ «ኤልያስ ሆይ፣ በዚህ ምን ታደርጋለህ? የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ እርሱ መጣ» ቁ.9። ከእግዚአብሔር ፈቃድና መስመር ወጥተን በምንገኝበት ጊዜ፤ የሚመጣልን ቃል ይኸው ቃል ነው። «በዚህ ምን ታደርጋለህ?» ይህም ሆኖ፤ ባሪያው የጠፋበት ጌታ፣ ወደ ባሪያው ሄዶ የሚያሰማው የጉብኝት ድምፅ እንጂ የተግሣጽ ቃል አልነበረም። ኤልያስም የነበረውን አቤቱታና የነፍስ ሰቆቃ ከተናገረ በኋላ፤ እግዚአብሔር «በትንሽ የዝምታ ድምፅ ይናገራዋል። ኤልያስ እግዚአብሔርን እስከዚያች ቀን ድረስ የሚያውቀው በእሳትና በአውሎ ነፋስ፣ በታላቅ ድምፅ ነበር። አሁን ግን እግዚአብሔር ከዚህ በፊት በማያውቀው መንገድ ይገናኘዋል። «በትንሽ የዝምታ ድምፅ»። እኛስ፣ ስንት ጊዜ የእግዚአብሔርን ትንሽ የዝምታ ድምፅ በልባችን ውስጥ መስማት ይሳነናል? የመንፈስ ቅዱስን «ትንሽ የዝምታ ድምፅ መስማት የሚሳነን ዋና ምክንያት፣ ብዙ ጊዜ የምንጠባበቀው እንደ አውሎ ነፋስና ነጐድጓድ ያለ ታላቅ ድምፅና ምልክትን ስለምንጠባበቅ ነው።

ከዚህ በኋላ፣ «ሂድ በመጣህበትም መንገድ በምድረ በዳ ወደ ደማስቆ ተመለስ» (ቁ. 15) የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤልያስ መጣለት። ከእግዚአብሔር ፈቃድና መስመር ወጥተን በሽንፈት በምንጓዝበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር፤ በሽንፈት በመጣንበት መንገድ <u>በድል እንድንመለስ</u> ይፈልጋል። «በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን»። እርሱ ሽንፈታችንን በድል የሚለውጥ አምላክ ነው።

እግዚአብሔር ኤልያስን፤ «በመጣህበት መንገድ ተመለስ» ብቻ ሳይሆን፤ ከተመለሰ በኋላ አገልግሎቱን ካቆመበት ስፍራ እንዲቀጥል ያዘዋል።

«ከዚያም በደረስህ ጊዜ በሶርያ ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ አዛሄልን ቀባው፤ በእስራኤልም ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የናሜሲን ልጅ ኢዩን ቀባው፣ በፋንታህም ነቢይ ይሆን ዘንድ የአቤልምሖላን ሰው የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ቀባው፤ (ቁ. 15-16)፡፡

የእግዚአብሔር ሰው፤ ሥራውን ሳይጨርስ ከምድር አይሰናበትም፡፡ የኤልያስ «በቃኝ ግደለኝ» ጸሎት ምን ያህል ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ እንደሆነ የምናየው ገና ያልጨረሰው ታላላቅ ሥራዎች እንደቀሩት ስናነብ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ምሳሌአችን እንደመሆኑ መጠን በዮሐ 17÷4 «እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ» ብሎ ይጸልያል፡፡ እግዚአብሔርን የምናከብረው የሰጠንን ሥራ በምድር ሳለን ስንጨርስ ነው፡፡

ኤልያስም፤ የዲያብሎስን ቃልና ዛቻ ሰምቶ ከእግዚአብሔር መስመር ከወጣ በኋላ፤ የእግዚአብሔር ህያው ቃል እንደገና መጥቶለት መንገዱ ሲቀናለትና በምድር ላይ የተመደበለትን ሥራ ሲያከናውን እንመለከታለን፡፡ ከቁ. 19-21 ያለው ክፍል የሚያሳየን፣ እግዚአብሔር ዘርዝሮ ከተናገረው የኤልያስ ተልእኮዎች ውስጥ አንዱ የሆነውን «በፋንታህ ነቢይ ይሆን ዘንድ ... ኤልሳዕን ቀባው» የተባለውን ተልዕኮ ሲፈጽም ነው፡፡

ኤልያስም ወደ እርሱ አልፎ መጐናጸፊያውን ጣለበት ... እርሱም ተነሥቶ ኤልያስን ተከትሎ ሄደ፣ ያገለግለውም ነበር» (ቁ. 19-21)

ከዚህ ክፍል የምንማረው አንድ ትልቅ ነገር አለው እርሱም፤ እግዚአብሔር ለኤልያስ የዘረዘራቸውን ሦስት ተልዕኮዎች፤ ማለትም በሶሪያ ላይ ንጉሥ እንዲሆን አዛሄልን መቀባት

- በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዲሆን ኢዩን መቀባት
- በፋንታው ነቢይ እንዲሆን አልሳዕን መቀባት፡፡

እነዚህን ሦስት ተልእኮዎች ተመልክተን፤ ኤልያስ የፈጸመው ከሦስቱ የመጨረሻውን ብቻ፣ ኤልሳዕን መቀባት እንደሆነ ስናይ በአእምሮአችን ጥያቄ ሊፈጥርብን ይችላል፡፡ ነገር ግን ጥያቄ ሳይሆን ትልቅ መንፈሳዊ ምስጢር ያለው ነገር በውስጡ አለ፡፡

የአዛሄልንና የኢዩን መቀባት የምናየው በ2ነገ 8÷7-15 እና በ2ነገ 9÷1-10 ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ሰዎች የተቀቡትም በነቢዩ ኤልሳዕ አማካኝነት ነው፡፡ የተቀቡበትም ዘመን፤ ተልእኮው ወደ ኤልያስ ከመጣና ኤልያስ በእሳት ሠረገላ ከተወሰደ ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው፡፡ በተለይ ኢዩ የተቀባው ቢያንስ ከ18 ዓመታት በኋላ ይሆናል፡፡ አክአብ እስኪሞት ወደ 4 ዓመታት 1ነገሥ 21÷22፤ 22÷1 አክአብ ሞቶ የአክአብ ልጅ አካዝያስ ሁለት ዓመት ነገሠ 1ነገ 22÷51፡፡ እርሱ ከሞተ በኋላ ወንድሙ ኢዮራም 12 ዓመታት ነገሠ 2ነገ 8÷25፡፡ 4+2+12=18 ዓመታት፡፡ የአዛሄልና የኢዩ መቀባት ለኤልያስ የተነገረለት ተልዕኮ ቢሆንም፤ ኤልያስ ኤልሳዕን በቀባ ጊዜ፤ በተዘዋዋሪ በኤልሳዕ በኩል ተልዕኮውን እንደፈጸመ እናያለን፡፡ እኛም እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠውን አንዳንድ ተልእኮዎች የምንፈጽመው፤ እነዚያን ተልእኮዎች የሚፈጽሙ የእግዚአብሔር ሰዎችን <u>በማፍራት</u> ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከብዙሃኑ ይልቅ በጥቂት ደቀመዛሙርቱ ላይ ብዙ ጊዜውን ያጠፋ የነበረው፤ በእነርሱ በኩል ዓለምን እኛንም ጭምር እንደሚደርስ ስለሚያውቅ ነው፡፡ ከአገልግሎት ትልቅ ስፍራ ሊሰጠው የሚገባው «ራስን መተካት» እንደሆነ ያስተምረናል፡፡

1ነገ ምዕ 20፡ -

ይህ ምዕራፍ በድሮ (በ1962 እ.ኤ.አ) እትም ስለ ናቡቴ ታሪክ የሚናገር ምዕራፍ ቢሆንም፤ ከዚያ በኋላ በተጻፉት እትሞች 1980 እ.ኤ.አ. እና 1993 እ.ኤ.አ. አዲሱ በመደበኛ ትርጉም ምዕ 20 ስለ ሰማርያ ከተማ በሶርያ ንጉሥ መከበብ ሲተርክ፣ የናቡቴን ታሪክ የምናገኘው በምዕ. 21 ላይ ነው፡፡ በተለያዩ የእንግሊዝኛ እትሞች የተጻፉት እትሞችም

የሁለተኛውን ዓይነት ቅንብር ያላቸው በመሆኑ፣ እኛም ይህንን ሁሉ በግንዛቤ በማስገባት ምዕራፍ 20ን «የሰማርያን ከተማ መከበብ» ምዕ. 21 ደግሞ «የናቡቴን ታሪክ» በሚተርከው ቅንብር አቅርበናል።

ከላይ በጠቀስነው ቅንብር መሠረት፤ ምዕ. 20 የሚተርከው፤ የሶርያ ንጉሥ ወልደ አዴር የሰማርያን ከተማ በመክበብ እንደወጋትና በዚያን ጊዜ የእስራኤል ንጉሥ ከነበረው ከአክአብ ጋር ያደረገውን ፍልሚያ ይህ ምዕራፍ ትልቅ የመንፈሳዊ ውጊያ ትምህርት ያዘለ ምዕራፍ ነው። ትምህርቱንም የምናገኘው፣ በተለይ የእስራኤል ንጉሥ አክአብ ከሶርያ ንጉሥ ከወልደ አዴር ጋር ባደረገው ግንኙትና የቃላት ልውውጥ ውስጥ ከምናያቸው ስህተቶች ሁኔታዎች ነው።

ከቁ. 1-6 የምናነበው፤ የሶርያ ንጉሥ ወልደ አዴር ሰማርያን ከከበበ በኋላ ለእስራኤል ንጉሥ የላከበትን መልእክቶች እና የአክአብን ምላሽ ነው።

«ወልደ አዴር እንዲህ ይላል፣ ብርህና ወርቅህ ለእኔ ነው ሴቶችህና መልካሞቹም ልጆችህ ለእኔ ናቸው፤ ብሎ ወደ ከተማይቱ መልእክተኞችን ላከ። የእስራኤልም ንጉሥ መልሶ ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፣ አንተ እንዳልህ ነው፤ እኔ ለእኔም የሆነው ሁሉ የአንተ ነው አለ» (ቁ. 3-4)። በእነዚህ ሁለት ጥቅሶች የምናየው፤ ወልደ አዴር (ጠላት) በማስፈራራት የዛቻን ቃል ሲልክ፤ አክአብም ለዚህ የዛቻ ቃል ሲንበረከክና ጠላት ከጠየቀው በላይ («እኔ ለእኔም የሆነው ሁሉ የአንተ ነው») ራሱን ለጠላት ሲሸጥ ነው። በነገራችን ላይ፤ አክአብ፣ የሆነውን ወልደ አዴርን የሚጠራው «ጌታዬ ንጉሥ ሆይ» በማለት ነበረ። አክአብ በጠላት ጌትነት ሥር ራሱን አድርጎ  ጠላቱ እንዲነግሥበት ፈቀደ።

ይህንን የአክአብን ምላሽ የሰማ ወልደ አዴር፤ የልብ ልብ ስለተሰማው፤ እንደገና ጠንከር ያለ መልእክት ለአክአብ ይልክበታል።

«ደግሞም፤ መልእክተኞች ተመልሰው ወልደ አዴር እንዲህ ይላል፡- ቀድሞ፡ ብርህንና ወርቅህን፣ ሴቶችህንና ልጆችህንም ትሰጠኛለህ ብዬ ልኬብህ ነበር፤ ነገም በዚህ ጊዜ ባሪያዎቼን እልክብሃለሁ፣ ቤትህንም የባሪያዎችህንም ቤቶች ይበረብራሉ፣ <u>ደስ የሚያሰኛቸውንም ሁሉ</u> በእጃቸው አድርገው ይወስዳሉ አሉ» ቁ. 5-6። ለነገሩ፤ ወልደ አዴር የላከው ሁለተኛ መልእክት፤ አክአብ ከመለሰው መልስ ጋር የሚስማማ ነው። አክአብ፤ «እኔ ለእኔም ያለኝ ሁሉ የአንተ ነው» ብሎ ራሱን ሽጦ ስለነበረ፤ ወልደ አዴር «ደስ የሚያሰኛቸውን ሁሉ» ይወስዳሉ ማለቱ አያስገርምም። ከጠላት ጋራ ድርድር ከጀመርን «ደስ የሚያሰኘውን ሁሉ» ማድረግ እንደሚፈልግ መዘንጋት የለብንም። ከጠላት ከዲያብሎስ ጋራ መቼም ቢሆን የእርቅ ስምምነት ማድረግ አንችልም። አትንካኝ አልነካህም ብለን ከጠላት ጋር መስማማት አንችልም።

አክአብ የወልደ አዴርን ሁለተኛ ምላሽ ሲሰማ የአገሩን ሽማግሌዎች ጠርቶ ምክር ይጠይቃል። ሁልጊዜ የሽማግሌዎችን /የአስተዋዮችን/ ምክር መጠየቅ መልካም ነው። እነርሱም አክአብን «አትስማው፤ እሺም አትበለው» አሉት (ቁ. 8)። በጣም ትልቅ ምክር ነው የሰጡት። መቼም ቢሆን ጠላታችን ዲያብሎስን መስማትም ሆነ እሺ ማለት የለብንም። በክርስትና ሕይወታችን ችግር የሚመጣው ጠላታችን ዲያብሎስን «ስንሰማው» እና «እሺ ስንለው» ነው።

አክአብም ይህንን የሽማግሌዎች ምክር ሰምቶ፤ «ለወልደ አዴርም መልእክተኞች፡- ለጌታዬ ለንጉሡ ለእኔ ለባሪያህ በመጀመሪያ የላከኸን ሁሉ አደርጋለሁ፤ ይህን ግን አደርገው ዘንድ አይቻለኝም በሉት አላቸው» ቁ. 9። ይህንን የአክአብን ምላሽ ብናጤን፤ የሽማግሌዎቹን መልካም ምክር ከሰማ በኋላ እንኳን፤ ወልደ አዴርን፤ «ጌታዬ» ማለቱን አልተወም። እንደውም «ለእኔ ለባሪያህ» በማለት ራሱን ለጠላቱ ባሪያ አድርጎ ያቀርባል። ይህም ሳያንሰው፣ አሁንም

ከጠላቱ ጋር ድርድሩን ቀጠለ። ከዚህ መለስ መውሰድ ትችላለህ፣ ከዚህ መለስ ግን እባክህ ተውልኝ ዓይነት ድርድር ነው።

ወልደ አዱር፣ በአንድ በኩል «ባሪያህ ነኝ» በሌላ በኩል ደግሞ «ይህንን ማድረግ አልችልም» የሚለው ቋንቋ  አልተዋጠለትም። ጠላት፣ ባሪያ ካደረገ በደንብ ቀጥቅጦ መግዛት እንጂ ከዚህ መለስ የሚል ነገር አያውቅም። ወልደ አዱር፣ «እምቢ ካልክ አሳይሃለሁ» ዓይነት መልስ ለአክአብ፣ ሲልክለት፣ አክአብ «በቃ! ለሰልፍ የሚታጠቅ ጋሻ ጦሩን እንደሚያወልቅ አይመካ አለው» (ቁ. 11)። አክአብ አሁን ገና ትክክለኛውን ቃል ሲናገር እንሰማለን። ጠላትን «በቃ» ካላልን በስተቀር ምንም ዓይነት ድርድር ከእርሱ ጋር አይሠራም። አክአብ የተናገረው በአጭሩ፣ «ገና እኮ አልተሟከርንም፣ ብዙ አትደንፋ» ማለቱ ነው።

አክአብ ጠላቱን «በቃ» ሲል፣ እግዚአብሔር ነቢይ ልኮ ለአክአብ መናገር ጀመረ፣ «እነሆም ነቢይ ወደ እስራኤል ንጉሥ ወደ አክአብ ቀርቦ፡- እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ይህን ብዙ ጭፍራ ሁሉ ታያለህን? እነሆ ዛሬ በእጅህ አሳልፌ እሰጠዋለሁ፣ እኔም እግዚአብሔር እንደሆንሁ ታውቃለህ አለ» (ቁ. 13-14)። ከሰይጣን ጋር እየተደራደርን እግዚአብሔር አይናገረንም። እግዚአብሔር የሚናገረን ጠላታችንን «በቃ» ስንል ነው። «ሁለት ሐሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው» ያዕ 1፥7-8። እግዚአብሔር የሚረዳን ቁርጥ ውሳኔ ስናደርግ ነው። አክአብ ጠላቱን «በቃ» ስላለ፣ እግዚአብሔርም ስለረዳው፣ ታላቅ የነበረውን የሶርያን ሠራዊት ሲያሸንፍ እናያለን፣ «... ሶርያውያንንም በታላቅ ውጊት ገደላቸው» ቁ. 21።

ከዚህ ድል በኋላ እንደገና የእግዚአብሔር ነቢይ ወደ አክአብ መጥቶ «የሶርያ ንጉሥ በሚመጣው ዓመት ይመጣብሃልና ሂድ በርታ፣ የምታደርገውንም ተመልከትና እወቅ አለው» ቁ. 22። ጠላት አንዴ ስላሸነፍነው ጓዙን ጠቅልሎ አይጠፋም። እንደገና አመቺ ጊዜ ፈልጎ መምጣቱ አይቀርም።

«የሶርያም ንጉሥ ባሪያዎች አሉት /ለወልደ አዱር/፣ አምላካቸው የተራሮች አምላክ ነው፣ ስለዚህ በርትተውብን ነበር፣ ነገር ግን በሜዳ ላይ ከእነርሱ ጋር ብንዋጋ በእርግጥ እንበረታባቸዋለን» ቁ. 23። በዚህ ምክር በመመራት በአመቱ ወልደ አዴር ታላቅ ሠራዊት አሰልፎ በአክአብ ላይ መጣ። «የእግዚአብሔርም ሰው ቀርቦ የእስራኤልን ንጉሥ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ሶርያውያን፡- እግዚአብሔር የተራሮች አምላክ እንጂ የሸለቆ አምላክ አይደለም ብለዋልና ይህን ታላቅ ጭፍራ ሁሉ በእጅህ አሳልፌ እሰጠዋለሁ፣ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ አለው» ቁ. 28።

ይህ ከላይ የተጠቀሰው የጠላት አባባል፣ ሰይጣን አማኝን የሚከስበት አንዱ መንገድ ነው። እያንዳንዳችን በተለያዩ ችግሮችና ፈተናዎች /በሸለቆ/ በምናልፍበት ጊዜ ይመጣና «አምላክህ የተራራ አምላክ እንጂ፣ የሸለቆ አምላክ አይደለም፣ ስለዚህ ነው በዚህ በመከራ ጊዜ በሸለቆ ውስጥ የተወህ ይለናል።

«በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፣ ነገር ግን አይዟችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ» የሚለውን የጌታን ቃል ያላስተዋለና በሸለቆ ያላለፈ ክርስቲያን፣ በዚህን ጊዜ ወደ ኋላ ለማፈግፈግ ይከጅላል፣ አንዳንዱም ወደ ኋላ ይመለሳል።

በሌላ አንጻር ደግሞ፣ ከአምላኩ ጋር በሰላምና በበረከት በተራራ ያለውን ክርስቲያን፣ ኢዮብን እንደ ከሰሰው፣ በውኑ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራ በከንቱ ነውን? እርሱንና ቤቱን በዙሪያውም ያሉትን ሁሉ አላጠርህለትምን? የእጁን ሥራ ባርከህለታል፣ ከብቱም በምድር ላይ በዝቶአል። ነገር ግን እጅህን ዘርግተህ ያለውን ሁሉ ዳብስ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል»

ኢዮብ 1፥9-11። በማለት እርሱ «የተራራ ክርስቲያን እንጂ «የሸለቆ ክርስቲያን» አይደለም። ወደ ሸለቆ ወረድ ብታደርገው ይክድሃል እያለ እያንዳንዳችንን ይከሰናል።

አምላካችን «የተራራ አምላክ» ብቻ ሳይሆን «የሸለቆም» በችግራችንም፣ በኃዘናችንም፣ በማጣት፣ በመገርጣትም አምላክ ነው። እኛስ? «የተራራ ብቻ» ክርስቲያኖች ነን፣ ወይስ «የሸለቆም» ክርስቲያኖች ነን፣ ወይስ «የሸለቆም» ክርስቲያኖች ነን? እግዚአብሔር ሲባርከን፣ ሲፈውሰን፣ ሲያበላን፣ ሲያጠጣን፣ ጸሎታችንን ሲመልስልን ብቻ ነው የምናመልከው ወይስ እንደ ኢዮብ «የሆነው ነገር ይምጣብኝ ሥጋዬን በጥርሴ እይዛለሁ፤ ነፍሴንም በእጄ አኖራለሁ፤ እነሆ ቢገድለኝ ስንኳ እርሱን በትእግሥት እጠባበቃለሁ፣ ነገር ግን መንገዴን በፊቱ አጸናለሁ» (ኢዮብ 13፥13-15) እንላለን? እንደ ሲድራቅ ሚሳቅና አብድናጎ «ባያድነን እንኳን» ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን እንችላለን?

በቁ. 29 እና 30 ላይ፣ እስራኤል በሶርያ ላይ ታላቅ ድልን እንዳገኙ እናነባለን «የእስራኤልም ልጆች ከሶርያውያን በአንድ ቀን መቶ ሺህ እግረኛ ገደሉ። ... ቅጥሩም በቀሩት በሃያ ሰባት ሺህ ሰዎች ላይ ወደቀ። ወልደ አዴርም ሸሽቶ ወደ ከተማይቱ ወደ እልፍኙ ውስጥ ገባ።» እግዚአብሔር ሲዋጋልን ቅጥሩም (ተፈጥሮም) እንኳን ይተባበራል።

ከቁ. 31-34 የምናየው፤ ወልደ አዴር ተሸንፎ ከተመለሰ በኋላ አክአብ ምሕረት ሲያደርግለትና ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን ሲገባ ነው። «ባሪያዎቹም እነሆ የእስራኤል ቤት ነገሥታት መሐሪዎች እንደ ሆኑ ሰምተናል፤ በወገባችን ማቅ እንታጠቅ በራሳችንም ገመድ እንጠምጥም ወደ እስራኤልም ንጉሥ እንውጣ ምናልባት ነፍስህን ይምራታል አሉት።» በዚህም ምክር መሠረት ወልደ አዴር ለአክአብ እንዲህ ብሎ በባሪያዎቹ ይልክበታል፤ «ባሪያህ ወልደ አዴር፦ ነፍሴን ትምራት ዘንድ እለምንሃለሁ ብሎአል።» አክአብም «ገና በሕይወቱ አለን? <u>ወንድሜ ነው</u> አለ።» ከመቼ ወዲህ ነው ሊያጠፋን የሚወድ ጠላት ወንድማችን የሆነው? አክአብ እግዚአብሔርን ሳይጠይቅ ከጠላቱ ጋር ድርድር ሲያደርግ እናያለን። የወልደ አዴር ባሪያዎችም፤ «ወንድምህ ወልደ አዴር አለ አሉት። እርሱም ሂዱ አምጡት አለ። ወልደ አዴርም ወደ እርሱ መጣ በሰረገላውም ላይ አስቀመጠው። ወልደ አዴርም፦ አባቴ ከአባትህ የወሰዳቸውን ከተሞች እመልስልሃለሁ አባቴ በሰማርያ እንዳደረገ አንተ በደማስቆ ገበያ ታደርጋለህ አለው። አክአብም እኔም በዚህ ቃል ኪዳን እሰድሃለሁ አለ። ከእርሱም ጋር ቃል ኪዳን አድርጎ ሰደደው።» እግዚአብሔር ያልማረውን ሲምር፤ ሊያጠፋው አመቺ ጊዜ ከሚጠባበቅ ጠላቱ ጋር ቃል ኪዳን ሲጋባ እናያለን።

ከቁ. 35-43 ትእይንታዊ ትንቢታዊና ትምህርታዊ የሆነ የእግዚአብሔርን መልእክት እናነባለን።

«ከነቢያት ወገን አንድ ሰው፣ <u>በእግዚአብሔር</u> ቃል ባልንጀራውን ምታኝ አለው። ሰውዬውም ይመታው ዘንድ እንቢ አለ። እርሱም፦ የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማህምና እነሆ ከእኔ በራቅህ ጊዜ አንበሳ ይገድልሃል አለው። ከእርሱም በራቀ ጊዜ አንበሳ አግኝቶ ገደለው።» ይህ ሰው፤ «እንዴት ወንድሜን እመታሃለሁ» በሚል ሰብአዊ ርኅራኄ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሲተላለፍ ነው የምናየው፤ ምክንያቱም፣ ነቢዩ «ምታኝ» ያለው «በእግዚአብሔር ቃል» ነበረ። በአንበሳ የተገደለበትም ምክንያት «የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማህምና» ተብሎ ነው። ከዚህ የምንማረው፤ መጨከን ቢያስፈልገንም እንኳን የእግዚአብሔርን ቃልና ድምፅ መታዘዝ እንዳለብን ነው። በአጉል ሰብአዊ ርኅራኄና ትህትና፤ ከእግዚአብሔር ይልቅ ርኅሩህ የሆንን ይመስል ለጠላታችንም ሆነ ለወንድማችን ምሕረትን እናሳያለን ብለን «የእግዚአብሔርን ቃል መተላለፍ» የለብንም።

በዚህ ክፍል የምናየው ነቢይ፤ «ሌላ ሰው አግኝቶ ምታኝ አለው:: ሰውዬውም መታው በመምታቱም አቆሰለው::» ይኸኛው ሰው፤ ምናልባት ከዚህ በፊት የነበረው ሰው የደረሰበትን ቅጣት ሰምቶ ይሆናል፤ «በአንበሳ ከምበላ ብታዘዝ ይሻላል» ብሎ ነቢዩን እስኪያቆስለው ድረስ የመታው::

ነቢዩ ዋናው ተልእኮው ለአክአብ እንደነበረ ከቁ. 38-43 ያለው ክፍል ያስረዳናል:: ለአክአብ መልእክቱን ለማስተላለፍ ተመትቶ መቁሰልና በመንገድ ላይ ተቀምጦ ንጉሡን መጠ ባበቅ ነበረበት:: ከዚህ ክፍል እንደምናየው የዚህ ነቢይ ተልእኮ፣ ቃልን ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ለአክአብ «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» ብሎ መናገር ብቻ ሳይሆን ተመትቶና ቆስሎ በመንገድ ላይ ወድቆ መታየትንም ያካትት ነበር:: ቃልን ከእግዚአብሔር ተቀብሎ መናገር ቀላል ነው፤ አንዳንድ ጊዜ ግን የእግዚአብሔር መልእክት «መመታትን» እና «መቁሰልንም» ያካትታል:: እግዚአብሔር በእኛ በኩል ሊያስተላልፍ የሚፈልገው መልእክት ብዙ ጊዜ «ከምንቀበለው መከራ» ጋር የተያያዘ ነው:: እኛ ግን መከራና ቁስል የሌለበት አገልግሎት ነው የምንፈልገው::

«ነቢዩም ሄዶ በመንገድ አጠገብ ንጉሡን ቆየው፤ ዓይኖቹንም በቀጸላው ሸፍኖ ተሸሸገ:: ንጉሡም ባለፈ ጊዜ ወደ እርሱ ጮኸ:- ባሪያህ ወደ ሰልፍ መካከል ወጣ፤ እነሆም አንድ ሰው ፈቀቅ ብሎ ወደ እኔ አንድ ሰው አመጣና:- ይህን ሰው ጠብቅ፣ ቢኰበልልም ነፍስህ በነፍሱ ፈንታ ትሆናለች፤ ወይም አንድ መክሊት ብር ትከፍላለህ አለኝ:: ባሪያህም ወዲህና ወዲያ ሲመለከት ጠፋ አለው:: የእስራኤልም ንጉሥ ፍርድህ እንዲሁ ይሆናል፤ አንተ ፈርጀኸዋል አለው:: ፈጥኖም ቀጸላውን ከዓይኑ አነሣ የእስራኤልም ንጉሥ ከነቢያት ወገን እንደ ሆነ አወቀው:: እርሱም:- እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- እኔ እርም ያልሁትን ሰው ከእጅህ አውጥተሃልና ነፍሱ በነፍስህ ፈንታ ሕዝብህም በሕዝቡ ፈንታ ይሆናሉ፤ አለው:: የእስራኤልም ንጉሥ እየተቆጣና እየተናደደ ወደ ቤቱ ተመለሰ፣ ወደ ሰማርያም መጣ::»

ይህ መቼም በጣም አስደናቂ ትእይንት ነው:: እግዚአብሔር መልእክትን ማስተላለፍ ያውቅበታል:: ተግሣጽን ወይም ፍርድን ወደ ሕይወታችን ሲያመጣ ደግሞ፤ ራሳችን በራሳችን ላይ እንድንፈርድ፤ የራሳችንን ጎሊና እንደመስታወት በማድረግ ራሳችንን እንድናይ ያደርገናል:: አክአብ በዚያ በመንገድ ላይ ወድቆና ራሱን ሸፋፍኖ በነበረው ሰው ላይ ለመፍረድ አላወላወለም፤ ነገር ግን በዚህ ሰው ላይ ሲፈርድ በራሱ ላይ እንደፈረደ አላወቀም ነበር:: ነቢዩ ናታን መጥቶ ኦርዮንን በተመለከተ ለንጉሥ ዳዊት ያቀረበውን ትእይንታዊ የሆነ መልእክት ይመስላል 2ኛ ሳሙ. 12÷1-13

አክአብ፣ እግዚአብሔርን እርም ያለውን ሰው በመልቀቁ፣ ሊያጠፋው የሚገባውን ጠላት ባለማጥፋቱ፤ አጉል ሰብአዊ ምሕረት የተደረገለት ወልደ አዴር አክአብ ከእርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በማፍረስ፣ አመቺ ጊዜ ሲያገኝ እስራኤልን መልሶ እንደወጋ በ2ኛ ነገ 6÷24 እናነባለን:: «ያላጠፋነው ጠላት ያጠፋናል»:: በ1ኛ ነገ ምዕ. 22 አክአብ የሞተው ከሶርያ ጋር ሲዋጋ እንደሆነ እናነባለን::

1ኛ ነገ ምዕ. 21:- ቀደም ብለን እንደገለጽነው፤ በአዲሱ መደበኛ ትርጉምና በ1980 በታተመው ትርጉም፣ እንዲሁም በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶችም ይህ ምዕራፍ የሚተርከው የናቡቴንና የአክብአን ታሪክ ሲሆን፤ የ1962ቱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትም ግን የናቡቴን ታሪክ ምዕራፍ 20 ላይ ያቀርበዋል::

ይህ ምዕራፍ፤ የሰውን ክፋት፣ የእግዚአብሔርን ፍርድና ምሕረት በአንድነት ግልጽ አድርጎ የሚያሳይ ምዕራፍ ነው:: ናቡቴ በአክአብ ቤት አጠገብ የነበረውን የወይን ቦታ ለአክአብ ለመሸጥም ሆነ ለመለወጥ «የአባቶቼን ርስት እሰጥህ ዘንድ እግዚአብሔር ያርቅልኝ»

በማለት እምቢ ስላለው ንጉሡ «ተቆጥቶና ተናድዶ ወደ ቤቱ ገባ፡፡ በአልጋውም ላይ ተጋድሞ ፊቱን ተሸፋፈነ፣ እንጀራም አልበላም፡፡» ይህንንም ያየች ሚስቱ ኤልዛቤል፡- «አንተ አሁን የእስራኤልን መንግሥት ትገዛለህ? ተነሣ እንጀራም ብላ፣ ልብህም ደስ ይበላት የኢይዝራኤላዊውን የናቡቴን የወይን ቦታ እሰጥሃለሁ አለችው፡፡» ይህንንም ብላ በአክአብ ስም ደብዳቤ በመጻፍና በማኅተሙ በማተም ናቡቴ ተወግሮ እንዲሞት አስደረገች፡፡

«ከናቡቴም ጋር ወደ ተቀመጡት ሽማግሌዎችና ከበርቴዎች ደብዳቤውን ላከች፡፡ በዳብዳቤውም፡- ስለ ጾም አዋጅ ንገሩ፣ ናቡቴንም በሕዝቡ ፊት አስቀምጡት፤ ሁለትም ምናምንቴ ሰዎች በፊቱ አስቀምጡና እግዚአብሔርንና ንጉሡን ሰድቧል ብለው ይመስክሩበት፣ አውጥታችሁም እስኪሞት ድረስ ውገሩት ብላ ጻፈች፡፡»

ከዚህ ክፍል የምናየው፤ ናቡቴ በከተማው ውስጥ ከነበሩት ሽማግሌዎችና ከበርቴዎች ማለትም «አሉ» ከሚባሉት የከበሩ ሰዎች አንዱ እንደነበረ ነው፡፡ በተጨማሪም፤ ብዙ ጊዜ አመጽና ክፋት የሚሠራው የጽድቅን ካባ ተሸፋፍኖ እንደሆነ እናያለን፡፡ «ስለ ጾም አዋጅ ንገሩ» አለች ኤልዛቤል፡፡ «ለአመጽና ለነፍስ ግድያ መጾም»፡፡ በአዲስ ኪዳን፤ ጳውሎስን እስኪገደሉ ድረስ እንዳይበሉና እንዳይጠጡ (ለመጾም) በመሐላ የነበሩ አርባ ሰዎች ታሪክ እናነባለን፡፡ (ሐዋ 23÷12-15)፡፡

አልዛቤል ደብዳቤውን የላከችላቸው «ሽማግሌዎችና ከበርቴዎች» ኤልዛቤል እንዳዘዘችው ሲያደርጉና ናቡቴን በሐሰት አስመስክረውና ወግረው ሲገድሉ እናነባለን፡፡ በንጉሥ ስም የወጣ ትእዛዝ ቢሆንም፣ እንዲህ ዓይነቱን ክፉ ትእዛዝ መታዘዝ የለባቸውም ነበር፡፡

አክአብም፤ የናቡቴን መሞት ሲሰማ «ይወርሰው ዘንድ ወደ ኢይዝራኤላዊው ወደ ናቡቴ ወይን ቦታ ሊወርድ ተነሣ፡፡»

ይህንንም ሁሉ የሚያይ አምላክ፤ ኤልያስን «የእስራኤልን ንጉሥ አክአብን ትገናኝ ዘንድ ውረድ፤… አንተም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ገድለህ ወረስኸውን? ብለህ ንገረው፡፡» በማለት ጆሮን ጭው የሚያደርግ የፍርድን ቃል በአክአብና በኤልዛቤል ላይ ያስተላልፋል፡፡ መቼም የእግዚአብሔር ፍርድ፤ ሰዎች ሁሉ አንድ ቀን በእርሱ ፍርድ ዙፋን ፊት ሲቀርቡ ብቻ ሳይሆን አሁንም በምድር ላይ እያሉ የሚከሰት ነገር ነው፡፡ እርሱ በሰማይ ብቻ ሳይሆን በምድርም ሆነ ከምድር በታች «የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ነው»፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከሁሉም የሚያስደንቀው ነገር፤ አክአብ በኤልያስ በኩል የመጣውን አስደንጋጭ የእግዚአብሔር ፍርድ በሰማ ጊዜ «ልብሱን ቀድዶ ገላውን ማቅ አለበሰ፣ ጾመም፣ በማቅም ላይ ተኛ ቅስስ ብሎም ሄደ፡፡ ደግሞም አክዓብ በፊቴ እንደተዋረደ አየህን? በፊቴ የተዋረደ ስለሆነ በልጁ ዘመን በቤቱ ላይ ክፉ ነገር አመጣለሁ እንጂ በእርሱ ዘመን ክፉ ነገር አላመጣም የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ ቴስብያዊው ወደ ኤልያስ መጣ፡፡» በእግዚአብሔር ታላቅ ፍርድ መካከል የእግዚአብሔርን ታላቅ ምሕረት እናያለን፡፡ በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔር ቃል ስለ እግዚአብሔር ፍርድ በማጠናበት ጊዜ እዚህ ክፍል ላይ ስደርስ ከእግዚአብሔር ፍርድ ይልቅ በእግዚአብሔር ምሕረት ተማረኩ፡፡

አ! የእግዚአብሔር ምሕረት እንዴት ድንቅ ነው? በምሕረቱ ባለጠጋ የሆነ፤ ምህረቱ ለዘላለም የሆነ፣ እግዚአብሔር አምላካችን ይባረክ! ያልጠፋነው በጽድቃችን ሳይሆን ከምሕረቱ የተነሳ ነው፡፡ ምህረቱ ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው፡፡ «በደልን ይቅር የሚል፣ የርስቱንም ቅሬታ ዓመፅ የሚያሳልፍ እንደ አንተ ያለ አምላክ ማን ነው? ምሕረትን ይወድዳልና ቁጣውን ለዘለዓለም አይጠብቅም፡፡ ተመልሶ ይምረናል፣ ክፋታችንንም ይጠቀጥቃል፣ ኃጢአታችንንም በባህሩ ጥልቅ ይጥለዋል፡፡» (ሚክ 7÷18-19)

ያዕቆብ በመልእክቱ «...ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና» (ያዕ. 5፥11) ይለናል። በተጨማሪም፣ «... ምሕረት በፍርድ ላይ ይመካል» በማለት ያዕ. 2፥13 ከፍርድ ይልቅ የሚበልጠው ምሕረት እንደሆነ ያስገነዝበናል። በአዲሱ መደበኛ ትርጉም «... ምሕረት በፍርድ ላይ <u>ያይላል</u>» ይላል።

በ1ነገ ምዕ 20 ላይ የእግዚአብሔር ቃል ስለ አክአብ ሲናገር «በእግዚአብሔር ፊት ክፋት ለመሥራት ራሱን እንደ ሸጠ፣ ሚስቱም ኤልዛቤል እንደ ነዳችው እንደ አክአብ ያለ ሰው አልነበረም» (ቁ. 25) በማለት ምን ዓይነት ሰው እንደነበረ ይገልጽልናል። ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ሰው እንኳን ራሱን በእግዚአብሔር ፊት ባዋረደ ጊዜ የእግዚአብሔር ልብ ሲመለስለትና ምሕረትን ሲቀበል እናያለን።

1ኛ ነገ 22፡- ንጉሡ አክአብ በሐሰተኛ ነቢያት ተነድቶ በሶርያ ሠራዊት እንደተገደለ ያሳያል።

ንጉሡ አክአብ እግዚአብሔር ጠላቱን በእጁ ጥሎለት በነበረበት ጊዜ ሳያጠፋው ቀርቶ አሁን ከሦስት ዓመታት በኋላ «የእስራኤልም ንጉሥ ባሪያዎቹን፡- ሬማት ዘገለዓድ የእኛ እንደሆነች፣ እኛም ከሶሪያ ንጉሥ እጅ ሳንወስዳት ዝም እንዳልን ታውቃላችሁን? አላቸው።» (ቁ. 3)

የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥንም «በሬማት ዘገለዓድ እንዋጋ ዘንድ ከእኔ ጋር ትመጣለህን?» ብሎ ይጠይቀዋል። «ኢዮሳፍጥም የእስራኤልን ንጉሥ፡- የእግዚአብሔርን ቃል አስቀድመህ ትጠ ይቅ ዘንድ እለምንሃለሁ አለው» ቁ. 5። ኢዮሣፍጥ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ስለነበረ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አስቀድሞ ማወቅ አስፈላጊ እንደሆነ የተረዳ ሰው ነበረ። «የእስራኤልም ንጉሥ አክዓብ <u>ነቢያቶቹን</u> አራት መቶ የሚያህሉትን ሰዎች ሰብስቦ፡- ወደ ሬማት ዘገለዓድ ለሰልፍ ልሂድን? ወይስ ልቅር? አላቸው። እነርሱም፡- እግዚአብሔር በንጉሥ እጅ አሳልፎ ይሰጣታልና ውጣ አሉት።» ቁ. 6 እነዚህ 400 ነቢያት የእግዚአብሔር ነቢያት ሳይሆኑ «የአክአብ ነቢያት» እንደነበሩ «ነቢያቶቹን» የሚለው ቃል ያስረዳናል። የእርሱ ራሱ ነቢያት ስለነበሩ የልቡን ምኞት ሲያጸድቁለት እናያለን።

ንጉሡ ኢዮሳፍጥ ይህንን ሳይረዳ አልቀረም፣ «ኢዮሣፍጥ ግን፡- እንጠይቀው ዘንድ ሌላ የእግዚአብሔር ነቢይ በዚህ አይገኝምን? (ቁ. 7) ብሎ ይጠይቃል። የ400 ነቢያቶቹ ነገር አልተዋጠለትም። የእስራኤልም ንጉሥ፣ «ሚክያስ የሚባል አንድ ሰው አለ፣ ነገር ግን ክፉ እንጂ መልካም ትንቢት አይናገርልኝምና እጠላዋለሁ አለው» እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢያት ሁልጊዜ መልካም የሚናገሩልን ሳይሆኑ፣ መመለስ ሲያስፈልገን የሚገሥጹን፣ የሚመክሩን፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ስንሆን ደግሞ አይዞህ የሚሉን ናቸው።

ሚክያስን እንዲጠራ የተላከው ጃንደረባ ሚክያስን እንዲህ ይለዋል፣ «እነሆ ነቢያት ሁሉ በአንድ አፍ ሆነው ለንጉሡ መልካምን ይናገራሉ፣ ቃልህም እንደቃላቸው እንዲሆን መልካም እንድትናገር እለምንሃለሁ» (ቁ.13)። የእግዚአብሔር ሰው የሚናገረው የብዙኀኑን ድምፅ ሰምቶ ከሆነ የሰው አገልጋይ እንጂ የእግዚአብሔር አገልጋይ ባልሆነ። ሚክያስም ለጃንደረባው፣ «ሕያው እግዚአብሔርን እግዚአብሔር የሚነግረኝን እርሱን እናገራለሁ አለ» ቁ. 14።

ሚክያስም በንጉሡ ፊት ቆሞ፣ በነቢያቶቹ ሁሉ አፍ ያለው ሐሰተኛ መንፈስ እንደሆነ እንዲህ በማለት ያስረዳል፣ «እግዚአብሔርም፡ -ወጥቶ በሬማት ዘገለዓድ ይወድቅ ዘንድ አክዓብን የሚያሳስት ማን ነው? አለ። ... መንፈስም ወጣ በእግዚአብሔርም ፊት እኔ አሳስተዋለሁ አለ። እግዚአብሔርም በምን? አለው፣ እርሱም ወጥቼ በነቢያቶቹ ሁሉ አፍ ሐሰተኛ መንፈስ እሆናለሁ አለ። እግዚአብሔርም ማሳሳትስ ታሳስተዋለህ፣ ይሆንልህማል ውጣ እንዲህም አድርግ አለው» ቁ. 20-22።

ይህ፤ ነቢዩ ሚክያስ የሚተርክ ትዕይንት፤ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ በጥቂት ስፍራዎች፤ የሰማያትን መጋረጃ ከፈት አድርጎ ከምድራዊው ክስተት ጀርባ /Bhind the Scenes/ የሚደረገውን ትእይንት ከሚተርኩት ታሪኮች አንደኛው ነው:: ሌላ ጎልቶ የምናየው ተመሳሳይ ሰማያዊ ትእይንት በኢዮብ ምዕ 1 እና 2 የምናየው ትእይንት ነው:: በእነዚህ ትእይንቶች በምድር ላይ እየተከሰተ ያለ ክስተት እናያለን፤ በአንጻሩ ደግሞ በምድር ላይ ከሚከሰተው ክስተት አስቀድሞ በሰማያት የተከናወነና ለምድራዊው ክስተት ምክንያት የሆነ ሰማያዊ ትዕይንትን ያሳየናል:: በዚህ አሁን በምናጠናው ምዕራፍ (1ኛ ነገ ምዕ 22) ውስጥ የምናየው አክዓብን ለማሳሳት በሰማይ የተደረገውን ትእይንት ሲሆን፤ በኢዮብ ምዕ. 1 እና 2 ግን እግዚአብሔር ኢዮብን ይተማመንበት ስለነበረ ከሰይጣን ጋር እንደተወራረደበት የሚያሳይ ትዕይንት ነው:: በእያንዳንዳችን ሕይወት የሚከሰቱ ጎላ ብለው የሚታዩ ነገሮችም ሰማያዊ ጅማሬ ሊኖራቸው ይችላል ብሎ ማሰቡ ጠቃሚ ነው:: እንደ ኢዮብ እግዚአብሔር እየተወራረደብን ይሆን ወይስ እንደአክአብ መንገዳችንን በእግዚአብሔር ፊት ስላጣመምን፤ ወጥመድ እየተዘረጋብን ይሆን?

ዳዊት «ከቸር ሰው ጋር ቸር ሆነህ ትገኛለህ፤
ከቅን ሰው ጋር ቅን ሆነህ ትገኛለህ፤
ከንጹህ ጋር ንጹህ ሆነህ ትገኛለህ፤
ከጠማማም ጋር ጠማማ ሆነ ትገኛለህ::» መዝ 18፥25፤26

ብሎ እንደተናገረው የአክአብ ሕይወት ጠማማ ስለነበረ እግዚአብሔር በጠማማ መንገድ ሲመጣበትና ሲወድቅ እናያለን::

ነቢዩ ሚክያስ እውነተኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን መልእክት ካስተላለፈ በኋላ የሐሰተኛ ነቢያቶቹ ዋና መሪ ሴዴቅያስ «ሚክያስን ጉንጩን በጥፊ መታውና አንተን ሊናገር የእግዚአብሔር መንፈስ በምን መንገድ ከእኔ አለፈ? አለ» ቁ. 24:: «እኔነት» የነገሠበት አገልግሎት ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን መንፈስ የሚጻረር ነው:: እውነተኛ አገልግሎት ደግሞ ዋጋ ስለሚያስከፍል፤ ንጉሡ መልእክተኞቹን «በደኅና እስክመለስ ድረስ ይህን ሰው በግዞት አኑሩት የመከራም እንጀራ መግቡት፣ የመከራም ውኃ አጠጡት» ብሎ ያዛል (ቁ. 27):: «ሚክያስም:- በደኅና ብትመለስ እግዚአብሔር በእኔ የተናገረ አይደለም:: ደግሞም:- አሕዛብ ሁሉ ሆይ ስሙኝ አለ» ቁ. 28:: ሚክያስ በአምላኩ ምን ያህል እንደሚተማመን ያሳየናል::

በእርግጥ ሚክያስ እንደተናገረው አክአብ በጦርነቱ ተወግቶ በሰረገላው ላይ እንዳለ ሞተ:: በነቢዩ ኤልያስም እንደተናገረ «ውሾች ደሙን ላሱት» ቁ. 38::

በዚህ ክፍል ስለ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ጥቂት መጥቀስ አግባብ ይሆናል:: ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በዚያም ክፍል ሆነ በ2ኛ ዜና 17-20 ስናይ እግዚአብሔርን የሚፈራና ቅን ንጉሥ እንደነበረ ማየት እንችላለን:: የእርሱ አንድ ድክመት ክፉ ከነበረው ከእስራኤል ንጉሥ ከአክዓብና ከልጁ ከኢዮራም ጋር መተባበሩ ነበረ:: መተባበር ብቻ ሳይሆን ጋብቻም እንደነበረ በ2ኛ ዜና 18:1 ላይ ተጠቅሷል:: 1ነገ 22 እና 2ኛ ዜና 18 ተመሳሳይ ታሪክ የሚተርኩ ምዕራፎች ስለሆኑ አንዳንድ ነጥቦችን ከ2ኛ ዜና 18 ማየቱ ታሪኩን በሙላት እንድናየው ይረዳናል:: በ2ኛ ዜና 18:2 ላይ «... አክአብም ለእርሱና ማለትም ለኢዮሣፍጥ ከእርሱ ጋር ለነበሩት ሕዝብ ብዙ በጎችንና በሬዎችን አረደ፤ ከእርሱም ጋር ወደ ሬማት ዘገለዓድ ይሄድ ዘንድ <u>አባበለው</u>» ይላል::

አዮሣፍጥ ቅንና መልካም ንጉሥ ቢሆንም በክፉ <u>መባበል</u> ግን ደካማ ጎኑ ነበር::

«እንጠይቀው ዘንድ የእግዚአብሔር ነቢይ የሆነ ሌላ ሰው በዚህ አይገኝምን?» ብሎ ነቢዩ ሚክያስ በመጣ ጊዜ፤ ነቢዩ ሚክያስ የተናገረውን ድንቅ ትእይንትና ትንቢት ሁሉ ሰምቶ «ጆሮ ዳባ ልበስ» ብሎ ዝም ብሎ ወደ ጦርነቱ መውጣቱ ሌላው ስህተቱ ነበር:: የእግዚአብሔር ነቢይ የማይደመጥ ከሆነ «የእግዚአብሔር ነቢይ በዚህ አይገኝምን?» ብሎ መጠየቁን ትርጉም

የለሽ ያደርገዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ እኛም የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቃችን «ጠይቄ ነበር» ብለን ኀሊናችንን ለመደለል ይሆን? ፈቃዱን በገለጸልን ጊዜ ፈቃዱን የማናደርግ ከሆነ በእውነትም ራሳችንን እያታለልን ነው፡፡

እግዚአብሔር ግን መሐሪ ስለሆነ ድካሙን ሳይሆን የልቡን ቅንነት አይቶ፤ በጦርነት ውስጥ ተከቦ ሊወጋ ሲል «ኢዮሣፍጥ ግን ጮኸ፣ እግዚአብሔርም ረዳው፣ አምላኩም ከእርሱ መለሳቸው» 2ኛ ዜና 18፡31፡፡

እግዚአብሔር ከጠላት ፍላጻ ቢታደገውም ስለ መተላለፉ ግን ሳይገስጸው አልቀረም፤ «የይሁዳም ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ወደ ቤቱ ወደ ኢየሩሳሌም በደኅና ተመለሰ፡፡ ባለ ራእዩ የአናኒ ልጅ ኢዩ ሊገናኘው ወጣ፣ ንጉሡንም ኢዮሣፍጥን <u>ከሐዲውን ታግዛለህን</u>? ወይስ <u>እግዚአብሔርን የሚጠሉትን ትወድዳለህን</u>? ስለዚህም ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ቁጣ ሆኖብሃል፡፡ ነገር ግን የማምለኪያ ዐፀዶቹን ከምድር አስወግደሃልና፣ እግዚአብሔርን ትፈልግ ዘንድ ልብህን አዘጋጅተሃልና መልካም ነገር ተገኝቶብሃል አለው፡፡» 2ኛ ዜና 19÷1-2፡፡

«ከሐዲውን ታግዛለህን?» «እግዚአብሔርን የሚጠሉትን ትወዳለህን?» ማንን እንደምናግዝ ማወቅ አለብን፡፡ ሳናውቅ ዲያብሎስን እያገዝን እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን፡፡ ሳናውቅ የዓለምንና የዲያብሎስን ነገር እየወደድን እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን፡፡ እግዚአብሔር በክፋቱ ሊያጠፋው ያሰበውን ሰው ሲረዳ፤ ሳያውቀው የእግዚአብሔርን ሐሳብ እየተጻረረ ነበር፡፡

እግዚአብሔር ምንም ኢዮሣፍጥን ቢቆጣውም፤ «እግዚአብሔር ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ፣ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፣ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና» ዕብ 6÷10 ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ ኢዮሣፍጥ ያደረገውን መልካም ነገር «ጎሽ» ይለዋል፡፡

*Global Good News Literature*
*P.O.Box 451336*
*Los Angeles, CA 90045*
(C) Copyright 2014